ለ ወንድሜ፡ ጋሻዬ፡ ፋሲል፡ [illegible]

[illegible]



[illegible]

ወንድምህ፣

[illegible]

Oct. 20/2000,

STOCKHOLM

Kortehat Talilign?
``Why cut it off?´´
(Collections of sensational poems)
**Hailu Gabre Yohannes (Gemoraw)**
December 1992, (First Edition)
Stockholm-Sweden.

# «ቆርጠሀት ጣልልኝ?»

## ኃይሉ (ገሞራው)

ፍ ን ዳ ታ - ቁጥር 91 - 100

ስቶክሆልም —— 1992

# እ ል ፊ ት

የግጥሚቴን ደራሲነት አይንፈገኝ እንጂ፣ አንድ መቶ ሺ ቅጂዎችን ካሳተምሁ በኋላ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር እንደፈለገው ቢያደርጋት አለመቃወሜንና በዚሁም ውሳኔዬ መሠረት አሳልፌ መስጠቴን አረጋግጣለሁ።

# ቆርጠሀት ጣልልኝ?

## እና


2 – ሰካራም አህያ ፥

3 – ነጭ አሉ ! ነጭ ወይ !

4 – ድመቶች ሲያዘሉ ፥

5 – ወይዘሪት ወይዘሮ !

6 – መውጫት አጥራኝ !

7 – ወርሳትን ነው ወርሳት !

8 – ምን አይነት ዘመን ነው !

9 – አውሬ ቡራቡሬ !

10 – ለኔ ለኢምንቴ !

# በ ረ ከ ት

ይህች ግጥም በበረከትነት የቀረበችው ፤ የትም ይኑሩ የትም ፤ ምን ጊዜም ይኑሩ ምንም ፤ከአን ጀታቸው በሐቅ ፤ በሰው መሠረታዊ እኩልነት አምነው ለሚ ታገሉና ይህም ቅዱስ ተጋድሎ ለሚጠይቀው መሥዋዕትነት ራ ሳቸውን ያለአንዳች ማመንታት በማቅረብ ፤ በትግሉ ነዲድ ውስጥ ተለብልበውና ተቃጥለው ላለፉ ሁሉ ነው ።

# የመለከከት ሸውራራነት

# ወይም

## የ ስ ተ ሳ ሳ ብ   ጠ ን ጋ ራ ነ ት !

መተርጎም ሐሳብ ፥ ብዙ ምሁራንን ሲያወናብድና ሲያተራምስ ኖሯል ። አደገኛነቱ ይህን ያህል ብሎ እስከ መገመት ድረስ ያስቸግራል ። አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ ምሁራን ነን ባዮች ፥ ሌሎች የጻፉትን ሐሳብ እንጠልጥለው በመውሰድ ለራሳቸው በሚያመችና በሚጠቅማቸው መንገድ በመተርጎም ፥ የደራሲውን መሠረተ ሐሳብ በመቀልበስ ፥ አጠይመውና አጥቁረው ያቀርባሉ ። በራሳቸው የተንሸዋረረ አመለካከት ፥ የቀረበውን ሐሳብ ጠምዝዘው በመቀየድ ፥ የደራሲውን ሐሳባዊ ተልዕኮ በግኮላሸት ያጨናግፋሉ ። ይህ አይነቱ የመተርጎማን ተንኮል ፥ ከከባድ ወንጀልነት አልፎ ፥ ከሞራል ግዴታዎች ክልል ውጭ የሚንገባወድ፥ አፀያፊና ወናኛ ተግባር ነው ። በዚህ እትም ውስጥ ሠፍረው የምታገኙአቸውን ግጥሞች ሁሉ ፥ እኔ በታኘሁበት ሐሳባዊ ተልዕኮ አቅጣጫ ብቻ ፥ ርቱዕ በሆነ ቀና መንገድ እንብባችሁ እንደአምትረዱልኝ ፥ ተስፋዬም እምነቴም ነው ።

# አ ጣ ቃ ሽ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| 1 – ገጸ አርዕስት | 3 |
| 2 – እልፊት | 5 |
| 3 – የዚህ እትም ግጥሞች | 7 |
| 4 – በረከት | 9 |
| 5 – ያመለካከት ጠንጋራነት | 11 |
| 6 – አጣቃሽ | 13 |
| 7 – አንደርድሮ አድራሽ | 15 |
| 8 – ቆርጠሃት ጣልልኝ | 69 |
| 9 – ሰካራም አህያ | 91 |
| 10 – ነሽ አሉ ! ነሽ ወይ ! | 113 |
| 11 – ድመቶች ሲያሾሩ ! | 131 |
| 12 – ወይዘሪት ወይዘሮ ! | 153 |
| 13 – መውጫት አምራጁ ! | 171 |
| 14 – መርሳትን ነው መርሳት ! | 193 |
| 15 – ምን አይነት ዘመን ነው ! | 227 |
| 16 – አውሬ ቡራቡሬ ! | 241 |
| 17 – ለኔ ለኢምንቱ ! | 257 |
| 18 – ጠማራት ( Cards ) | 269 |



# አንደርድሮ አድራሽ

ከዚህ በፊት ታትመው ለተሠራጩ ግጥሞቼ እትሞች ሁሉ የግጥሞቼን ይዘታዊ ምንነትና ፥ ባጠቃላይም የግጥምን አወቃቀራዊ ባሕርያት ለመግለጽ በማሰብ ፥ እንደመቅድም እያደረግሁ መለስተኛ መንደርደሪያ ማስፈሬ ይታወሳል ። ዓላማውም ፥ አንባቢዎቹን ከግጥሞቼ ይዘቶች ጋር ይበልጥ ለማቀራረብና በተለይም ግጥም ወዳጅ ለሚሆኑት ወገኖች ፥ መሠረታውያን የሆኑ መምሪያዎችን ለማስተዋወቅ ፥ የማደርገው ሙከራዬ ነበር ። በግጥሞቼ አንፃር

ችው ቁም ነገር ያዘለ መሆኑን ተረድቼበታለሁ ። ያቀረቡልኝንም ግምገማ ፥ እንደገንቢ ሒሰነቱ ፥ ልጠቀምበት ወስኛለሁ ።

ገና ከመጀሐፉ እምብርታዊ ፅምቡጥ ላይ ሳይ ሳይደርሱ ፥ በመንደርደሪያው ክፍል ውስጥ ፥ አረፋ የሚደደፍቁ እንዳሉም ተረድቻለሁ ። በበኩሌ ፥ ሰፋ ያለ መቅድማዊ መግለጫ መስጠቴ ፥ ይዘቱ ይበልጥ እንዲያመረቃ ለማድረግ እንጂ ፥ አንባቢዎቼ ራሳቸው አስበውና ተመራምረው ቁም ነገሮቹን ፈልፍለው እያገኙም በሚል ግምት አይደለም ።

በርግጥም አንዳንዶቹ ግጥሞች ቅኔ ለበስ የሆነ ባሕርይ ስላላቸው ፥ እኔ ላስተላልፍ ከፍለግሁት ውሱን ተልዕኮአዊ መንፈስ ውጭ በሚፈነገጥ ፥ በአንባቢዩ አስተሳሰባዊ አሸንዳ ፥ ጭልጥ ብሎ ይፈስ ይሆናል ፥ የሚል ፍራቻ ስላለብኝ ፥ በመጠኑም ቢሆን የመንደርደሪያው መኖር ግድብ ያበጅለታል የሚል ግምት አለኝ ። እንዲያ ግድረኔም የግጥሙን ይዘታዊ ትላና ፥ መልክና ጎራ እያመላከተ አስተካከሉ ለአንባቢዩ እያመቻቸ ይጠርግለታል እንጂ ፥ መንገደ ሐሳቡን እያደበዝዘበትም ብዬ እምናለሁ ። በተለይም ፥ በ

ቅርብ ጊዜ ውስጥ ፥ ላሳትም ያዘጋጀኋቸው የግጥም ስብስቦቼ ፥ ይህን አባባሌን ጉልህ አድርገው እንደሚገልፁልኝ ተስፋ አድርጌባቸዋለሁ ። ከነዚያ ግጥሞቼ ውስጥ አብዛኞቹ የውጭ ሐሳቦች መተርጉማን ስለሆኑ ፥ መንፈስን የመበወዝና የማጦዝ ተፅዕኖአዊ አደጋ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነው ።

በሥነ ጽሑፍ መስክ የተሠማራ ብዕረኛ እንደሚያደርገው ሁሉ ፥ የራሴን ብሔራዊ የሥነ ፅሑፍ ቅርስ ይበልጥ እንዲጎለበትና እንዲዳብርም ለማድረግ ፥ ከሌላው ሕዝብም ባሕላዊ ክምችት ፥ በጎ በጎውንና ጤናማውን እየመረጡ ማዳቀልም ሆነ ማስተዋወቅ ፥ የተለመደ ሆኗል ። በዚህም መመሪያ መሠረት ፥ እኔም በትምህርት ተሠማርቼ ከነበርኩበት ከሩቅ ምሥራቅ የባሕልና የሥነ ጽሑፍ መድበላዊ ቅርስ ውስጥ እንደባሕል መሸጋገሪያ ድልድይነታቸው ሊያገለግሉ የሚችሉትን ፥ ሥነ ጽሑፋዊ አውታሮችን ብቻ በመምረጥ — ሥነ ጽሑፍ ባሕሎችን የማገናኘት ክፍል አለውና — ለኢትዮጵያውያን አንባብያን ይጠቅማሉ ብዬ ያመንኩባቸውን እየተረጎምኩ ማስተዋወቅ ጀምሬአለሁ ። ሁለት የተለያዩ ባሕሎች የሚያንፀባርቆትን ግለ-ወጣዊ ያመለክከት ዝንባሌዎች ፥ አስታራቂና



አጓዳኝ ማዕከላዊ ሰላጭ መንገድ ፈልጎ ማቀራረብና ቢቻልም ማዋሐድ ፥ ያንዲቱን ዋሕድ ዓለም ልዩ ልዩ ሕዝቦች ፥ የትም ሀገር ይኑሩ የትም ፥ ለማቀራረብ ይረዳል ። እንዲህም ማድረግ ከተቻለ ፥ መንዝ በመለስ ጥቃቅን ልዩነቶች የሚያቀጣቅጧቸውን የዓለም ሕዝቦች ለማግባባት ፥ መለስተኛም ቢሆን መፍትሔአዊ አስተዋፅዖ አለው ። በዚህም ተግባር አንፃር ፥ ያንዱን ባሕላዊ ክዋኔ ከሌላው ጋር ሊያመላክት የሚያስችል ፥ የባሕል መስኮታዊ ጭላንጭል ፈልፍሎ ለማግኘትና እርስበርሳቸውም ጎን ለጎን እንዲተያዩ ማቀናጀት ፥እጅግ ከባድ ተግባር ባይሆንም ፥ ቀላል አይደለም ። በተለይም ፥ በምድር ላይ ተነጥለው የሚገኙበት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ፥ እጅግ ያራራቃቸው በመሆኑ ፥ አቀራርቦ ለማዛመድ ያስቸግራል ። የበረዶ አካባቢ ያፈራውን ሰው ፥ ለሞንበር ተጎራባች ከሆኑ ሀገሮች ሰው ጋር ፥ በአስተሳሰብ ለማቆራኘት የሚደረገው ሙከራ ፥ እጅግ መጣሪ ነው ። መሠረታዊ ፍጥረታቸው ግን ፥ ሁለቱም አይነቶች ፥የሰው ልጆች

ናቸው ። እንደስውነታቸው ያላቸውን የጋራዮሽ ግዕከላዊ አ
ባቢ እንዲሞሉ ማድረጉም ፣ የበስተኋላቸውን ልዩነቶች ለ
መሸርሸርና ብሎም ጥርዶ ለማስተካከል ስለሚረዳ ፣ መከራው
አድካሚ ቢሆንም ፣ ግዱ ወዉታግ ነው ።

በባሕላዊ ቅርፁና በሥነ ጽሑፋዊ ይዘቱም የ
ወጥቅር አምሳልነት የሌለው ፣ የሩቅ ምሥራቅ ( የቻይና፣
የጃፓን ፣ የኮሪያ. . . ) ሕዝቦች ኀሊናዊ ነፀብራቅ የሆነ
ው ሥነ ጽሑፋዊ ወድበል ፣ ከኢትዮጵያዊው ጋር በንፃሬ ሲ
ቀርብ ፣ ከራሱ ከግጥሙ አካላዊ ይዘት ይልቅ ፣ ምንነቱን
ይበልጥ አጉልቶ ለማሳየት ፣ የወንደርደሪያ መግለጫዎች ከ
ፍተኛ ሚና አላቸው ። የሁለቱም ባሕሎች አስተሳሰባዊ ይዘ
ቶች እንዳሉ የተጠበቁ ሆነው ፣ በተቻለ መጠን አቀራርቦ
ና አጠጋግቶ ለመተርጎም ፣ በቀጥታ ከግጥም ወደ ግጥም ከ
መመለስ ይልቅ ፣ ሐተታዊ መግለጫ በተጨማሪ ከማከል ሌላ፣
የተሻለ አማራጭ አይገኝም ። ለማጥማቂ ምሳ ፣ የወንደርደ
ሪያ መግለጫዎች ፣ የቁርስ ያህል ናቸውና ።

ሁለት የተለያዩ ምንዝር ባሕሎችን ፣ በንፅፅር



ወልክ ለማቅረብ ፣ ራሱ ግጥሙ ብቻውን መቅረቡ በቂ አይደ
ለም ። የዚህን አባባል ምንነት ለማስረዳት ፣ ጥሩ ማሳሌ
ዎች የሚሆኑን ፣ ተከታዮቹ ግጥሞች ናቸው ።የሁለቱም ግጥ
ሞች ሐሳባዊ ይዘት የቻይናውያን ኀሊናዊ ቅርስ ሲሆን ፣
ለኢትዮጵያዊ አንባቢ በሚጥም ወልክ ተቀናብረው የቀረቡ ና
ቸውና ልብ ብላችሁ ወርምሯቸው ።

( ሀ ) ደርዘን ልጆች ወልዳ ( ዱር ነው በሽታዋ )

( ለ ) ሰካራም አህያ ( በዚህ እትም ውስጥ )

በኢትዮጵያውያን እምነታዊ ባሕል አስተሳሰብ
የቅድመ ሞት ሕይወትና የድኅረ ሞት ሕይወት ምንነት ፣ ግ
ልጽና ጉልህ በሆነ ትርጓሜ ተመዝግቦ ይገኛል ። የሌሎች
ሕዝቦች ባሕላዊ ቅርሶች ፣ በዚህ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ም
ን አይነት አመለካከትና አስተሳሰብ እንዳላቸው ለማሳየት
የላይኞቹ ሁለት ግጥሞች ጥሩ ቀላጤዎች ናቸው ።

ከራሱ ብሔራዊ የባሕል ክልል ፈንጠር ብሎ
በመውጣት ፣ ቀለም ለመቁጠር የወጣ ተማሪ ፣ እንደዚህ ያ
ሉ የባሕል ልዩነቶችን ማንጠርና ፣ ቢቻልም የሚገናኙበትን

እትብት ወፀ መጠቀም ፥ ተግባሩም ግዴታውም ነው ። ስለሆ
ነም ፥ የሩቅ ምሥራቅ ባሕላዊ እምነት ፥ በይዘቱ የደለበ
በዘመናት ዕድሜውም የጠነከነና እያሌ ትውልዶችንም ሲያፈራ
ርቅ የኖረ በመሆኑ ፥ ስለ ቅድመ ሞት ሕይወትና ስለ ድኅ
ረ ሞትም ያካበተውን ተመክሮና የሕይወት ትዝብቶች ፥ ለኢ
ትዮጵያዊ ሰብዕና ማጣበሪያነት ማቅረብ ፥ ከፍተኛ አስተዋ
ፅዖ ነው ። ባሕላዊ ልዩነት የሚለውን ሐሳብ ከረቂቅነት
ባሕርይነቱ ለማላቀቅ ፥ አንዲት ቁራጭ ምሳሌ ማቅረቡ ይበ
ጃል ። በአንዳንድ የሩቅ ምሥራቅ ሀገሮች ባሕላዊ የአካል
አገላለጽ ቋንቋ ( Gestural Language ) ፥ ራ
ስን ከግራ ወደ ቀኝ ማነቃነቅ ፥ የአዎንታ ምልክት ሲሆን
መሰሉ የአንገት በላይ ንቅናቄ ፥ በኢትዮጵያዊው ባሕል ግ
ን ፥ የእሉታ ሐሳብ መግለጫ ምልክት ነው ። የነዚህ ባሕ
ሎች ተጠቃሚ የሆኑ ሁለት ሰዎች ቢገናኙና ሌላም የጋራ ቋ
ንቋ ባይኖራቸው ፥ እነዚህ ሁለት ሰዎች እርስ በርስ ሊና
ጡ ነው ማለት ነው ። ስለዚህም ነው ፥ የባሕል መተርጉማ
ን መኖር የሚያስፈልገውም የሚጠቅመውም ።



ይህን የመሰለውን የሕዝቦች ሕልውናዊ ቁም ነገር
በየመልኩ መዝግቦ ለየሀገሩ ሰው ማስተላለፍ ፥ ከሚለያዩ
በት እንከኖቻቸው ይልቅ የሚስማሙበትን ነጥቦች ጠቁሞ ለማ
ሳየት እጅግ ይረዳል ። ለሰው ልጅ ፥ ይበልጥ ሊጠቅመው
የሚችለው ፥ ከልዩነቱ ይልቅ አንድነቱ ነው ። ከሥነ ጽሑ
ፍ ተግባራዊ ተልዕኮዎችም ፥ ቀዳሚውና አይነተኛው ክፍል፥
ይኸው ነው ።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ፥ መተርጉመ ሕይወት ምንነቱ
በግልጽ ነጥሮና ተከትቦ ይገኛል ። ኩፋሌ ሰብዕ የሆኑት
ሁለቱ የሰው ባሕርያት ምንጮች ፥ ሥጋና ነፍስ ወይም ትስ
ብዕትና መለኮት እንደሆኑ ፥ በምድብ ትምህርቶች ውስጥ ሳ
ይቀር ፥ የዕውቀት ምድብ ቦታውን ይዞ ይገኛል ። ሥጋ በ
ግዙፍ አካላዊ ባሕርዩ ሟች እንደሆነና ፥ በግብዝነቱም ፈ
ራሽና በሰባሽ እንደሆነ አግናዊ ሐቅነቱ ተረጋግጦ ታምኖበ
ታል ። ከምድራዊ ሕልውናው ሲሰናበትም ፥ እንደአፈርነቱ
አፈር ሆኖ በሕይወት በኖረበት ምድር ላይ ለተወሰነ ጊዜ
በኢምንትነት ይቆይና ፥ በስተኋላ ላይ በትንግኤ ተሐድሶ

አግኝቶ እንደብዙቱ "በገሐነም ይጠበሳል ወይም በነርያም ሲዝናና ለዘለዓለም ይኖራል" ተብሏል ። ይህም የሚከናወነው÷ ሲሞት ተለይታው ተሠውራበት የነበረችውን የሕይወቱ መንቀሳቀሻ የነበረችውን ፥ ቀዳማይ ነፍሱን ይዞ ነው ።

በባሕርይዋ ፥ ነባቢት ለባዊትና ሕያዊት የሆነችዋ ነፍስ ፥ እንደማኅደሯ ሥጋ ሞት የሌለባት በመሆኗ ፥ ምንም አይነት ሕልፈት ሳያገኛት ለዘለዓለም እንደምትኖር ፥አማንያን ሁሉ ይቀበላሉ ። ይህ የነፍስ ትርጓሜያዊ ምንነት ውሳኔ ፥ በሩቅ ምሥራቅ እምነታዊ ጥራዞች ውስጥም ፥ ሐቅነቱ ተጠብቆ የተመዘገበ ነው ። የኛም ሆነ የሩቅ ምሥራቅ አማንያን የነፍስ ሕያውነት እሳቤ ፥ መሰልና ሚዛናዊ ቢሆንም ፥ በሕይወት ትርጉም አስተሳሰባቸውና አቀራረባቸው አንጻር ግን ፥ የሰማይና የምድርን መራራቅ ያህል ልዩነት አላቸው ። ይህን ልዩነት መንዝረው ሊዘረዝሩት ይገባል ።

ያንድን ሕዝብ ባሕላዊ አስተሳሰብ ለሌላ ሕዝብ እየመነዘሩ ማስተዋወቅ ፥ ጥቅሙ ከምን ላይ ነው? የሚል ጠያቂ ይኖር ይሆናል ። የባሕል ባሕልነቱ ልዩ ከመሆኑ ላይ



እስከሆነም ድረስ ፥ ይህ ጥያቄ በርግጥ ስሑ አይወጣለትም መልሱ ግን ብዙ የሚያንጠራራ አይደለም ። ሰዎች በተለያዩ ክፍለ ምድር ላይ ይኑሩ እንጂ ፥ የሚገኙት በአንዲት የምድር ዓለማዊ ሉል ላይ ነው ። በመሠረታዊ ፍላጎታቸው አንፃርም ፥ የትም ይኑሩ የትም ፥ ተመሳሳይ ናቸው ። በየአካባቢያቸው ተፈጥሮአዊ አስገዳጅነት ፥ አንዳንድ ልዩነቶች ቢታይባቸውም ፥ የሚጠበቅ ነው ። ያንዱን ክፍለ ምድር ነዋሪ ሰው ፥ ያካባቢው ዕፀዋት ፥ ማያት ፥ ምግቦች ፥ ዓየራዊ ጠባይ,..ወዘተ በርቱዕና በኢርቱዕ መንገዶች ባሕርዩ ሰብዕናውን ሞርደው በእሱነቱ ይቀርፁታል ። ያም እሱነቱ÷ ያካባቢው ውጤት ነው ። ቆለኛው ሰውና ደገኛው ሰው ቢለያዩ ፥ ያ አይነቱ ያካባቢ የተፈጥሮ ልዩነት ያስከተለው ፅዓ ነው ። የቆለኛውን ሁኔታዊ ምንነት ደገኛው ቢያውቀው የደገኛውንም እንዲሁ ቆለኛው ቢረዳው ፥ እንደሰውነታቸው የሚግባቡበት ዘዴ ሊፈጠር ይችላል ። ስለዚህም ነው ፥ በየማኅበረ ሰቡ ውስጥ ፥ የባሕል ፥ የትምህርትና የሥነ ጽ

ሎና ሠራዊት ምሁራን ለዚህ ተግባር ተመድበው እንዲያገለግሉ የተደረገው ። የሌላውን ሕዝብ ባሕል እንድናውቅ የሚገፋፋንም ይኸው ሰው የመሆን ባሕርያችን አገብሮን ነው ። የሰውና ሰው መተዋወቅ !

ሕዝቦችን ለማወቅ ደግሞ ዋናውና አቋራጩ ዘዴ ፥ የኅሊናቸው ጭማቂ የሆነውን ባሕላቸውን በሥርዓት አጥንቶ ምንነቱን በሚገባ መረዳት ነው ። በዚህ መስክ አስተዋፅዖ ከሚያደርጉ የዕውቀት ዘርፎች አንዱ ፥ ሥነጽሑፍ እንደሆነ ቀደም ባለው አንቀጽ ጠቅሻለሁ ።

የሩቅ ምሥራቅ ምድር ፥ አብዛኛው የሰው ልጅ የሚኖርበት ክፍለ ዓለም ነው ። የሀገራችን ሕዝብ ፥ ስለሌላው ዓለም ሕዝብ ለማወቅ ላለው ፍላጎት ማሟያ እንዲሆን፥ ከየሀገሩ ሕዝቦች ባሕል ፥ ታሪክ ፥ ሥነ ልቦና ወዘተ በመጠኑም ቢሆን በየጊዜው ቀርቦለታል ። ከታሪክ ፀሐፊዎችና ከደራስያን ፥ በተለያዩ መንገዶች ተቀነባብረው ፥ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ምግበ ኅሊና እንዲሆኑ ፥ በየጊዜው መዘጋጀታቸውን እናውቃለን ። የኔም መሰል ሙከራ ፥ የዚሁ የ



ማስተዋወቂያ መስመር ቅጥያ ነው ።

የሩቅ ምሥራቅ ሕዝቦች ፥ እጅግ የደለበ የመንፈስ ቅርስ አላቸው ። የብዙ ሺህ አመታት ድልብ በመሆኑም ፥ ንቀው የሚተዉት አይደለም ። አብዛኛውም ባሕላዊ ክምችታቸው ፥ ስለ ኅሊና ጥራት ፥ ስለ ልቦና ቅንነትና ባጠቃላይም ስለ መንፈስ ተሐድሶ ፥ ላያሌ አዝማናት ከኖሩ ትውልዶች ተጨምቆ የነጠረ ተመክሮ ስለሆነ ፥ ጠቃሚነቱ የመድኃኒት ያህል ነው ።

እነዚህን የኅሊና ቅርሶች ፥ እንደየአይነታቸው በየዘርፉ በየዘርፉ መድበው ፥ በባሕረ መዝገባቸው ውስጥ ከትበው ፥ ለተከታታይ ትውልዶች እንዲያልፉ አድርገዋል ። ከብዙኃኑ የመንፈስ ቅርሶች ውስጥ ፥ ዋና ዋናዎቹን እንኳሮች ብቻ ቢጠቀሱ ፥ የቡዲሒዝም ፥ የታዎይዝም ፥ የኮንፌየስዝም ፥ የሺንቶይዝም . . . ወዘተ ቀዳምያን ናቸው ።

ያብዛኛው የሩቅ ምሥራቅ ሕዝብ ሥርዓተ ሕይወት የተነደፈው ፥ በነዚህ መራሕያን ሕላዌ ሕግጋት ላይ ነው ። እነዚህ የመንፈስ ቅርሶች ፥ ከሕይወት ፍልስፍና አ

ልፈው ፥ ነባር እምነቶች እስከመሆን በቅተዋል ። በእነዚህም የእምነቶች ድባባዊ ጥላ ስር ያሉ ሁሉ ፥ አዲስ ዘመን ያፈራቸው ትኩስ ፍልስፍናዎች ሳይነድፏቸው ፥ ዛሬም ቢሆን በመንፈስ ወሪነት የሚጠቀሙት ፥ በነዚሁ ምርኅተ ሕይወት ድንጋጌዎች ነው ። ተወልደው እስኪሞቱ ድረስ ፥ በዚህ ምድራዊ ኑሮአቸው በሚኖሩበት ወቅት ፥"እምቅድመ ይፍጥር የእምር ግብር"እንደሚባለው ፥ ባሕርየ ሕይወታቸውን የሚወስነው ፥ ይኸው መመሪያ ነው ። በበኩሌ እጅግ የሚያስገርመኝ ፥ ያንድ ሰው ግማሽ ዕድሜ በሚሆነው ፥የግማሽ ምዕት አመት ደመኛ አብዮት በተካሔደበት ፥ እንደ ሀገረ ቻይና ባለው እንኳ ፥ ያ አይነቱ የመንፈስ ቅርስ ምንም ፍንክች ሳይል ፥ እንደሀገራችን እቴቴ በየሰዉ ቤት ጓዳ ውስጥ ተከብሮ ሲሠራበት መኖሩ ነው ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ቻይናውያንን ከምድረ ገጽ ላይ አጥዶ ማጥፋት የቻለው ደመኛ አብዮት ፥ እነዚህን ኀሊና ውስጥ ተቀብረው ያሉ የመንፈስ ቅርሶች ሊያጥባቸው ከቶ አልቻለም ።




እንደሚተረከው ከሆነ ፥ የነዚህ እምነታዊ እስተሳሰብ አመንጭ አባት ፥ ቡድሐ ነው ይባላል ። ይህ ሰው ሉዓላዊ ቅድስና የነበረው ለመሆኑ ፥ የእምነት መጻሕፍት ሁሉ መዝግበዋል ። ከቅድስናው ከፍተኛ ግዕርጋዊ ብቃት የተነሳ ፥ የዓለምን እንስሳትና አራዊት ሳይቀሩ የቅርብ ወዳጆቹ አድርጓቸው ነበር እየተባለ ይነገርለታል ። ትውልደ ሀገሩ ብሔረ ሕንደኬ እንደሆነና የሃይማኖት አባትነቱም ለሕንዳውያን እንድሆነ ታውቋል ። የኖረበትም ዘመን፥ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ( 566 - 480 ) እንደነበረ ይነገራል ። የቡድሒዝም ሃይማኖት መምራች እንደሆነና፥ የዚህም እምነት መሠረት የመከራና የሥቃይ ምንጭ ፥ ምኞትና ፍላጎት እንደሆነ አስመልክቶ ፥ ይህንንም መቋቋም የሚቻለው የመንፈስ ሰላም መፍጠር ሲቻል ብቻ እንደሆነ በመምከር ፥ ለሰዎች ስለትዕግሥት ልፅልና ያስተምራል ።

ቡድሐም ይህን ምሥጢረ ሕይወት ሲያስተምር ኖር የዚህ ዓለም መጥዕለ ዘመኑን ፈጽሞ በሞት ሊያልፍ ሲቃረብ በዓለም ላይ ተሠራጭተው ለሚገኙ እንስሳትና አራዊት ሁሉ

ያንዱም የምንጊዜም የመጨረሻ ስንብት ሊያደርግላቸው ጥሪ ያደርግላቸዋል ። የነበረው ቅድስና ፥ እንስሳትና አራዊት ሳይቀሩ ፥ ከፍተኛ አክብሮትና ፍቅር እስኪያሳድሩበት ድረስ በቅቶ እንደነበር ይነገርለታል ። በብዙ ዕልፍ አዕላፋት ከሚቆጠሩት እንስሳትና አራዊት ውስጥ ፥ ያንን የስንብት ጥሪውን አክብረው በጊዜው የተገኙት ፥ አስራ ሁለት ብቻ ነበሩ ይባላል ። ቡድሐም ፥ ጥሪውን አክብረው ለተገኙት እንስሳትና አራዊት ፥ ውለታዊ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ አንዳንድ አመት መድቦ ይሰይምላቸዋል ( ይሰጣቸዋል ) ።

በየአስራ ሁለት ዑደተ ዘመን ውስጥ ፥ አንድ አመት እንደሚደርሳቸውም አስልቶና ቀምሮ ደልድሎላቸዋል ። የኋላ ሊቃውንተ ቡድሐ ፥ ይህን ምድብ ጊዜ ፥ በወራት ፥ በሳምንታት ፥ በቀናት ፥ በሰዓታት ጭምር እየመነዘሩ ዘርዝረው ያቀርቡታል ። ( ይህን ዝርዝር ሐተታ በሚመለከት ፥ ስለ ሦስት በሐውርታት — እስያ ፥ አውሮፓ አፍሪካ — ነገረ መጠንቋላንና ፥ ባጠቃላይም እንደ ኮከብ ቆጠራ ( Horoscope ) እና ሌሎችም አካላት



ታላቁ ቡድሐ ፥ የዚህ ዓለም የሕላዌ ኮንትራቱን ፈጽሞ ሊያልፍ ሲል ፥ የዓለሙ ጠቅላላ እንስሳትና አራዊት በሙሉ መጥተው እንዲሰናበቱት ጥሪ ያደርጋል ። ያንን ታላቅ ጥሪ አክብረው ከመጡት ውስጥ ፥ [illegible] ይገኙበታል ። በጥሪው መሠረት አክብረው በመምጣታቸው ፥ ዋጋና መታሰቢያቸው ይሆን ዘንድ ፥ እንደደረሱበት ቅደም ተከተል አንዳንድ ዓመት ሰጥቷቸዋል ።

ስጋያትን በመርመር ፥ በሰዎች ላይ ሊደርሱ ስለሚችሉት ትንቢታዊ ሁኔታዎች የማወቅ ጉዳይ ፥ በንፅፅርና በዝርዝር የዘጋጀሁትን – "መድኃኒተ–ሥጋ" – የተባለ መጽሐፌን እንዲያነቡልኝ እጋብዛለሁ ።

ለአስራ ሁለቱ እንስሳትና አራዊት መታሰቢያ እንዲሆናቸው የተወደበው ጊዜ ፥ የቡድሐን የስን ብት ጥሪ አክብረው ሲመጡ ፥ እንደደረሱበት ጊዜ ቅደም ተከተል ነበር ። ለየተወደቡበትም አመት መጋቢያን እንዲሆኑ፥ በትረ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ። የዚህ የዘመናት መታሰቢያነት ቁም ነገር ፥ ለእንስሳቱ ከመወደቡ ላይ ሳይሆን ፥ በምድብ አመታቸው ውስጥ ፥ የሚወለዱ ሰዎች ሁሉ ፥ የየምድብ አመቱን እንስሳ ጠባይ የሚወርሱ ከመሆናቸው ምርጫ ላይ ነው ። እያንዳንዱ የሰው ልጅ ወደ እዚህ ምድራዊ ዓለም ሲመጣ ፥ በዘማናት ውስጥ ከሚገኙት አንደ ኛው አመት ፥ ወር ፥ ሣምንት ፥ ቀን ፥ ሰዓት ፥ ደቂቃ ሰከንድ ውስጥ እንደሆነ ይታወቃል ። ወደደም ጠላም ፥ ማንኛውም ሰው ፥ ከአስራ ሁለቱ እንስሳት መገብተ አመት



ውስጥ በአንደኛው ውቅት ይወለድና የዚያ የተወለደበትን አመት እንስሳ ፥ ሳይወድ በግድ ይወርሳል ማለት ነው ።

የእንስሳውን ባሕርይ መጫወሩ ፥ የግዴታና የእርባ ቀን ፅድሉ የሰጠው ፥ የሕይወት ጸዋው ነው ማለት ነው ። ይህ አይነቱ አመለካከት ፥ እንዳንድ ወናፍታን ሃይማኖት የነይሁዳን ፥ የነኢላመስን ፥ እንደፈያታዊ ዘፀጋምና የመሳሰሉትን ፥ "እምቅድመ ይፍጥር ፥ የእምር ግብር" ከሚለው አንቀጽ መሠረተ ሐሳብ ጋር እያቋጠሩ ከሚያቀርቡት ትችት ብዙም አይለይም ።

አብዛኛዎቹ የሩቅ ምሥራቅ ሕዝቦች ፥ ይህን ቡድሐዊ የፅምነት አስተሳሰብ ፥ ለዘመናት እንደህገራችን እቴቴ ሉዓላዊ ክብር በመስጠት ፥ በታላቅ እንክብካቤ በዓላቸው ውስጥ ደብቀው ፥ ሲገለገሉበት ኖረዋል ። ማን ምን እንደሆነም የሚያሳዩበትን ፥ ከታቢ ሕይወት ፥ እንደ አድዋው ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ የጥንቆላ መጽሐፍ ( ዓውደ ነገሥት ) አዘጋጅተው ፥ በምሥጢር ያሠራሉ ።

ተከታዩ ሠንጠረዥ፥ ያለንበትን ምዕት አመት

ብቻ በማጠከር ፥ የትውልዱን ልጆች ምንነት ለማሳየት ከ 1900 - 1995 ዓ ም ተመዝግቧል። ( አቆጣጠሩ በጎርጎርዮሳውያን ስለሆነ ፥ ከኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ጋር ያለውን ልዩነት ለመድፈን ፥ ስ ምንት አመታት ጨምሩበት ).

| እንስሳው | ዓመተ ምሕረቱ |
|---|---|
| ( 1 ) አይጥ | 1990-1912-1924-1936-1948 1960-1972-1984 |
| ( 2 ) በሬ | 1901-1913-1925-1937-1949 1961-1973-1985 |
| ( 3 ) ነብር | 1902-1914-1926-1938-1950 1962-1974-1986 |
| ( 4 ) ጥንቸል | 1903-1915-1927-1939-1951 1963-1975-1987 |
| ( 5 ) ዘንዶ | 1904-1916-1928-1940-1952 1964-1976-1988 |
| ( 6 ) እባብ | 1905-1917-1929-1941-1953 1965-1977-1989 |



| እንስሳው | ዓመተ ምሕረቱ |
|---|---|
| ( 7 ) ፈረስ | 1906-1918-1930-1942-1954 1966-1978-1990 |
| ( 8 ) በግ | 1907-1919-1931-1943-1955 1967-1979-1991 |
| ( 9 ) ጦጣ | 1908-1920-1932-1944-1956 1968-1980-1992 |
| ( 10 ) ዶሮ | 1909-1921-1933-1945-1957 1969-1981-1993 |
| ( 11 ) ውሻ | -1910-1922-1834-1946-1958 1970-1982-1994 |
| ( 12 ) ዓሳማ | 1911-1923-1935-1947-1959 |

ከላይ እንደተጠቀሰው ፥ የዚህ መንጠሪቹ ቁም ነገር፥ የእንስሳቱን ስው‐ዓመታት ማሳየቱ ሳይሆን ፥ እያንዳንዱ ሰው እንደተወለደበት አመት እንስሳ ጠባይና ባሕርይ ፥ ሕይወቱን ሙሉ ሲያንፀባርቅ ይኖራል ፥ የሚለው ወርሐ‐ሕይወት ነው ። ማለትም ፥ በድመት አመት የተወለደ

የድመትን ባሕርይ እያስተናገደ ፥ ፅድሟን ሙሉ እንደሚናገርና እንዲሁም በሌሎቹ እንስሳትና አራዊት አመታት የተወለደ ሰው ፥ እንደ አመተ-ልደቱ ፥ ያሳማ ፥ የአይጥ የበሬ ፥ የነብር ወዘተ ጠባይና ባሕርይ ይንፀባርቅበታል

በተለይም ፥ የአስራ ሁለት ዑደተ-አመት አድርገው በየመገብተ-አመታቸው ተፈራርቀው ሲደርሱ ፥ እያንዳንዱ ግለ-ሰብ ፥«ይህ የኔ አመት ነው ፥ ሁሉ ነገር ይመረቅንልኛል ፥ በመከራዬ ሁሉ ይቀናኛል !»የሚለው ይህንኑ በተለየ አመት የተወለደ መሆኑን በማገናዘብ ነው ።

የዚህ ነባር አስተሳሰባዊ ባሕል ባለቤቶች የሆኑት የሩቅ ምሥራቅ ሕዝቦች ፥ ወጥመን አመት ሁሉ ፥ አስቀድመው ምንነቱን የሚተረጉሙት ፥ በአመቱ እንስሳትና አራዊት መስተዋትነት ነው ።«በዘንዶ አመት ጦርነት ፥ በፋም አመት ሰላም ፥ በአሳማ አመት ጥጋብ ...»ይሆናል ብለው የሚተነብዩትም ፥ ከዚሁ በመነሳት ነው ። እንዲህ እንዲህ ያለውን ያባቶች ቅርስ ፥ የአብዮት ዘመን ውልድ የሆነው ተራማጅ ቻይናዊ ፥ በጥቅሉ ተረት ነው ይለዋል ።



እንዳንዱም ፥ በአደባባይ ያውጋዘው እንጅ ፥ በየግላው ያመልክበታል ። የሞን-ጃሎፍ ተግባር ፥ ግመፋስት ግስተዋወቅ ፥ እየጠቀመም ማሳየት እንጅ ፥ በግለ ሰቦች ምርጫ ውስጥ ገብቶ ፥«እንዲህ አድርጉ !»እያለ ፥ እንደገረረበት ባፋምባራስ ወይም ኮማንደር ፥ ትዕዛዝ የሚያዝ ሰፋይደለና ያም አይነት ሥልጣን ስለሌለው ፥ የሞን ጃሎፍ ምርታዊ ድግሱን እንደየምርጫችሁ እንድትመገቡለት ያቀርባል ። ስለሆነም ፥ ለየራሳችሁ ምርጫ ቀርቧል ።

ይህ የሩቅ ምሥራቅ የሕይወት አመለካከት ፥ በሰዎች ሕይወታዊ ኪደት ውስጥ«ምን አይነት ትርጉምና ግንፋል አለው? ምንስ ፋይዳ ይሰጣል?»ለሚሉ ጠያቂዎች ፥ እንዳንድ በገቢር የተፈተኑ ማስረጃዎችን መጠቃቀስ ይቻላል ።

- በአመተ-ልደት ተፅዕና የሚያምኑ በመሆናቸው በነሳማ አመት የተወለደችን ከረፋ ፥ በውሻ አመት ለተወለደ ነረምሳ ፥ ቶማ ትቀራለች እንጅ ፥ ቢሞቱ አይድሩም ። ይህን ሳያገናዝቡ በጭፍን ድፍረት የፋሩ እንደሆነ ፥ ውጤቱ የሚከተለው አይነት ነው ።



በውሻ ዓመት የተወለደን-ከባለ አሳማው ዓመት ጋር ቢያጋቡ ውጤቱ እንደምፀሉ ነው - የምርኅት ጋብቻ ሲነፀብ ደንቡ!



- በተወሳሳይ ምክንያት-ወንምኤም ፥ የድመት እናት ውሻ ከረዲትን ፥ ለአይጥ እናት ነረምሳ ፥ በኑሮ ጓደኝነት አይድሩም ። ያ አይነት ጋብቻ ቢፈፀም ግን ፥ባል የሚሆነው አባወራ ፥ ሚስቱን አቅፎ ከመሳም ይልቅ ወምድዶ መጊጠጥ እንደሚቀናው የታወቀ ነው ።

- ሁለቱም ተጋቢዎች ደግሞ ፥ የመሰል እናት-ድመት ውልዶች መሆናቸው ከታወቀ ፥ በባልና ሚስትነት እንዲጋቡ አያደርጉም ። ዋናውም ምክንያት ፥ የጋብቻው ውጤት ፥ የሚከተለውን አይነት አደገኛ ትንቅንቅ እንደሚፈጥር አስቀድመው ስለሚያውቁ ነው ። ሌላው ደግሞ ፥ አባወራው በድመት ዘመን የተወለደ ሆኖ ፥ ሚስቱ የአይጥ ዘመን ውልድ ብትሆን ፥ ትዳራቸው ምን አይነት መንቻካ እንደሚሆን አንባቢ ሊያውቀው ይችላል ።

- የእናት ትርጓሜያዊ ሁኔታ ፥ ከሰዎች ሕይወታዊ ዕድል መሳኝነት አልፎ ፥ በፀሀዮችና በሌሎችም በቁንቶችም ላይ ሳይቀር ይጠቀመበታል ። ከተቆረጠ በኋላ ፥ እንደገና እቶጥቁጦ የግደግ ተፈጥሮአዊ ክሒል ያለውን ተክ



ባሕርየ እንስሳው ተመሳስሎ – ጠባያቸውም በሙሉ ፤
እግዚቶሬኝ ከሆነ – አመልና አመሉ ፤
ከንቱ ነው መከራቸው – ምን ጊዜም አይሰግው ፤
ቢጋቡም መናቢት ነው – በትግራቸውም አይዋዋው !

# አንደርድሮ አድራሽ



ል ፤ ለዘለዓለም መከና እንዳይቀር ፤ አብቃይ የሆነ የእንስሳ አመት ካልመጣ በስተቀር ፤ መጥረቢያቸው ስለሰባና፤ መጋዛቸውም ስለቀላ ብቻ ፤ በዘፈቀደ ገስግሰውና ባሰኛቸውም ጊዜም ተነስተው አይቆርጡም ። ለቆረጣ አመች የሆነ ጊዜም እንዳለ ያምናሉ ።

የሩቅ ምሥራቃውያን ሕዝቦች የዘመን ፅንሰ ሐሳብ እጅግ ስር የሰደደና የእምነትም ያህል ልፅልና የተሰጠው ነው ። ይህም በመሆኑ ይመስላል ፤ አብዛኛው ሕዝብ ፤ ልጆቹን ሲወልድ ፤ አስቀድሞ ሐራ ዘመኑን አሰልቶና የአመተ እንስሳውን ባሕርይ አጥንቶ ነው ። ዝርዝር ሐተታ ውስጥ አልገባም እንጅ ፤ በየትኛው አመተ–እንስሳ ሕፃን ቢፀነስና ተከልም ቢቆረጥ እንደሚሠምር መጠቆም ይቻል ነበር ። ትዳር የሚመሠርቱትም ጥምር ጉብሎች ፤ የየትኛው አመት ተሬምሳ ፤ ለየትኛይቱ አመት ኮረዳት እንደሚስማማ አካቶ ማሳየትም ይቻል ነበር ። ይህን ጥበባዊ ምርኝተ–እስተኝምር ( Combination ) ከነዝርዝር ሙሉዓው ማቅረብም ይቻል ነበር ። ሌላው ቀርቶ ፤ በዚህ የዘመን ቅግሬያዊ ጥ

ፀብ የተራቀቁ ሊቃውንት ፥ ዕለተ ሞታቸውን ጭምር አስልተ ው በቅድሚያ እንደሚያውቁ ( ትርፉ ጭንቀት ነው እንጅ ) ይነገራል ።

እንዲህ እንዲህ ያለውን የዘመናት ፍካሬ ሕይ ወት በምርጫት የማያውቀው ያገሬ ሕዝብ ፥ በገረረበት ወቅ ት ብቻ ጭን እያራስ የሚፈለፍለው ልጅ ፥ አብዛኛው ምድራ ዊ ሕይወቱ ሳይቀናው ፥ ደስ ሳይለው ኖሮ ፥ ደስ እንዳሳ ለው ይሞታል ። በባሕርይ የማይጣጣሙ የተለያዩ አመታት ው ልዶችን አጋብቶ ፥ ትዳራቸው በሳኒታው ምንቅርቅሩ የሚወጣ ው ። የደከመበትን የተከለ ደንና ጫካ ፥ ባሰኘው ዕለት ወድሞ ፥ ያለማቋረጥ የሚደርቅበትም ፥ ይህን መሰል ጥበብ ካለመረዳቱ ይመስላል ።

የመተርጉመ-ዘመን ሊቃውንት ፥ በሁለት ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ። እነዚህም ፥ የቅድመ ሞት ሕይወ ትና በድኅረ ሞት ወቅት ስለሚከሠተው የዳግም ልደት ጉዳይ ናቸው ። እንብባችሁልኝ ከሆነ ፥ «ደርዘን ልጆች ወልዳ» የሚለው ግጥሜ ፥ ስለቅድመ ሞት ሕይወት ምንነት የሚተርክ



ነው ። አጠቃላይ ይዘቱም ፥ የማንኛውም ሰው ቅድመ ሞታዊ ሕይወት ፥ በሚያንፀባርቀው ባሕርይ አንፃር ፥ የተወለደበት አመት አይነት ወሳኝ እንደሆነ ማስተማሩ ነው እንዳንድ የሀገራችን ቧልተኞች ሲሳደቡ ፥ «ይህ የጠጅ ፅንስ ! ይቺ የካቲካላ ፅንስ ! ይህ የሰንበት ፅንስ ! ...» እንደሚሉት ያለ ነው ። በዘመኑም ትይታ አንፃር ፥ «ዘመነ ሉቃስን ፥ ሉቃሳም አመት ነው ። ደዌ ይፀናወትበታል ፥ የተወለደው ሁሉ ፋፋ እንዳሳደገው ሕፃን ፋንቋሶ ይሆናል ዘመነ ዮሐንስ ደግሞ ፥ ጦርነት የሚከፋበት አመት ነው ። ሞት በሽበሽ ይሆናል ። ጠብና ንትርክ ይበዛበታል ።» እንደሚሉት ያለ ነው ። ዘመናትን ለመወገብ በየአራት አመቱ እየተፈራረቁ የሚመጡትን ወንጌላውያን አስመልክተውም የተለያየ መተርጉመ ዘመን እንደሰጧቸው እናውቃለን ። ማስታወስም ቢያስፈልግ ፥

( 1 ) ዘመነ ዮሐንስ – ( ዘንጦር – አዋራኛው )
( 2 ) ዘመነ ማርቆስ – ( ዘአንበሳ – አንበሳኛው )
( 3 ) ዘመነ ማቴዎስ – ( ዘሰብዕ – ሰውኛው )

( 4 ) ዘመነ ሉቃስ – ( ዘላህም – ላምኛው )

ለወንጌላውያኑ ተምሳሌ መግለጫ ሆነው የቀረቡትን ፍጡራን ጠጋ ብለን የመረመርን እንደሆነ ፣ ምናልባት ከሩቅ ምሥራቅያኑ ምሥጢረ እንስሳት ጎራ ጎትቶ ይከተን ይሆናል ።የተለዩበት ነጥብ ቢኖር ፣ ቁጥራቸው አራት መሆኑና ከፍጡራኑም አንዱ ፣ የሀገራችን አመታዊ እሳቤ አሞራና ሰው መጨመሩ ነው ። ብዙ ወገኖቻችንም ፣ ከወንጌላውያኑ ይልቅ ፣ በተቀጥላ ካስገቧቸው ፍጡራን ጋር በማያያዝ ፣ የየአመቱን ምንነት ሲተረጉሙበት ተገኝተዋል። ይህን ጉዳይ እንደብዙቱ ለሌላ አጥኚ ብተወው ይሻላል ።

የነፍስን ሕያዊነትና ትድግና በማስመልከት ፣ አንድ ነጥብ ማንሳት ይቻላል ። በኛም ሆነ በምሥራቁ አስተሳሰብ ፣ ስለነፍስ ዘለዓለማዊነት ፣ የጋራና አንዳች የሆነ መሰል አቋም ይታያል ። በድኅረ ሞት ባለው ሕይወት ወቅት ፣ ስለነፍስ አኗኗር ሁኔታን በሚመለከት ግን ልዩነቶች ይታይባቸዋል ። የኛው "ኪወ ይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ" በሚለው ይካተትና ምርጫውም ገሐነም ወይም መንግሥተ



ሰማያት ይሆናል ። አሁንም "እንደሥራው ዋጋውን ያገኛል" በሚለው ነጥብ ላይ ተመሳስለው ይገኛሉ። የሚያመሳስሉት ግን በአፈፃፀም ሁኔታ ላይ ነው ። እንደ ምሥራቃውያኑ አስተሳሰብ ከሆነ ፣ የነፍስ ድኅረ ሞታዊ በሕይወት አኗኗር እጅግ የተለየ መልክ አለው ። ትንሣኤ ሳይሆን ዳግም ልደት ( Reincarnation ) ነው ። የ ሲኦል ወይም የገነት ፣ የ ገሐነም ወይም የ መንግሥተ ሰማያት ጉዳይ አይደለም ።

እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ፣ ሕያዊት ነፍስ የቅድመ ሞት ሕይወታዊ ኮንትራቷን ስትጨርስ ፣ በራሷ ምንም አይነት ውሳኔ ሳታደርግ ፣ እንደገና በአዲስ ሰው ወይም ሌላ ፍጡር አካል ጋር ተዋሕዳ ፣ እንደ አዲስ ሕፃን እምቦሳ ፣ ውርንጭላ ፣ ቡችላ ፣ ጫጩት ፣ ቀጀ . . . ወዘተ ሆና ትወለዳለች ። ማለትም ፣ ከሞተው አካሏ ላይ ፣ የማትሞተው ነፍስ ፣ በምትለይበት ጊዜ ፣ በዚያው ወቅት የቀድሞ ምግባሯ በወሰነላት ዕድል መሠረት ፣ የድኅረ ሞት

ፋገግሮ ሕይወቷን ፥ በአዲስ መልክ ትጀምራለች ። ሕያዊት ነፍስ በፋገም ልደቷ ተሐድሳ ብቅ የምትልበት ጥበባዊ ምሥጢር እጅግ አስደናቂ በመሆኑ ፥ እኔንም ጭምር ከማስደ ደንገጥ አልፎ በጣም አሳስቦኛል ።

«ሕቀ አጎፀፅኮ እመፋእክቲክ»( ከባለ ግርማ ሞገሳም መላእክቶችህ ትንሽ አሳንሰከው ) ተብሎ የተነገረለት ፥ ታላቅና ክቡር የነበረ ሰው ፥ በፋገም ልደቱ ወቅት ፥የተራ አሀያ ውርንጭላ ልጅ ሆኖ ሲወለድ ከማየት የበለጠ ፥ ሌላ የሚያስደንቅ ትንግርት አለ ትላላችሁን? ከፀርፅ ጥንታውያን ሊቃውንት አንዱ የሆነው አርስጣጣሊስ ( Aristotle 384 - 322 B C ) በዘመኑ ፅለታት በአንደኛው ቀን ፥ የጎረቤቱ አንድ ሕፃን ፥ አንዲት አሮጊት ድምት ይዞ ሲደበድብ ያገኘና «ለምን ትቀጠቅጣታለህ ከሴቶች እያቶችህ ውስጥ ፥ አንደኛዋ ልትሆን ትችላለች» ቢለው ፥ ልጁ ደንገጦ ወዲያው እቅፎ አባብሏታል ይባላል። ይህ መሰሉ ታሪክ ፥ የምሥራታውያንን ፋገም ልደት ሐቅነት



የሚደገፍ ይመስላል ። እንደነዚህ በመሳሰሉ ምክንያቶች የተነሳ ፥ የፋገም ልደትን ምሥጢር ፥ አደባብሰው የሚያልፉት አይሆንም ።

የቀለምን ተግሬ እንዲህ እንዲህ ያሉ ትንግርታውያን ታሪክ ነክ ቁም ነገሮች ፥ ቀልቡን ከመስቀል አልፈው ያስደነግጡታል ። በልዩ ትንግርትነታቸውም ፥ ኅሊናውን ያነሆሩታል ። የቀለም ተግሬው ብፅረኛ ከሆነም ይጽፍበታል ።

የሌላን ሕዝብ ባሕል ለማጥናት የተሠማራ ደቀ መዝሙርም ከሆነ ፥ ፀሪቦን ( Inspiration ) ይፈጥርለታል ። የሀን መሰሉ ልዩና እንግዳ አስተሳሰብ ፥ ጣዕመ ፅሑት ስለሚያመርትለት ፥ ፈጥኖ ለመገናኙ ለማስተዋወቅ እንዲጣደፍ ይገፋፋዋል ። «ስካራም አህያ?» የሚለው የዚህ እትም ሁለተኛው ግጥም ፥ የዚህ አይነቱ አጋጣሚ ግፊት ውጤት ነው ። በእትሙ ውስጥ ሠፍረው ከሚገኙት ግጥሞች ሁሉ ፥ ልዩና እንግዳ የሆነ ሐሳብ የያዘ በመሆኑም ፥ ከሌሎቹ የተለየ ፥ መለስተኛ ትንተና አስፈልጓታል ።

የዚህ ግጥም ይዘት የሚያተኩረው ፥ ከድኅረ ሞት ቀጥሎ ስለሚኖረው የሕይወት አይነት ነው ። ሰዎች ሁሉ እንደባሕርይ ዝንባሌያቸው ፥ በምድራዊ ሕይወታቸው ወቅት የተለያዩ ምግባራት እንደሚፈጽሙ የታወቀ ነው ። ባለናዜራ ስሜቱ ሰው ፥ ዘማዊነት ያበዛል ። ቀሚስ ለብሳ ያያትን ሔዋናዊት ሁሉ ፥ የለጉሜ ውሻ ይመስል ዘልዬ ልንከስሽ ይላል ። እፍታሬ ወጠጥ የሆነው ደግሞ ፥ ያገኘውን እምቡላ ሁሉ እየጨለጠ ፥ ሰካራም ይሆናል ። የጅ ልግድ ያለበት ሌላው ደግሞ ፥ ሞጭላፋ ሌባ ነው ። ባታላይነት ጥበብ የሠለጠነው ውሽታም አባይ ደግሞ ፥ የወጣለት ፖለቲከኛ ይሆናል ። የቀረውም እንዲሁ ፥ እንደብልቱ ነው ።

እነዚህ የቅድመ ሞት ሕይወት ሰብዓዊ ባሕርያት ሁሉ ፥ ነባር የባሕርይ ነፀብራቅ ሆነው ፥ ከድኅረ ሞት ቀጥሎ የሚወጣውን አዲስ ሕይወታዊ ምንነት ይፈትላሉ ይነድፋሉ ፥ ያላውራሉም ። ማለትም ፥ በቅድመ ሞት ወቅት በየግለ ሰቡ ይፈፀሙ የነበሩ ባሕርያዊ ምግባራት ፥ በጎም ይሁን ዕኩይ ፥ ገርም ይሁን ጨካኝ ፥ ቸርም ይሁን ቀንቋ



ና ፥ ለጋምም ይሁን ጨቅ ፥ እንደየአይነታቸው ፥ የተከ ታዩን የድኅረ ሞት ሕይወት ሕልውናዊ ምንነት ይወስናሉ ። ይቅድመ ሞት ሕይወታዊ ምግባራት ባሕርያዊ ዝንባሌዎች ለተከታዩ የድኅረ ሞት ሕይወት መታወቂያ ጠባሳዎች ናቸው ማለት ነው ። የሰው ልጅ በሕይወት በነበረበት ወቅት የሚ ፈጽማቸው ምግባራት ፥ ከሞተ በኋላ በሚኖረው ዳግም ልደት ሕይወቱ ላይ ፥ የማይፋቁ ማኅተሞች ሆነው ይገዝፋሉ ። የሃይማኖት አባቶች ጥንታዊ ትምህርት ፥ "ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ" እንደሚሉት አይነት ፥ የዳግም ኩነቶች በሙሉ የቀዳማይ ሕይወት ቀጥተኛ ውጤቶች ናቸው ማለት ነው። በዳግም ልደት የሩቅ ምሥራቅ ሊታወንት ግንዛቤ መሠረት ፥ ሰዎች እንደቀዳማይ ሕይወታዊ ምግባራቸው ፥ ከሞታቸው በኋ ላ እንደገና በሚወለዱበት ሕይወት ውስጥ ፥ የሥራቸውን ዋጋ እንደሚከፈሉበት ፥ አለአንዳች መጠራጠር ያስተምራሉ።

ብዙ ጊዜ የሚደንቀኝ ፥ አንድ ያሀዮች ትንግርት ፥ አዘውትሮ ያጋጥመኝ ነበር ። ይኸውም ድንቅ ድርጊት የ"እንወራረድ አሀያ እንሬድ !" ዜቅ አይደለም ።

ዘርን አህዮች ካሳውት ቦታ አንፍንሬው ሔደው ፥ ለወንደባለያቸው የሚወርዉት ሥፍራ ፥ ሁልጊዜ እምቡሳና አወድ ከሚፈሰሱበት ቦታ ላይ ነው ። ከወንደባለላቸውም አስቀድመው ፥ የዚያ ሥፍራ ተስማሚነቱን ፥ በዚያ ሰፋፊ አፍንጫቸው በማሽተት ይታኛሉ ። የጠጅና የጠላ ማንገሻ የሆነው ጌሾ የፈሰሰበት ቦታ ከሆነ ፥ ለወንደባለያነቱ ምቹነቱን ለማረጋገጥ ይወስላል ፥ በደስታ ብዛት እያንባረቁ ያናፋሉ ።
ያን ወሰሉ ያህዮች ድርጊት ሁልጊዜ ይደንቀኝ ነበር ። ትርጓሜያዊ ምንነቱ ግልጽ የሆነልኝ ግን ፥ ከቻይና ቀይታዬ ስለ ዳግም ልደታቸው ታሪክ ከተረዳሁ በኋላ ነው ። እነዚያ የቡድሐ ትምህርቶች ፥ የባሕረ ሐሳብ ያህል ሰፊና ጥልቅ ናቸው ።

“በቅድመ ሞት ሕይወቱ ወቅት ፥ ሲጠጣና ሲጠነብዝ የነበረ ሰካራም ሰው ሁሉ ፥በድኅረ ሞቱ ሕይወት ዘመን አህያ ሆኖ ተወልዶ ፥ አህያ ሆኖ ኖሮ ፥ አህያ እንደሆነ ይሞታል ” ይላል ምሥራቃዊው መጽሐፍ ። ለካስ ፥ በየአምቡላው ላይ የጌሾ ጠረን እያሸተተ እንዲያ ሲያናፉ ያየሁት



ያገሬ አህያ ሁሉ ፥ ያለበቂ ምክንያት አልነበረም ። ያ ምድሬ አህያ ሁሉ ፥ ለካስ በጥንት ፍጥረቱ ፥ ሰካራም ሰው የነበረ ኖሯል ። የዳግም ልደት ሁኔታን የሚዘረዝሩ ቡድሐውያን መጻሕፍት ሁሉ ፥ በቀድሞ ምግባር አስገዳጅነት ጥንተ ተፈጥሮአቸውን ለውጠው ፥ ምን ምን ሆነው እንደሚወለዱ ሲዘረዝር ፥

| በጥንተ ተፈጥሮው | | በዳግም ልደቱ |
|---|---|---|
| ሰው የነበረና | ሰካራም በመሆኑ | አህያ ይሆናል |
|  | |  |
| ሰው የነበረና | ዘማዊ በመሆኑ | ውሻ ይሆናል |
|  | |  |
| ሰው የነበረና | ቀባጣሪ በመሆኑ | በቀቀን ይሆናል |
|  | |  |

| | | |
|---|---|---|
| ሰው የነበረና | በለቲከኛ በመሆኑ | ጦጣ ይሆናል |





| | | |
|---|---|---|
| ሰው የነበረና | ቃል ያዛባ በመሆኑ | ዕንቁራሪት ይሆናል |





አድኅ በለአም ( የበለአም አህያ ) ፣ በሰው አንደበት ተናገረች የሚባለ ታሪክና የሩቅ ምሥራቃውያን የዳግም ልደት ፍልስፍና ፣ እርስ በርሱ የተጋባ መሰላል ። የበለአም አህያ ፣ በቅድመ ሕይወቱ ሰካራም የነበረ ሰው ይሆን?

እነዚህን የዳግም ልደት ተፈጥሮአዊ የለውጥ መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ፣ እያንዳንዱ ሰው በፈፀመው ምግባራዊ ውጤት እንደገር ፣ ከሞተ በኋላ ምን ሆኖ ከማትዋ ተው ነፍሱ ጋር እንደገና እንደሚወለድ ፣ አስቀድሞ መገምገም ሆነ ማወቅ ይቻላል ። ይህንንና ሌላም ዝርዝ ር ስልነክ የሆኑ ጉዳዮች ማወቅ ለሚፈልጉ አንባቢዎች ፣



የምስቁን ታላላቅ በሐውርት ባሕላዊ የምንቆላ ፣ የኮከብ ቆጠራ ( Astrology ) የአስማት ድግምት ፣ የምትሐ ት (Magic) የምስሐብ መናፍስት (Spiritualism) የተለያዩ መድኃኒቶች ... ወዘተ በቁምነገርነት ደረጃቸው ፣ አንዱን ከሌላው እያነፃፀረ የሚያቀርበውን መጽሐፌን ( መ ድኃኒተ ሥጋ ) እንዲያነቡ እጋብዛለሁ ። በዚያም መጽሐፍ አማካይነት ፣ በነዚያ መሰል ጉዳዮች ላይ ፣ ዕውቀታዊ ጥ ማት ያለበትን ሁሉ ፣ ሊያረካ እንደሚችል አምናለሁ ።

የብዕረኛ ተቀዳሚ ተግባሩ ማስተማር እንደ መሆኑ ሁሉ ፣ የማስተማር ጥበብ ደግሞ ፣ በአፈፃፀም ባሕርዩ ፣ እርቃኑን አለአንዳች ማጫፊያ ደረቅ ሆኖ ቢቀርብ ፣ ከቸሮ ና ለዛ ያጣ ይሆንና ፣ ተማሪውን ሳይጥመውና ሳይቀበለው ይችላል ። ስለዚህም ፣ ተማሪው ቀደም ሲል ካካበተው የዕ ውቀት ቅርስ ጋር አስታኮ ፣ መምህሩ በአዲስነት ሊወግብ የደገሰውን ምግበ ትምህርት ፣ በምሳሌያዊ ቅመሞች አጣፍጦና ገጽታውንም ቀባብቶና ኳኩሎ ማቅረብ ይኖርበታል።

ከላይ እንደተዘረዘረው ሁሉ ፣ አንድ ሰው

ወደዚህ ዓለም ለመኖር ከመጣች እናቱ ማኅፀን ሲወለድ ፥የ ተወለደበትን ቀንም ሆነ አመት መቀየር አይቻልም ። እንደ ምሥራቃውያኑ አባባል ፥ የሕይወት ዕድሉም በዚያው ቀንና አመት ማኅተምነት ተቸንክሯል ። ሆኖም ፥ የሰው ልጅ በተ ፈጥሮው ብልህና አዋቂ ስለሆነ ፥ የአርባ ቀን ዕድሉን ማ ሻሻል የሚችልበት ክሒል አለው ። እንኳንስ ብሩህ ሰው ቀ ርቶ ፥ በሥርዓት ከተያዙ ፥ የእንስሳትም ጠባያቸውንም ሆነ ባሕርያቸውን ማሻሻል ይቻላል ። በርግጥም የሰው ልጅ የተወለደበት አመት ባሕርየ እንስሳ አንፀባራቂ መሆኑ ከተረጋገጠ ፥ የዚያን እንስሳ ባሕርይና ጠባይ አጥንቶ፥ መርሐ ሕይወቱን በዚያው አይነት ብቻ አስተካክሎ መምራት ብቻ ሳይሆን ፥ በሚያመችና በሚያመረታ አይነት አሻሽሎ ማ ስተካከልም ይችላል ። ኑሮ በዘዴም ይሏል ይኸው ነው ። ይህን የቅድመ ሞት ሕይወት ዝግጅት የሚጠቁመው ግጥም ፥ “ደርዘን ልጆች ወልዳ”የሚለው ሲሆን ፥“ስካራም አህያ”የሚ ለው ግጥም ደግሞ ፥ ከድኅረ ሞት ቀጥሎ ለሚመጣው ሕይወት መዘጋጃ የሚሆኑ ቁም ነገሮችን በምሳሌያዊ አቀራረብ ይጠቁ



ማል ። ማለትም ፥ በቅድመ ሞት ሕይወቱ ወቅት ፥ ስካራም ሆኖ የሚኖር ሰው ፥ በድኅረ ሞት የዳግም ልደታዊ ሕይወቱ አህያ ይሆናል ከተባለ ፥ ዛሬ በሕይወት እያለ ፥ ስካራም እንዳይሆን ፥“አትጠጣ ወይም ብትጠጣም እስክትሰክር ድረስ ሳይሆን መጥነህ ጠጣ”ብሎ ማስተማሩ ፥ አህያ ሆኖ እያኖሩ ከሚኖር ያድነዋል ማለት ነው ። ከዚህስ የበለጠ የብዕር ቁም ነገር ምን ሊኖር ይችላል?

በነባር ባሕላችን ትምህርታዊ ቅርስ መሠረት ሞራላዊ የሆነው የግብረ ገብ ትምህርት ፥“ይህን ዕኩይ ነገር አታድርግ ! ይህን ክፉ ድርጊት አትፈጽም ! ይህን ከፈጸምክ ግን ፥ በነፍስህ ትቀጣለህ ፥ ትኮነናለህ !» እያለ ግልጽና ርቱዕ በሆነ መንገድ ሲያስተምርና እሪ ሲል ም ኖሯል ። ይህ ግጥምም ፥ ይህንኑ የሞራል ሠራዊት እሪታ ፥ ኅሊናን አስተካክሎ ሊገዋ በሚችል ልዩ ዘዴ «አ ህያ መሆን ትፈልጋለህን”እያለ ያቀርባል ።

አንድ ሰው ስካራም ቢሆን ፥ በግል ምርጫው እንጂ፥ በተፈጥሮ ድንጋጌ በግድ የሚያስገድድ ፥ ከበስተጓ

ላው የተማነበት ሌላ ገሬ ኃይል ኖሮበት አይደለም ።
በርግጥም ፥«በኑሮ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች አስገድደውኝ
ነው የምጠጣው»የሚል ሰበብ ቢሰጥም ፥ ችግሮቹን በመጠጥ
ኃይል ለመቋቋም ከመሞከር ይልቅ ፥ ሌላ የተሻለ መቆጣጠሪ
ያ ለመፍጠር መዘየድ እንደሚገባው ይጠቁማል ። በኢትዮጵያ
ዊው ነባር ባሕል አንፃር ፥ ከሞት በኋላ በመጥፎ ምግባር
ቁጋንት የሚነገረው የሲያልና የገሐነም ነበልባለ እሳት እ
ንጅ ፥ እህያ የመሆኑ ምሥጢር ከቶ አይታወቅም ። ይህን
ሲሰማ ግን ፥ እንደሚያስደነግጠው አውቃለሁ ። የዚህ አይ
ነቱም ትምህርት ፅሬትነት ፥ ከማስደንገጡ ላይ ነው ። ም
ናልባትም አስፈራርቶት ፥ ከፅኩይ ምግባሩ ቶሎ ይመለሰውና
ለንስሐ ሞት ያበቃውም ይሆናል ። ስለዚህም ፥ ሰካራም እ
ህያ የሚለው ግጥም ፥ ኢርቱዕ በሆነ መንገድ ፥«እህያ መ
ሆን ከፈለግህ ፥ ቀምቃሚ ጠጪ ሁን»እያለ ያስጠነቅቃል ።
ጎሊና ያለው ለሚባልለት የሰው ልጅ ፥ ከዚህ የተሻለ
አስደንጋጭ ማስጠንቀቂያ ፥ ከየት ሊመጣለት ነው ! !

ለዚህኛው እትሜ ፥ አጠቃላይ ርዕስ አድርጌ ያ



ቀረብኩት –«ቀርጠሃት ጣልልኝ»– የሚለውን ነው ። የርዕ
ሱ ግጥግጦ ይዘት ፥ በግብር ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ ላ
ይ የበረቀ ሥያሜ ነው ። ደገኛው ማኅበረ ሰባችን ፥ ያን
ድን እምባ ልጆች ሁሉም ቤተሰብ እንደራሱ ቆጥሮ ፥ በጋራ
ተንከባክቦና ተቆጣጥሮ ፥ ያሳድግ እንደነበር እንዘነጋም።
ሁሉ ልጅ ፥ የሁሉ አባትና እናት ልጅ እንደነበረ የሚታወቅ
ም ነው ። የመንደራችን ልጆች ፥ እንደወላጅ አባቶቻችን፥
አክብረን የምንወካባቸው አንድ አዛውንት ነበሩ ። እኚህም
አባት ፥ በጀግንነታቸው የታወቁ ፥ በተለይም በማይጨው ጉ
ራ ላይ ፥ ከጠላያን ወራሪ ጋረ የተፋጠጡ ታላቅ አርበኛ
ነበሩ ። ሁላችንም የሠፈሩ ልጆች «አባባ» ስለእምንላቸው
መጠሪያ የተፀውዖ ስማቸውን እንኳ ፥ በውል አናውቀውም ።

የኚህን ታላቅ አባት ታሪክ ፥ ለተባለው ግ
ጥም ይዘታዊ ግቀንቀኛ ያደረግሁበት ምክንያት፥ አንድ ልዩ
የሆነ ግላዊ ታሪክ ስላላቸው ነው ። እኚህ ሰው ፥ በዘመ
ናቸው ፥ የአንድ ክፍለ ጦር አዛዥና አበጋዝ መኮንን ነበ
ሩ ። በሐቅ ምንነት የሚያምኑ አባት ስለነበሩ ፥ ከበላይ

አለቆቻቸው ጋር ስላልተግባቡ ፥ ለኑሮ ማርጠቢያ የሆነ ጥሪት ፥ ከዘውዱ መንግሥት አላገኙም ። ስለሆነም ኑሮአቸው እንደገረረ ጀንፏ ደረቅ ነበር ። ያም ሆኖ ግን የሰው ፍቅርና አክብሮት አልጎደለባቸውም ። ሁልጊዜም ደስተኛ ነበሩ ።

አይምሬ ጀግና ስለነበሩ ፥ ዘምተው ያልተዋጉበት የዘመናቸው ጦርነቶች አይገኙም ። በተለይ ፥ ተጋዳይ አርበኝነታቸውን ያስመሰከሩበት ጦርነት ግን ፥ የማይጨው ዘመቻ ነበር ። እያቆቻቸው ፥ በአላጥ ላይ የሠሩትን ጀብዱ ሲተርኩ ፥ ሰሚውን ሁሉ ጊ አድርገው ቀልቡን ያግባሉ ። ለትረካ ችሎታቸው እንከን አይወጣለትም ።

በዚያ የማይጨው ነዲድ የጦርነት አውድማ ላይ በሳቸው አበጋዝነት ይመራ የነበረው ሠራዊት ፥ የየበኩሉን መሥዋዕትነት ሲከፍል ፥ ከጠላት በተተኮሰች ጥይት ፥ እሳቸውንም ፥ የቀኝ እጅ አውራ ጣታቸውን ጣፍ አቁስላ ነበር ። ያቺም የቆሰለች ጣት ዘመናቸውን ሙሉ እየቆጠቆጠች ስትጠዘጥዛቸው ኖራለች ። በጦርነቱ ወቅትም ፥ ለብዙዎች



ታጋዮች እንደደረሰው የከፋ ዕድል ጀዋ ፥ እሳቸውም ወደ ጦርነቱ ማብቂያ ላይ ተማርከው ፥ በእጂናፉ ኖረዋል ።

ያቺ በጥይት የቆሰለች ያውራ ጣት ጣፍ ቁስል በየሔዱበት ሥፍራ ሁሉ አብራቸው ኖራለች ።“ያርበኝነት መታሰቢያ ሜዳልያዬ ናት”እያሉ ያቅራሩባታል ። በተማረኩ ወቅት ፥ በሕክምና ሰም ፥ ቁስሊቱ በመርዛግ መርፌ ተጠቅጥቃ ኖር ፥ ዕድሜ ልካቸውን ሙሉ ክረምት በመጣ ቁጥር እያመረቀዘች ስትጠዘጥዛቸው ትኖር ነበር ። እንዳንዴ በጨው እንዳንዴም በሚጥሚጣ እያጠቡ ሲጠብሷት መለስተኛ እፎይታ ያገኙ ነበር ። ተጀምሮ እስኪጠረስ ድረስ ፥ ሐኪም ቤት ሔደው ቁስሊቱን አሳክመዋት አያውቁም ነበር ። “ከተቆረጠች ትሞታለህ!” የሚል ንግርት የተነገረባቸው ይመስል ፥ ዘመድ አዝማድ ፥ ወላጅ ወዳጅ ፥ የቤት የጎረቤት ሰው ሁሉ ፥ “ትቆረጥ!” እያለ ሲመክራቸው ፥ “አብረን እንደተወለድን ፥ አብረን እንሞታለን!... ባንድነት የተጠመዱ ጥንድ በሬዎች ፥ የሚፈቱትም ባንድነት ነው !» እያሉ ፥ የቁስሊቱን መከራና ሥቃይ ችለውና

ታግሠው ይኖሩ ነበር ።

ዘመን እየተኳደና ዕድሜም እየገፋ በሔደ ቁጥር አቅም እያነሰ ፥ በአካል ላይ የነበሩ ንስቁል ክፍሎችም ከመትርአቸው ይልቅ እየኳለበቱና የማጥቃት ኃይላቸውም እየተጠናከረ ፥ አርጅና የተጫነውን አካልም ይበልጥ ማሠቃየትና ማስጨነቅ ይጀምራሉ ። ባለፈው አመት ይህ አይነቱ ባረጁ ሰዎች ላይ የሚደርስ የመከራ ጽዋ ፥ በኛ ጀግናና አርበኛ ሰው ላይ በመድረሱና የዚያች ቁስልም ምዝመዛና ጥዝጠዛ መጠኑ እየጨመረ ሔዶ ፥ ሥቃዩን ከማይችሉበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ፥ በመጨረሻ ላይ ሆስፒታል ለመሔድ በግዛ ራሳቸው ይወስናሉ ። ይህን ተባራሪ ዜና የሰማሁት ፥ በቅርብ ሰሞን ነው ።

ዜናው እንደሚያብራራው ፥ ያቺ ከአርባ አመታት በላይ አብራቸው እያመረቀዘችና እየጠዘጠዘች የኖረችዋ ዓታቸው ፥ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ እያሠቃየች ልና ስለነሳቻቸውና ዕድሜያቸውም ወደ እርጅናው ምዕራፍ ስለተጠጋ ፥ መፍትሔ ለማግኘት ወሰነው ሆስፒታል ገብተዋል



ይላል ። ምናልባትም አግራሞ የሚሆን ሌላ መፍትሔ ካላገኙ ያቺን አርባ አመት ሙሉ ተሸክመዋት የኖሩትን ቁስላግ ዓታቸውን ነው ወይ ልንለያይ የሚለውን የመሰንባበቻ መዝሙር እየዘመሩ ፥ ኋላ በትንግኤ ሙታን እስኪገናኙ ድረስ፥ ሊሸኟት የተዘጋጁ ይመስላል ። ተከታትሎም በደረሰኝ ዜና ፥ የተመደበላቸው ዶክተር ፥ የሳቸውን ሙሉ እምነት ያለው በመሆኑ ፥ የዓቴቱን ቁስል አስመልክቶ ምን ማድረግ ለመወሰን የተቸገረ ይመስላል ። “አርባ አመት ሙሉ ተሸክመው የኖሩትን ክፍለ አካል ድንገት ለመቁረጥ መሞከር ፥ በራሱ በአካሉ ላይ ከሚያስከትለው ችግር ይልቅ በዓቴ ባለቤት መንፈስ ላይ የሚፈጥረው አደጋ የከፋ ሊሆን ይችላል” እያለ በማሰብ ፥ ዶክተሩን ጭንቀት ያንገላታዋል አሉ ። “ትቆረጥ!” የሚለውን ሐሳብ ራሱ አቅርቦላቸው፥ የራሳቸውን ግላዊ አስተያየት ፥ ከራሳቸው መስማት ፈልጎ ቢጠይቃቸው ፥“የሕመሜን መድኃኒት ራሴግ የማውቀው ከሆነ ፥ ሐኪም ዘንድ ምን ያስመጣኝ ነበር” እያሉ ይቀልዱበታል አሉ ። ሐኪሙም ፥“ይህን ያህል ረጅም

ዘመን ፥ ያለ በቂ ምክንያት ታግሚፕን ዓታቸውን ይዘው አልኖሩምና ፥ አሁን እንቁረጣት ብንላቸው ፥ ያረጋዊ ነገር ፥ እኛ የማናውቀው ልዩ እምነት ይኖራቸዋልና ይህን ጉዳይ ለማጥናት ፥ የሕክምና ባለደረቦቼን መሰብሰብና መምከር ይኖርብኛል” ብሎ ሐሳቡን ያልባል ።

የኛ አረጋዊ አባት ፥ በመጨረሻ ዘመናቸው ላይ እንደዚያ ያለ ዕድል ስለገጠማቸው ፥ ያ ሁሉ የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው የእምባቸው ወዓት በተበታተነበት ሰዓት ሳይረዳቸው ፥ ሳያፅናናቸው ፥ በመጨረሻ የጭንቀታቸው ጊዜ ሳይደርስላቸው --- እንዲያ እንዲያ በመሆኑ ፥ እኔም ጭምር የደረሰባቸው ሁኔታ አሳዝኖኝ ፥ ይችን ግጥም ለመጻፍ ገፋፍቶኛል ። ከዚህ ተልዕኮ ከልል ውጭ ፥ ግጥሚቱ ሌላ ሐሳብ አዝላለች የሚል መንፈስ ሸውራራ አንባቢ ቢመጣ የራሱ ጠንጋራነት የፈጠረው ጥቅንጥቅ እንጂ ፥ እኔን እንደማይመለከት በቅድሚያ አስጠነቅቃለሁ ።

በጠንጋራ ዓይኑ ጎኪናቸው እንሸዋረው ስለሚመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ጉዳይ ከተነሳ ፥ እንደሚመለከተው



ያለውን እኛጊ ትኔያዊ ግጥም ፥ እንዴት አድርገው ይተረጉሙት ይሆን ? የዚህ ግጥም አቀንቃኝ መሪ ሐሳብ ፥ የግይ ዉበቱ ረቂቃን ትዕይንቶች ናቸው ። እነሱን አስመልክቶ የሚነገረው ሁሉ ግን ፥ እነሱነታቸውን ግዙፉን አስመስሏቸዋል ። የሚቀርብለትን ሐሳብ ሁሉ ፥ በተዉናበስ ዓይኑ ልቡናው እየተንሸዋረረ ፥ አጠናግሮ የመተርጎም ደዌ ለተጸናወተው አንባቢ ሁሉ ፥ ከዚህ የተሻለ ሊቀርብለት የሚችል እኛጊ ግጥም አይገኝለትምና ፥ እንደፈለገው እንዲንሸዋረርበት ፥ ተከታዩን ግጥም ተጋብዟል ። የዚህንም እትም ወንደርደርደሪያ ፥ በዚሁ ግጥም እየዘጋሁ ፥ ስለተቀሩት የእትው ግጥሞች ዝርዝር ተዉግሬ መግለጫ ያልሰጠሁት ፥ ግልጽ ስለሆኑና አንባቢዎቼንም ተልዕኮአቸውን ለመረዳት እንደማያስቸግሩአቸው ስላመንኩ ነው ።

## የ ደ ረ ሰ   የ ለ ም !

ስግደ አለቀስ — ዝናብ ፅንባ አውርዶ ፥
የሚያፅናናው ቢያገኝ — ፍዉራን ተማልዶ ፥
ያዘኑ ግን የለም — ጭላውን አውርዶ !

እንዴውም ቀልዶ – እያለ ሸናብን !

እግዜሩን አዋርዶ – ከሰማይ ያለውን ፥

ይለናል ምድር ና – ታግለን ይጥለን !

ምድርም ተበሳጭታ – ተንቀጥቅጣ ነበር ፥

የሰማት ግን የለም – እዩዝሽ የሚል ከምር ፥

ደነሰች እያለ – ከመግቅ በሰተቀር !

መብረቅም ተወንቶ – ባገኘው ሁኔታ ፥

አሳይቶ ነበር – ምልክት ብልጭታ ፥

ድረሱልኝ የሚል – የጥሪ አቤቱታ ።

ከሩቅ ተቀምጦ – የሚያየው ተመልካች ፥

እግዜር ፎቶ አነሣን – ይለው ነበር ሲተች ፥

ምን ሆነ እንደማለት – ሲገባው ተፀፃች ! !

ነጎድጓድም አብዶ – እሪ ብሎ ነበር ፥

ለርዳታ ጥየቃ – ከታዛቢ ፍጡር ፥

የሰማው ግን የለም – እንደዚያ ሲያጓጉር !

ከቶም መርዳት ቀርቶ – ይሻል ነበር ዝም ቢል ፥



የሰማው ሰው ሁሉ – መቀለጃ አርጎታል ፥

እያለው በሬሱ – ጃዙን ይደልታል ! !.. ወዘተ

ታዲያ ምን ያደርጋል – ሰማዩ ማልቀሱ ፥

ሰው ካልደረሰለት – ተማድፎ በነፍሱ ! !

ታዲያ ምን ያደርጋል – ማውራቱ በሩቁ ፥

አለሁልህ ባይኖር – ሳይደርሱ ለጭንቁ ! !

ታዲያ ምን ፋይዳ አለው – መንቀጥቀጧስ ምድር ፥

ፍጡሯን ካላዳት – ተካፋይ ነን ችግር ! !

ምን ይጠቅመው ይሆን – መብረቅ መብለጭለጩ ፥

ያመናቸው ሰዎች – አብረው ካልተቀጩ ! !

ነጎድጓድስ ቢሆን – ምን ጠቀመው መጮህ ፥

ደራሽ ፍጡር ላይኖር – አለው የሚል እዩዝህ !

ግን ለትዝብቱ እንጂ – ብሶት ቢያስተጋቡም ፥

ጥይታቸውን ነግረው – ፍጡሯን ባይረዱም ፥

ሰማይ ምድርም አሉ – መብረቅ ነጎድጓድም ፥

ሕልው ናቸውና – ይኖራሉ ባለም !

ችግር ኖረ አልኖረ – ጭራሽ ተበቀ አይቀርልም !!

# አንደርድር አድራሽ

ዋይታቸውን ሰምቶ — ለከፉም ለደጉም ፤
ለትዝብቱ እንኳ — ከሚገኙት ባለም ፤
ከዚያ ሁሉ ወገን — ከ፲ ከ፲ አንድም ፤
ወዳጅ ሆነ ረዳት — ከቅርብም ከሩቅም ፤
እሪታ ሊያሰታግስ — የደረሰ የለም !!!


## ው ጠ ራ !

ቀደም ሲል ላነበባችሁት ፤ የሩቅ ምሥራቅ
የሰዎች ባሕርይ መጠንቀያ
መፈተኛ

ከዚህ በታች የሠፈሩት የታሪክ ትዝብቶች ፤ በአብዛኛው የሀገራችን ሕዝብ ተቀባይነት ያገኙ ናቸውና ፤ ምንም እንኳ ታሪክ የጣለ ሰዎች ግለኛ ተግባራዊ ውጤት ብቻ አለመሆኑ ቢታወቅም ፤ ከግለ ሰቦቹ አወቀ ልደት እንስሳት ጋር አገናዝባችሁ ፤ ልክነቱን ለማረጋገጥ ሞክሩ ።

| ሰዎቹ | ተግባራዊ ውጤታቸው | አውቁ | እንስሳው |
|---|---|---|---|
| (1) በቴዎድሮስ | አንድነትን ቀድሶ | ? | ? |
| (2) በዮሐንስ | ደርቡሾችን መልሶ | ? | ? |
| (3) በምኒልክ | ፈረንጆች አምበርክኮ | ? | ? |
| (4) በኢያሱ | ሻሽ ነው ትራሱ | ? | ? |
| (5) በዘውዲቱ | ሬሳ ነቶቱ | ? | ? |
| (6) በተፈሪ | የለም ፍርቱሪ | ? | ? |
| (7) በሰም አይጠሩ | ዲክታተር ጣያቱ | ? | ? |
| (8) በሰም አይጠሩ | ነገዶች አከሳከሰ | ? | ? |

# ቆርጠሃት ጣልልኝ?



# መዘክርነቷ


በጣልያን ወርዘኛ ጥይት ፥ ባታቸው ተነድፋ ፥ ቁስሏ እያመረቀዘ ፥ አርባ አመታት ሙሉ ፥ ቢገትቁ ባት የረሠ ፥ አሁን በያ ሰሞን ፥ በርጅናቸው ግብ ቲያ ዘመናቸው ላይ ፥ እንደገና አገርሽቶባት እየጠ ዘጠዘች በላስገረምቸው ፥ ዶክቶር ሐኪም ትቶረጥ ወይስ እንዳለች ጀርሞቿን ለመከላከል እንሞክር ብሎ ስላቀረበላቸው ሐሳብ ፥ ይህን መፍትሔ ለመወሰን ጥ ንቀት ላደረባቸው አረጋዊ አባትና ፥ እባቸውንም አ ስመልክቶ ስለተከሠተው ልዩ የሰዎች ችግር ፥ ይህች ግጥም በመታሰቢያነት ቀርባለች ።




በጣሊያን ወረራ — በዚያ ጥቁር ዘመን ፤
ሹሞ ግዴት ወቶት ፤ ትንሽቱ ባቱን ፤
ነበረ አንድ ሰው — አርበኛ ወኮንን ።

እያወረቀዉ — የቶሰለው ባቱ ፤
አርባ አመታት ግዷል — ቢያከው በየለቱ ።

በስተኋላ ላይ ግን — ሥቃይ ቢበዛበት ፤
በዕርጅናው ወግግን — ጀርሞች ቢነገሡበት ፤
ሊያስቆርጥ ወሰነ — ያቺን ደዌኛ ባት ።




## መዘዘኛዋ ጣት

በተፈጥሮማ — ያለ ትርጉሟ ናት ፤
ጣጥንቶች ተዋቅሩ — ፀደም ለሚገቶነት ፤
ቃቢሉ ተጠፍሩ — ለእሥራ ጆሮት ፤
በሥጋ ታንፃ — ሕይወት እምላለ ለሥለት ፤
በጥፍር በፉሳ — የለበጆች ሥፀት ፤
ለሌላ ጆርም እንጅ — በዋዋን የንፋት !!

ያ የጣልያን ጥይት — ውስጧ ተቀርቅሮ ፤
ሠርቆ ሊያሠቃያት — የናረች በርር ፤
ምንም ያልተሻላት — ከእምናም በንድር !!

ውስጧ ተቀርቅሮ — የዛው ያ ጥይት ፤
ጆሮዎች ወሌሉ ወሌሉ — በሌያች ደዌኛ ጣት ፤
ሥቃይ በዝቶባት ነው — ቁረጠኝ ያሰኛት !
እርሳ እወት ወቶ — ሊኖር ያማቀያት !!

ጆሮዎጅን ሬለቅቆ — ጓለንታ ከወጣ ፤
እትወኝም ነበር — ዛጋጅት ለቁርጠ !

ሕክምና እድርጋ — ደወርፈ በክንድ ፤
ጆሮዎጄ እንዲጠፉ — ወሳር ነው ለማዳን ፤
የምን ቁርጦ ወሳለ — እሄዳዊ ከዳለን !
ወቶ ለሥንትን — ከሥፍረቱ ማቅጠን !!!

ትቆረጥ ያሉ እሉ − በፍፁም ተስማምተው ፥
ወርዝነት እንዳላት − ሁሉም አረጋግጠው ፥
በጆሯም መበከሏን − ባጠቃላይ አምነው ።

ሌሎችም ነበሩ − በዚህ ያልተስማሙ ፥
ግሏን እንደሚቻል − ውሳኔ ያሰሙ ።

ክርክሩ መሮ − እርስ በርስ ሲጋጩ ፥
ጥቅጥቁ ግሎ − እርስ በርስ ሲናጩ ፥
ያልነካኩት የለም − ግሏን ሊቋጩ !!

ትቆረጥ የሚሉት − ጥቂቶች አባላት ፥
አውቀው ተረድተው ነው − ቫይረስ እንዳላት ፥
መመረዝ መቻሏን − ቀሪውን አካላት ፥
ፈረንጆች«ኢንፌክሽን»− ብለው የሚጠሩት ፥
"እንደአያድርስ" ያለ − የሰው ልጆች ጠላት ።

አትቆረጥ ባዮች − ያቀረቡት ሐሳብ ፥
አካለ ጎደሎ − ታረጋለች ባግባብ ፥



"ጉምድ ጣት" እሰብላም − ሁሉ እምታስደብ ፥
ሰውነት ውበትን − ከስፋት ማጣበብ ፥
ይሆናል ይላሉ − ተፈጥሮን መቀንጠብ ፥
እምላክ የሠራውን − ውበት አካልን ቢን !

በመጨረሻ ላይ − ሁሉም ባንድ ተስማው ፥
የጣቱ ባለቤት − በፍላጎት አቅው ፥
ራሱ እንዲወስን − ውሉ ድምፅ አሰው ።

እንዲህ ሲል አሰማ − እሱም ተጠራና ፥
ለገዛ ራሱ ጣት − ባለቤት ነውና ።

በዚያ ስብሰባ ላይ − ያለውን ነገር ፥
ግልጽልጽ አደርጎ − ያንጀቱን አሰማ ።

"አካሌን ወርዛ − ካስቸገረች በርግጥ ፥
ምናለ ቆርጣችሁ − ብትጥሉልኝ ከግጥ ፥
እየጠዘጠዘች − ካለች ዉና አልሰጥ !

በርግጥ ኢንፌክት አረጋ — ከገባች ከውስጧ ፥
ፋንዲት ጫቱ ሲባል — ሙሉ አካል ግቅለጧ ፥
እንዴት ጨና ይጫ — በቅንጫት ተገጧ !!

ሐኪሙ እንደሚለኝ — ከሆነማ ጫቷ ፥
የተረፋት የለም — ያልነካችው እኗ ፥

የስሮቿን ሐረግ — በደም ውስጥ በርግታ ፥
አውታረ ጅሮቿን — ባጥንት ውስጥ አድርታ ፥
ከራስ ፀጉር እስከ ጥፍር — ይዛለች በተርታ ።

መተንፈስ አልቻልኩም — እንዲህ በቀፋሉ ፥
ወርቄው ይሆናል — ሳምባዬን በሙሉ !

ኢንፌክት አርጋው እንጅ — ያቺ ወርቄም ጫቱ ፥
መናገር ያልቻልኩት — በሙሉ እንደበቴ !

ምላሴን አስሯው ነው — መናገር ያቃተኝ ፥
አለዚያማ በርግጥ — ሐቁ ወቸ ጠፋኝ !



ነካክታው ቢሆን ነው — ያ ጥርሴም ወድከው ፥
ኸንብሩ እንኳ ከብዶት — ያቅት መቆርጠው !

ያ ከንፈሬም ቢሆን — መሳም እንኳ ያቃተው ፥
በሷ ፋፋኮ ነው — ተንከርፍፎ ያለው !

ወርቄማይቱ ጫት — አይፋ ይሆናል ፥
የመረዛችው ዓይን — ማየት ያለ አልቻል !

እያቅተው ነበር — ያ ጆሮዬ መስማት ፥
በሷ ጦስ ይሆናል — የደነቆረበት !

ማፋራት ያልቻለው — ጉልት ኩፋሊቱ ፥
መፍጨት የተሳነው — ሙትድሉ እንጆቱ ፥
ወርፋቸው እንጅ — ያች ወርቄማ ጫቱ !

ጠቅላላው አካሌ — ድክመት የተሰማው ፥
ጥርጣሬ የለኝም — በጫቱ ጦስ ነው !

ያ መንጋጋዬ ጋኔል — የናረው ሲገጠኝ ፥

እሷን አሳፀ ነው — ወቅናዬን የነሳኝ !

በታሪክ በልማድ — በባሕል በወግ አንፃር ÷
የሌላን ሀገር ሰው — ጠባይ ብንመረምር ÷
እንኳን ዓቱ ቀርቶ — እግሩ እንኳ ቢሰበር ÷
ብዙ ግድ የለውም — ስድብም አይደረድር !

የኛ ሀገር ሰው ግን — ቀራጫ ነገሩ ÷
እያለ ሲሳደብ — አይጫል ነው ሲነሳ !
ወዘተ. ወዘተ. ወዘተ. — አሁንም ወዘተ ÷
ከቶ ወቸ ያልታል — ሁሉ ከታተተ !

ስለዚህ ስብሰባው — የኔን ቢቀበለው ÷
ምርጫ ውሳኔዬ — እንድትቆረጥ ነው !

እብራኝ ከቆዮች ግን — ነዝናዛ ነዝናዛ ÷
ወጨረሷ አይቀርም — ልትቀብረኝ ነገዛ !...»
እለና አሰረዳ — ባለፃት ወች ጥዛ !



«...ከሐኪሟ ጋራ — ያለኝም ድርድር ÷
ወታወቅ አለበት — እዳንዳች ጥርጥር !

ሕጋዊ ባለቤት — በሆነው መካከል ÷
በምምነት ኖሮ — ካልተደረገ ውል ÷

ያንዱ ክፍል ብቻ — ቢወስን በራሱ ÷
አወጀ ማለት ነው — ጦርነት በነፍሱ ÷

"ዩኒ ባይ" ውሳኔ — የሚለው ፈረንጁ ÷
ወገባባት ሲኖር ነው — ሁሉም በየፈርጁ ÷
ሌሎችን በወናቅ — ምንም አይፈረጁ =

ሕወም ፈዋሽ ወሰሎ — የዓት አሰታራቂ ÷
በኛ ወሐል ቢኖር — ሌላ ወግ አጥባቂ ÷

ይበልጥ ያወዘ እንጂ — የቁሰለኛውን ዓት ÷
ጥራሽ አያድንም — ጂ ጊዜ ቢያግት ! !

እኛው ብቻ ሆነን — ተስማምተን በሐቁ ÷

ይሻለናል በርግጥ — ችግርን ግረቂ ÷
በግለት አሰረዳ — ሽሜ ጉት ሊቁ !!!

ቀራጭ አስቆራጩም — አንድ አይነት ከሆነ÷
ትርፉ መንዝንዝ ነው — ጀርምም አልቦነ ÷
ወልሶም ያጠቃል — ቀን አይቶ ከዳን !
ብሎ ደመደመ — ባለሟት ወሰን !!!

የሟቷን ባለቤት — የሰማ አንድ ዶክተር ÷
በተቃውሞ ድምፅ — ጀመረ ሊናገር ።

ባለቤቱ ቢልም — ትቆረጥ በፍጥነት ÷
ባሳቡ አልስማማም — ሰላለበት ድክመት !

አምፒዩትድ ትሁን — ባዩ ሰው ቢበዛም ÷
ግዳን ስለሚቻል — ባሳቡ አልስማማም !

በፍፁም በጥራሽ — የምን ቆረጣ መጣል ÷
የጊግ መቆረጥ — ጎደሎ ያደርጋል ÷



እንዲያ የተጥበን — የኪነትን አካል !
ደገምም ሌላውን ጣት — ለቁርጥ ያበብሳል !
የተነቃነቀን — ጥርስንም ያወልቃል !
ከርፋፋውን ጆሮም — ቆራርጦ ይጥላል !
ቀውላላን አፍንጫን — ልቀንጥብ ያስቻል !
ሸውራራ ዓይኖችን — ፈጥኖ ያስወልቃል !
በአጭሩ እንትንም — ኩንትሽ ያስደርጋል !!

ባርባ በሰማንያ — ተቆርጦ በሥልጣን ÷
ስምምነት ሳይኖር — በካራ ቢወሰን ÷
ሰንቱን አለሰሚት — ያደርገዋል በድን ÷
አጥፍና አቅርቦ — በሚያይ የሰው ሁድን !

ከመቁረጥ ይልቅ — ይሻላል መምከር ÷
በወን በፈጠረው — በሐኪም ምርምር ÷
በልዩ ክኒና — ለግዳን መጣር !

ወቸ ተምከረ — ሻይረሷ እንዲወድም ÷
በልዩ ፀጥት — በጠቢባን ቅመም !

ወቸ ተሞከረች — በትል አድርቅ ክኒን ፥
የያዛት ወርዝ ሁሉ — ጠፍቶላት እንዲበን !

ወቸ ተሞከረች — በጸንጸሊን ማጥፊያ ፥
ጀርሞቿ እንዲወድሙ — የገቡት ባት ጉያ !

አወይ አደንዛዥ — በዚያ ክብረ ሰግይ ፥
ጀርሞቿን መሠለቅ — ይቻልስ የለም ወይ !

ወቸ ደነሙባት — ጁሁና ካህኑ ፥
ያንደርቢ አስግት — ጀርሞቹ እንዲበኑ !

በልዩ በርበሬም — በዚያ በሚጥሚጣ ፥
በቁንዶ በርበሬ — ባሪቱ እሚጠባ ፥
ወቸ ተሞከረ — ታጥና እንዲወባ ፥
ምድረ ጀርም ሠራዊት — ባት አባምም ባባ !

ወቸ ደነመባት — ያ ጠንቋይ ደብተራ ፥
ማዕሠረ እድን — ሊፈታ ሊያጠራ ፥



ጋኔል ወቸ ባይ — ወናፍስትስ ጠራ !

ይሀ ሁሉ ወፍትል — ወሞከር አለበት ፥
እንዴው በችኮላ — ቆርጦ ከሚጥላት !

ሁሉ ተሞከር — ባቲቱ ካልዳነች ፥
እግራሞ የላትም — በግድ ትባላለች !

አደገኛነቷ — በርግጥ ከታወቀ ፥
ካካሏ ጋር ያላት — ዝምድና ወለቀ ፥
ግለት ነው ተጊም — አለቀ ደቀቀ !!

እስከ ዘላለም — ወታረብ እንዳይኖር ፥
ወወድምድ አለበት — እምራምቿ ከስር ፥
ያኔም ታወቀሟለች — እንዳይቻል ወኖር ፥
ካካል ተገንጥሎ ፥ ለብቻ ወዘረር ፥
ባዚያ ኀልኀታ — በባዶ ወቃብር !!!...»
እለና ጨረሰ — ስሉ ፊሉን ባጭር ።

አንድ ሌላም ዶክተር — ፍጆታ ጠይቶ ፥
እንዲህ ሲል አብራራ — ግራ ቀኙን ዐምቶ ፥
ከልዩ ጥናቱ — ፊዚኦሎጂ ውብቶ !

    «..ባንዲት ሴት አካል ውስጥ — አሉ ብዙ ክፍሎች፥
    አጥንትና ጥፍር — ሥጋ ደም ጅማቶች ፥
    ደግሞም ቆዳና ፀጉር — ልዩ ልዩ ሴሎች !

እነዚህም ክፍሎች — እንደተፈጥሮአቸው ፥
ልዩ ጠባይና — ባሕርይ አላቸው ፥
አንዱ በተፈጥሮው — የሚለይ ከሌላው!

    እንላላቸውትም — አንዱ ብቻ ይሆናል ፥
    ቫይረስ ወርሶት — የታመመ አካል ።

ስለዚህ ባጭሩ — ይቆረጥ ካላችሁ ፥
ያ ክፉል ብቻ ነው — ማረፊያው ስንጠያችሁ !

    እለያም ውሳኔው — ያለበት መሰጠት ፥



    በያንዳንዳቸው ነው — በነዚህ አካላት ፥
    በደረሰው ሳይሆን — ሁሉም ሳያምንበት !

ስለዚህ በሥርዓት — ካለበት መወሰን ፥
የነሱ ጋራ ድምፅ — መስማት አለበት ፥
ቅድሚያውም ይኸው ነው — ተቻኩሎ ከመቁረጥ !
በማለት አብራራ — የልቡን በማውሳት ።....»

    በሴት መቁረጥ ጉዳይ — የተቸው ብዙ ነው ፥
    በመቃወም ሆነ — በድጋፍ ፍጆታው ።

"በሴቷ ላይ ያሉ — ልዩ ልዩ ክፍሎች ፥
አጥንትና ጥፍር — የሥጋም አሥራዎች ፥
ሌሎቹም አባላት — ቆዳ ደም ጅማቶች ፥
መስጠት አለባቸው — የውሳኔ ድምፆች ፥
የየግላቸውን — ምርጫና ሐሳቦች ፥
ለቁርጥ ከመቅረቧ — ያቺ ሴት እንጂ!..."
የሚለው ይበዛል — ከጉባኤ አባሎች ።

# ቆርጠሃት ጣልልኝ?



ጥቂትም ነበሩ — ውበት ያስተካከሉ ፥
ባለቤቱ ራሱ — እንዳሻው ያርጋ ያሉ ።

አንድ አረጋዊ ዶክተር — በረዥም ዲስኩሩ ፥
ስለ ሐኪም ሞራል — አንስቶ ባጭሩ ፥
ተናገሮ ነበረ — ስለ ክልል ቅጥሩ ።

እሱ እንዳለውም —“የሰው አካል ክፍሎች ፥
ተባብረው ቢኖሩ — እ ናቸው ዉነኞች ፥
ጀርምም አይደፍራቸው — እንኳንስ ተራ ምች !

እንደ ሰው ተባብረው ፥ ከኖሩ አንድ ላይ ፥
በሐቅ ተከባብረው — አንዱ አንዱን ሳይለይ ፥
ወንድማማች ሆነው — በንጽሐ ባሕርይ ፥
ባሠሩት ነበር — ሕይወት ባደባባይ !!

የሥጋ ውስጥ አጥንት — ሥጋ አለመውጋቱ ፥
በፍቅር ሰላለ ነው — ከጥንቱ ከጥዋቱ ።

«አይ ጣቴ አይ ጣቴ — የአካሌ ክፋይ ፥
ዘንተ ዓለም ኖረሽ — ከኔ ጋር አንድ ላይ ፥
ዘንድሮ በግዳጅ — ልትለይኝ ነው ወይ !!!»



የገዛ ታሪኬን ሳነበ
ውጥራሴን ገረመኝ!

# ቆርጠሃት ጣልልኝ?

ከዚህ ተፈጥሮ ሕግ — ሥርዓት ተምራችሁ ፥
የአካል ክፍሎችን — ባንድ አስተባብራችሁ ፥
ማኖር ብቻ እንጅ ነው — መቁረጥ አይዳዳችሁ !...»

ብሎ እንደወረሰ — ዶክተሩ ሊሰኩሩን ፥
ጉባኤው አበቃ — የዓት ውይይቱን ፥
እጀንዳም ተያዘ — ሊወሰን ሌላ ቀን ።

ቀጠሮ ተይዞ — እጀንዳው ቢሠምርም ፥
እስከ ዛሬ ድረስ — ስብሰባ አልተጠራም ።

# ሰካራም አህያ?



እረኤውን እየተጠቀመ ፥ በስካር የሚጠነብዘው ሰካራም ሁሉ ፥ ለካስ በዳግም ልደቱ አህያ እንደሚሆን ታውቆት ነው ።



ፍንደታ — ቁ 92

ከዚህ ተፈጥሮ ሕግ – ሥርዓት ተምራችሁ ፤
የአካል ክፍሎችን – ባንድ አስተባብራችሁ ፤
ማኖር ብቻ እንጅ ነው – መቁረጥ አይሻላችሁ !...»

ብሎ እንደጨረሰ – ዶክተሩ ዲስኩሩን ፤
ጉባኤው አበቃ – የዓት ውይይቱን ፤
አጀንዳም ተያዘ – ሊወሰን ሌላ ቀን ።

ቀጠሮ ተይዞ – አጀንዳው ቢወምርም ፤
እስከ ዛሬ ድረስ – ሰብሰባ አልተጠራም ።

# ስካራም አህያ?



አረሌውን እየቀወቀወ ፤ በስካር የሚጠነብዘው ሰካራም ሁሉ ፡ ለካስ በዳግም ልደቱ አህያ እንደሚሆን ታውቆት ነው ።



# መዘክርነቷ

በምድራዊ ቀዳማይ ሕይወታቸው ሳሉ ፥ ከሞታቸው በኋላ ፥ በዳግም ሕይወታቸው ምን እንደሚጠብቃቸው ባለማወቃቸው ብቻ ፥ አስጠያፊ ምግባራትን በየዕለቱ እየፈጸሙ በዘፈቀደ እንዳሻቸው እየተሞላቀቁ ፥ ለሚኖሩ ሁሉ ነው ።



# ስካራም አህያ?

በሩቅ ምሥራቅ ሰዎች — ባሕልና እምነት ፥
"አትሞትም" ይላሉ — ያቺ ነፍስ ሕያዊት ፥
ልብሷ ሥጋ ከድቶ — በሞቱ ሲለያት ።

"አትበንም አትተንም — ሕያዊት ያቺ ነፍስ ፥
ጨርሳ አትወድምም — ለባዊቷ መንፈስ ፥"
ይላሉ ፈርጥመው — በምሥራቅ አድማስ ፥
ተለይቷት ሲሸሽ — ሥጋ ሲገነደስ ፥
ካፈር ትልትታው — ሲቀበር ለመፍረስ ፥

ነፍስ አትቀበርም — ረቂቅ ናት ቅዱስ ።

ሥጋን የተለየች — ነፍስ ግን ሕያዊት ፤
ዝውውር አድርጋ — ያካል ኪራዩን ቤት ፤
ወደ ሌላ አካል — በልዩ አዲስ ልደት ፤
ትኖራለች እሱ — ዘለዓለም በሕይወት ።

በተለየ ደግሞ — ሰው የተባለው ፍጡር ፤
በዚህ ዓለም ሳለ — እንደሠራው ምግባር ፤
በነፍሱ ያገኛል — ዋጋውን በድምር ።

በነፍስ ዳግም ልደት — በሪኢንካርኔሽን ፤
ሌላ ሥጋ ለብሳ — ተወልዳ እንደሕፃን ፤

ገዝፋ ትወጣለች — ባዲስ ልዩ አምሳል ፤
ናትና ሕያዊት — የማትሞት እንዳካል ።

በሰው አካል እንኳ — በምትኖርበት ወቅት ፤
ክፍሉ አይታወቅም — ገላው ያለችበት ።
ልብ ላይ የሚሉ — ጥቂቶች አይደሉም ፤



ደምን ሲያስተላልፍ — ስለሚል ድም ድም !!

ሳቅ ሳቅ የሚላቸው — በሚሰጡት ትርጉም ፤
ነፍሴ ጥርሴ ላይ ናት — ይላሉ ለማንም ።

ልግታ ልቦቅስ — የሚለው ሰው ደግሞ ፤
ነፍሴ ከጄ ላይ ናት — ይላል ያ ገጠሞ ።

ነፍሴ ከብልቴ — እያለ እሚያምነው ፤
ሲያባርር ይውላል — ባለእንስት ያታ ሰው ።

ነፍሱም ካይናቹ ላይ — እንዳለች የሚያምነው ፤
ለስሜቱ ቅርቡን — ነው እሚመለከተው ።

እንዳንዱም ከእግሬ ናት — እያለ በማወን ፤
እንደሮጠ አለ — ምንጊዜም ሌት ከቀን ።

ወዶኮ አይደለም — የሚንሸዋረረው ፤
ፈልጎኮ አይደለም — የሚሽወደወደው ፤
አስገድዶት እንጂ — ስሜቱ ተፈጥሮው ።

የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች — ይህንን ሲገልጹ ፤
በዳግም ልደት ነው — የትርጓሜው ቅርፁ ፤
በግልፅ የሚታየው — የፍትሕ የርትዕ ገጹ ፤
ፍጥረቱን ቀይር — የሚሰጠው ድምፁ ።

በተፈጥሮ ሥራት — ያለ በዚህ ዓለም ፤
በዳግም ልደቱ — እንደጥንቱ አይሆንም ፤
ያታው ሳይቀር በዲስ — ይለወጣል ሁሉም ፤
ይላሉ ምሥራቆች — ቢጠቅም ባይጠቅም ።

ምድራዊ ምግባሩ — በሚወስነው ኃይል ፤
በሕይወቱ እያለ — እንደሠራው በደል ፤
ወንድ የነበረው ሰው — ሴት ሆኖ ይወጣል ፤
ወይም ሌላ እንስሳ — አውሬውን ይሆናል !

ክቡር የነበረው — በሞንት ልደቱ ፤
ታላቅ ሰው የነበር — እንደሰውነቱ ፤

ከሞተ በኋላ — የማትሞተው ነፍሱ ፤



ሌላ ሥጋ ለብሳ — ተቀውሮ መንፈሱ ፤
ሌላ እንስሳ ይሆናል — በልደት አዲሱ ።
እዮብ ነው ድንቅ ነው — ያዲስ ልደት ኩነት ፤
ያሉበትን ትቶ — ከሌሉበት መግባት ፤
“ሪኢንካርኔሽን”— ብለው የሚጠሩት ።

ሰው የነበር ፍጡር — ተራ ውሻ ሲሆን ፤
ኧረ እንዴት አይገርምም — የድኅረ ሞት ክውን!

እኔ አልዘረዝርም — ይህን ዚቅ አበፍቼ ፤
ውቅያኖሴ ነው — የማልችል ቀድቼ ።

ለማሳያ ያህል — አንዳንዶቹን ላንሳ ፤
በዳግም ልደቱ — ከሚያየው አበሳ ።

በሕይወቱ እያለ — ቀምታሚ የነበር ፤
ውስኪ ሾድካ እያለ — ሲጨልጥ ሲቀውር ፤
ለክርና ወንበሩ — ጃፊ ሲጠናበር ፤
በዕድል ጀዋ ተራው — ወደ ሞት ሲሻገር ፤

በዳግም ልደቱ – ወልሶ ሲፈጠር ፥
አህያ ሆኖ ነው – የሚገዝፍ ለመኖር ፥
የስካራምነት – ግዝልያና ክብር ፥
ብለዋል ይላሉም – የምሥራቅ ባሕል ምሁር !

በቀድሞ ሕይወቱ – የነበር ሰካራም ፥
በዳግም ልደቱ – ሲወለድ ለዓለም ፥
አህያውን ሆኖ – ነው እሱ የሚደክም ።

እረ ድንቅኮ ነው – ያዲስ ልደት ጸጋ ፥
አህያውን ሆኖ – ሲጫን ሊኖር ነዋ !

ሰው የነበር ፍጡር – አህያውን ሲሆን ፥
ምንኛ መዝቀጥ ነው – በተፈጥር ዕርከን !

ውሼ እየተባለ – በለገመ ቁጥር ፥
በነወድ ሊነረት – በጅራፍ ሊወተር ፥
ሲራገጥ ሲያናፋ – ዘለዓለሙን ሊኖር !

በመጠጥ መሰከሩ – ለዚያ ካበቃው ፥



ምነው ወኘ አይኛል – ቢጠው ሲጠግ !
አምናለሁ ይለያል – የርግማቸው አይነት ፥
ውስኪ ሲጨልጥ – የኖሩት መኳንንት !

አይመሳሰልም – ሲያናፉ እንዳህያ ፥
ሞኝ እንግም ቁርባቸው – የነበር እናያ !

በርግጥ ይታየኛል – ወዳኛ ጀርባቸው ፥
ሾድካ አርገው የኖሩ – ቁርባቸው ምባቸው !

ጠጭ የነበረው – ያንን ጠጅ ጧት ማታ ፥
ይታየኛል ዝሊያው – ሥራ እንዲያ ሲወታ !
ወይም ወዝለል ትቶ – አንቀል ሲንገላታ !
ክቡር ሰው የነበር – በሕይወት ዝሏ ፥
በዳግም ልደቱ – ሲወጣው አህያ ፥
ምንኛ ይጨንቀው – ሲያራግፍ ፋንድያ !

ከሁሉም ከሁሉም – በጣም የሚያስጠላው ፥
ባህያ ባሕርይ – ደደብ መባሉ ነው ።

# ሰክራም አህያ?



እስከሆነም ድረስ — ፍጡሩን አህያ ፤
ከቶ ምን ያውቀዋል — ቢያራግፍ ቀንድያ !


እንደሰው ታይቶኝ ነው — እንደዚያ ማለቴ ፤
ክቡር ሰው ሲዋረድ — ነዶ ጨሰ አንጀቴ !

እምናለሁ እናንተ — ከዛሬ ጀምሮ ፤
እርግጥ ትዋዋችሁ — መሸታ ቤት ጋር ፤
አህያውን ሆኖ — ላለመኖር ኑሮ ።

ወሬሳና ቦርዴ — ሲጠጣ የኖረው ፤
ምን ሊሆን እንዲችል — ከቶ አልናገረው ፤
ሰዋንተ ልማዱም — ኑሮ ያንደባለለው !

የፔርና ሰካራም — የነበረ ሰውም ፤
ሲያሽታብተ ሊኖር ነው — ባህይት ኋላ ማንብ !

ሹሬ ሳይሆን ይቀር — እንዳንዱ አህያ ፤
ሰዋንተ ልማዱ — ከሌላው ወለያ ፤
አወድ ፍግ ፈልጎ — ካልጠፋ ማናፊያ ፤



ወብጥ በማረው ወዘዝ ፤ ክቡር የነበረው ሰው ተለውጦ
አህያይቱን ሊሆን ዕውብና ድንቅ የሚያሰኝ ተፈጥሮአዊ
ትንግርት አይደለምን?

መንደባለሉና — መታመም ፋንድያ !

እምቡዋና ጌሾን — ጠባይ መሰለያ ÷

እድርጎት የኖረው — አህያ መሳቢያ !

ታስታውሱ ይሆናል — ስካራም ያያችሁ ÷

የሚወድቅበትን — ሥፍራ ለይታችሁ ÷

እሠር ካለበት ነው — በየሠፈራችሁ ።

ለካስ ምልክት ነው — ለትንቢቱ ሕይወት ÷

ቀድሞ የከሠተው — ኋላ ላህያነት ።

የሣር የውቃቢ — ይመስል ግርንፉ ÷

ባፏጩበት ቁጥር — መንገድ ላይ ግርንፉ ።

ስንቱን ቢቅ ዘርዝሬ — እዘልቃለሁ እኔ ÷

በመሰከሩ ብቻ — አጋጥሞት ኩነኔ ÷

ሰው አህያ ሆኖ — ያየውን ብያኔ !

በሕይወት ያሉትን — ልዩ ልዩ አህዮች ÷

እትኩረን ብንመዝን — ባላቸው ጠባዮች ÷



ብዙ አይነቶች ናቸው — ቅይሮች ኩነቶች ።

ሁሉንም መግለጹ — ስለሚያበቸግረኝ ÷

ዝርዝሩን እናንተው — ይቻላል ብትረዱኝ ÷

ስለዚህ በዚሁ — ይበቃኛል በሉኝ !

ተጨማሪም ካለ — እናንተው አውሩኝ !!

በሌላ እንቀጽ ደግሞ — ተዘርዝሮ ያለው ÷

በዝሙት ምክንያት — ውሻ ስለሆነው ÷

የሚያሳዝን ዕድል — ስላጋጠመው ነው ።

በሕይወት ዘመኑ — ዘግናኝ የነበር ÷

ላገም ልደቱ ላይ — የሚወርሰው ፍሙር ÷

ውሻነት ነው እሱ — እኮ አያድርስ እግዜር !

ተራ ኩቲን ሆኖ — ዋው ዋው ብሎ ሊኖር !

ቆንጆ ናት እያለ — የኖረ ሲያሳድድ ÷

ዋጋው ውሻነት ነው — አይቻልኮ ነው ጉድ ÷

እንደሰው የሞተው — በላገም ሲወለድ ።

የግፍ ግፉ ደግሞ — ከሆነ ቤት ወኛ ÷

ጸጉሟ ላይ ሊያብድ ነው — ባይኖረው ግርከኛ !

እዘካችሁ ይብቃኝ — ሁሉንም እልዘከዝክ ÷
ወገን ግን ይሰማልኝ — እንዲያደርገው ዘልክ ÷
ሰው ሆኖ ባለ ወቅት — ሰሜት እንዳያወልክ ÷
በሕግና ሥርዓት — ይኑር አይፍረከረክ ÷
ወባለትን ይተው — ባለ በሰው ወድረክ !
አራት ነቢያትም — ይከው ነው ሲተረክ !

በሕይወቱ ዘመን — ዘራፊ የነበር ÷

ምን ሊሆን እንዲችል — ይወቀው በገቢር !

ፖለቲካ እያለ — ሲቸኸም የኖረው ÷
ከወሞቱ በፊት — ከዛሬው ይወቀው ÷
በዛገም ልደቱ — ግ እንደሚጠብቀው !

ጦጣንን ከሆነ — በዛገም ልደቱ ÷



ሲያስቀኝ ሊኖር ነው — ጠቅላላ ኩነቱ ÷

ለሥልጣን ሲሻኮት — ያለፈ ሕይወቱ !

እያድርስ አይቻል ነው — ያቺን ጦጣ ወሆን ÷
ከግንድ ከቅርንጫፍ — ሲዘሉ ወባከን ÷
ጥልተው እግይወርጉት — ያንን ሆድ ለማምከን !

እንዳንዴም ሲዘሉ — ተዘጥለ ሐረግ ÷

ወመዘር ያወጣል — ወይ ወጥት ያለወግ !

ምንኛ ጠንቅ ነው — የፖለቲከስ ጫጫ ÷
እኳል ሲያኩ ወኖር — ሆኖ ያችን ጦጣ ÷
በዛገም ልደት ወቅት — ያጋም ግንድ ሽምጠጣ !

ከከፋት በበተቀር — ልቡ እግያስብ ÷

ጎሊናው የጦዘ — በፅኩይ የሚከለብ ÷

ሲኖር በዚህ ዓለም — ተንኮል ነገር ሲያደልብ ÷

ከሞተ በኋላ — ቀልቡ ተለወጣ ÷

ፅባብ ትሆን ይሆን — ወርቃማ ሞት አምጣ !

ለክፋት ሕይወቱ — ለፅኩይ ፅሴቱ ፥
ፅባብነት ሆኖ — ቁጣጣዊ ልደቱ ፥
ሲንፏፏቀቅ ሊኖራት — በግር የለሽ ደረቱ ፥
ወኸ ዉዛ ሊልስ — ባይረካ እንጀቱ !

እንደሰው የኖረው — ሆኖ አሳባቂ ፥
በቀቀኗን ሊሆን — የወሬ ሰባቂ !

እንደሰው የኖረው — ያ ጄለስ ምቀኛ ፥
ቀበሮዋን ሊሆን — ሲወለድ ዳግመኛ !

እንደሰው የኖረው — ሲያጋብስ ሲያጋምም ፥
አያ ጅቦን ሊሆን — የማይጠግብ ልክስክስ !

ከሞተ በኋላ — ስንቱ እሚሆነውን ፥
መዘርዘር አልችልም — በዚህ ይብቃኝ አሁን ።

እያንዳንዱ ሁሉም — የሠራው ምግባሩ ፥



ምን እንደሚያደርገው — ይወቀው ነው ጌሩ !

ይህን መምሪያ አድርጎ — ሁሉንም መተርጎም ፥
በምግባሩ አንፃር — አስቸጋሪ አይሆንም ።

የምትሠራውን ግብር — ሁልህ ስለምታውቅ ፥
ምን እንደምትሆን — ራስህን ጠይቅ !

ምን አይነት ባሕርይ — ምን አይነትስ ምግባር ፥
ድኀረ ሞት ወሳኙ — ቅድመ ልደት ሲኖር ፥
ለማድረግ የሚያስችል — እያንዳንዱን ፍጡር ፥
ቁንጫና ትኋን — ቅማል ወይም አነር ፥
አይጥና ትንኝ — ፀንቁራሪት ብሆር ፥
ወዘተ ወዘተ — እድራጊው ሲቀየር ፥
የቱ ጠባይና — የትኛውስ ተግባር ፥
መሆኑን ገምቱ — በያንዳንዱ ግንባር ፥
በሕይወት የሠራው — ሰው ልጅ ባለም ሲኖር !

በሌላኛው እንቀጽ — ዳግም ልደት ሲያትት ፥

ለሕይወት ተግባር — ዋጋ እንዲሆን ቅጣት ፤
ዓታም ይቀይራል — በዳግመኛው ልደት ።

ወንድ ሆኖ የኖረው — ወሲብ ሲያደበድቡ ፤
ሴት ይሆናል ይላል — ባዲስ ልደት ወደዚ ፤
በተራው እንደሴት — ሊፀንስና ሊያረግዝ ፤
ሊቀምሳት ጣጣውን — የሴትን ችግር ጓዝ !

በጎ ምግባር ሠርቶ — ያወረተ ጠባይ ፤
በዳግም ልደቱ — ይኖራል ክብር ላይ ፤
ምንጊዜም ቢወለድ — ዳግግይ ግልባይ ፤
ፍጥረቱን ሳይቀይር — ሌላም ሥቃይ ሳያይ ፤
ብፁዕ ሰው ነውና — ባላየው ባሕርይ ፤
ስለዚህ ስለሱ — አልኝም መተንበይ !

ፅኩይ ግብር የሠራ — ሁሉም በየግሉ ፤
ሲሞት ይቀምሳታል — መከራን በሙሉ ፤
በቁራንም ሆነ — ወይም በወንጌሉ ፤



እንደተነገረው — በሃይማኖት ሁሉ ፤
እንደምሥራቆችም — የዚህ ዋጋ ውሉ ፤
ፍርድን ያቀዳጃል — ሁሉም በየክፍሉ ፤
በግትምተው ነፍሱ — ሌላ ሆኖ አካሉ ።

የክርስቲያን ምርጫው — ከሁለት አይዘልም ፤
እኔም ያለሁበት — ያባት ያያት ቅርስም ፤
ወንገሥተ ሰማያት — አለያም ገሐነም ፤
ከገሊው ከአል ውጭ — ምንጊዜም አይወጣም ።

ምናልባት ነጸወት — የኔ ያገሬ ሰው ፤
ተጠምቶ እንደሆነ — ውሻ በሚያደርው ፤
በምሥራቁ ዕምነት — እስያ ውስጥ ባለው ፤
እንዲት ቃል አለችኝ — ለሱ የምነግረው ።
እግዜር አደራውን — አህያ አያርግህ ፤
ስትጣን እንዳትኖር — በዳግም ልደትህ !!!

# ነሽ አሉ፣ ነሽ ወይ?

# ነህ አሉ፣ ነህ ወይ?



ሺ ባ — Shiva

እንደሺባ አካል — አራት እጅ ቢኖርሽ ፥
እንደሕንድያኑ — ሁሉ ባመለክሽ ፥
እንቺ ግን ባካልሽ — ተራ ሰው ስለሆንሽ ፥
አትወግደቂ — ግንም አይመገድልሽ !!

# መዘክርነቷ

ምግታሬዊ

አንዳንድ አንጎላቸው የመዘባቸው ፉዞ ሰዎች ፣ ግለ ራሳቸውን ከሌላው ሰው የተለዩና የሚበልጡም በማስመሰል፥ ክቡሩን የሰው ልጅ መሠረታዊ እኩልነትና የአንድነት ልዕ ልና ለሚፃረሩ ኢሰብዓውያን ሁሉ የቀረበ ርቱዕ ምግታር ።



# ነሽ አሉ
# ነሽ ወይ?

# ነህ አሉ
# ነህ ወይ?

ዳይኖሰርስ ሲጠፉ — ሌዋታን ብሔሞት ፥
ደገኛ የሚያህሉት — የጥንቱ ፍጥረታት ፥

ዕድሜያቸውን ቆጥረው — ካለው ሲጠፉ ፥
የተካቸው ሰው ነው — ትንሹ ሙንፉ ፥
ይላሉ ሊቃውንት — መርምረው ያለፉ ።

ሁለት አይኖች ያሉት — በግንባሩ መሐል ፥
ወንቶች እግርና እጅ — ደግሞም ምግን አካል ፥

ነገሩን ወግኒያ — አንድ አፍንጫ ያለው ፥
ድምፅ እግሰግዐት — ጆሮ ከናንቴናው ፥

መሰል ነው የሰው ልጅ — ትክክል በተራ፥
በደምና ባጥንት — ታንፆ የተሠራ ፥
አንዱ ካንዱ እማይበልጥ — ከአንዱ ጋራ ፥
አፋስካም ካምቻትካም — የትም ምድር ቢዘራ !

አካባቢውና — ኑሮም ቢለየው ፥
የሰው ልጅ መሰል ነው — ቦታ የሌለው ።

ያካባቢ ባሕል — ባይነት ቢለያይም ፥
የሰው ልጅ ዋሕድ ነው — በተፈጥሮው አቋም ።

ቢረዝምና ቢያጥር — ቢቀላና ቢጠቁር ፥
ጂንስና ሆርሞን ነው — ወይ ያለበት አድባር ፥
ውቅቱ ምግብናው — የያለበት ሀገር ፥
የለየው መሆኑን — በጥናት ምርምር ፥
የጄኔቲክስ ጠበብት — ተናግረዋል በምር ፥



ወነቸው ምክንያት — ለልዩነት ምንዝር ፥
እንዴው ለደንብ ያህል — መዘፋለቅ ቢኖር ።

አለበለዚያ ግን — ሁሉ ሰው እኩል ነው ፥
ባጥንቶች ተዋቅሮ — ሥጋን ለብሶ ያለው !!

ግንም ከግን እያነሰ — ቢቆጠር ጆግቱ ፥
ግነው ከግን የሚያንስ — ቢወዘዝ እንጀቱ፥
የትኛውስ ይሆን — ብሬት ጭንቅላቱ !
ግግሽ አካሉ ሰው — ነብርግ ያ ፊቱ !
መሰል ማኅተም ነው — ሰው ልጅ በፍጥረቱ ።

ለመሰልነቱ — ስንፈጥር ጥርጥር ፥
አርገን እናያለን — ክንፍ እንዳለው ፍጡር ፥
ቀለም እንሰጣለን — ብለን ነጭ ጥቁር ፥
ወይም የቢሆና — የሌላው አይነት ዘር ፥
ከበርባርስ ያለ — የማይኖርም በምድር ፥
ከንቱ ተረብ ወሬ — ጎሊናን አደናግር !

# ነሽ አሉ ፣ ነሽ ወይ?

ያሉትን ይበሉ — ግን እሚቀበለው ፥
አይናገርም በጥራሽ — እስከመጨረሻው ፥
ሁሉም ያውቃልና — ሐቁን በውነታው ፥
መሰሉ የሰው ልጅ — ነባቢት ነፍስ ያለው ፥
እኩል እንደሆነ — መሰል በተፈጥሮው !

ሂዩማን ራሱ — ዘሩ እንኳ ሲቆጠር ፥
አንድ ብቻ ነው — ሁሌም ቢዘረዘር ።

ላይናገርበ ቢንቁ — ሌላ ታናሽ ፍጡር ፥
ምክንያት አላቸው — የማያደራድር ።

ረቢ ሠገደ — በመንፈቀ ሌሊት ፥
ለሌላው ረቢ — እያለ ቢጸጋት ፥
ያገር ባለቅኔ — ቢሰጥ አስተያየት ፥
ባቶችን ጠቅሶ እንጂ — ያበላለጠበት ፥
እንዳለው ግን ያውቃል — ሰው ልጅ እኩልነት ፥
የአቢን አልሰጠም — ለሦሕላን ፍጥረት ።



# ነህ አሉ ፣ ነህ ወይ ?

ይህ እንዲህ ከሆነ — መሠረታዊው ሐቅ ፥
ልዩ ነን ባዮችን — ይስው እስቲ ልጠይቅ ።

የጥያቄዬ ቢቅ — አይከብድም ነው ቀላል ፥
ነሽ አሉ ነሽ ወይ — ብሎ ይጠይቃል !
ልዩነቱ ቦታው — ምን እንደሁ ያበርታል !
በሥላቅ በምፀት — ሲጀመር ያሥቃል !!


ኩኩዬ ነህ አሉ — ኩኩዬ ነህ ወይ
ከሰው የተለየ — ቀንድ ያለህ ከላይ !

ሌሰቢያ ነሽ አሉ — ሌሰቢያ ነሽ ወይ
ወተች ያነጠነጥሽ — ከባቶችሽ ላይ !

አንቺዬ የየት ነሽ — ብዬ ብጠይቃት ፥
የጁዬ ነኝ አለች — የልግድ ሆኖባት !

አንተዬስ ግን ትሆን — ብዬ ብጠይቀው ፥
ጅሩዬ ነኝ አለኝ — ቋንቋ እንደሁ ሳያውቀው !

## ግማሽ ሰው – kentaur



እንደግሪኩ ብትሆን – ግማሽ ሰው ኬንታውር ፥
በልዩ ተፈጥሮህ – ባመለክሁህ ነበር ።
አንተ ግን እንደኔው – ሙሉ ሁለንተናህ ፥
ተራ ሰው ነህና – በተፈጥሮ ቅርፅህ ፥
ጭራሽ አይገባኝም – አምልከኝ ማለትህ !!



## ነሽ አሉ፣ ነሽ ወይ?

ሰዎች ነን የሚል ወለሰ – ቢሰጡን ኖሮ ፥
ምንኛ በዓወኝ – ወለሳቸው ግር ሆና !
በሰውነት ያለን – ትልቁን ሐቅ ትተን ፥
በዝርዝር ልዩነት – እንግቅታለን ፥
ምን መግቀቅ ብቻ – ልናም እንነሳለን !

ታሪያ እስቲ ልጠይቅ – ሁሉንም በተራ ፥
ወለሰ እምቢ ባይሆን – እምባ እየጠራ !

እግራ ነህ አሉ – እግራ ነህ ወይ ፥
ከሰው የተለየ – ያለህ ባሕርይ ፥
ካናም ተፈጥሮ ውጭ – ያካበትህ ጠባይ !

ያንኪዬ ነሽ አሉ – ያንኪቱ ነሽ ወይ ፥
ከሌላው የሰው ዘር – ፍፁም የማትወሰይ !

ወላሞ ነህ አሉ – ወላሞ ነህ ወይ
በልዩ ተአምር – ጠብ ያልክ ከሰማይ !
ከሰው ተለይተህ – ያለህ ዓይን ጭን ላይ !

ኩናማ ነህ አሉ – ኩናማ ነህ ወይ
እንትንህ ግምባር ላይ – ተተክሎ እሚታይ !

ቆረቴ ነሽ አሉ – ቆረቴ ነሽ ወይ
ሰሉም ዓይኖች ያሉሽ – ከግንባርሽ ላይ !

ነጃግ ይሉሃል – ነጃግ ነህ ወይ
ጀርባህ ጥሩ ያለው – ዝንቦችን ከልካይ !
ከሰው ተለይተህ – አውሬውን መሳይ !

ጉዴላ ነህ አሉ – ጉዴላ ነህ ወይ
ሌላው ሰው የሚያይህ – እንደ ሰው ገዳይ
ሰው እሚያተኩረው – አንተን አንተን ሲያይ !
ጎንደሬት ነሽ አሉ – ጎንደሬት ነሽ ወይ
ያጥንትሽ ኬሚካል – ካጥንት የሚለይ !

ጉራጌ ነህ አሉ – ጉራጌ ነህ ወይ
ከንፉግ ሰው የሆንክ – ከሌላ የሚለይ !
ገራጂቷ ቀልብህ – የሚያከንፍ ሰጋይ !



ትግሬ ነኝ ትላለህ – ትግሬያዊ ነህ ወይ
ከጠቅላላው ሰው ልጅ – ያለህ የሚለይ !
ባለ ሐምራዊ ደም – ያይደለ ተራ ቀይ !

ወዘተ ወዘተ – ሁሉን ይጠይቃል ፤
እኔ ከሌላው ሰው – አይደለሁም መሰል ፤
እያለ በድፍረት – አይደለሁም እኩል ፤
የሚደነቁትን – ዕብሪተኛ ክፍል ።

ያን መሰል ጥያቄ – መጠየቅ ይቻላል ፤
እንጥር ለማምረት – ሐቁን የሰው እውል ።

የዚህ ሁሉ ብሒል – አንድ ማስሬያው ልጥ ፤
ለማለት ይቻላል – ሰው ከሰውም አይበልጥ ፤
እኩል በተፈጠረው – የትም ምድር ቢቆጥ ።

ቆላ ይኑር ደጋ – ጂ ቋንቋ ይናገር ፤
ባሕሉና ልምዱ – ይሁን ልዩ ቅይር ፤
እንደሰውነቱ – መብቱ ነው ለመኖር ፤

ሰብፅናው ተከብሮ – ምንም ሳይደፈር ፥
ሁሉ በየፊናው – በለሆነ ክብር ፥
እኩልና መሰል – ነውና ሲፈጠር !

እንዴው ቋንቋ እንጅ – ድምፆች እያጋጨ ፥
ከወንዙ ከነፋው – ሰብስቦ እየረጨ ፥
ሰውን ልጅ ከሰው ጋር – በማገባር አጋጨ ።

ሰው ግን በተፈጥሮው – ሁሉ ሰው እኩል ነው ፥
እንዱ ከሌላው ጋር – ሲተያይ ተፈጥሮው ፥
የተለየ አጥንት – ደም አካል የሌለው !

በርግጥ አይመስለኝም – ልዩ አካል የሚኖር ፥
ባለሦስት አፍንጫ – ባለስድስት እግር ፥
ጆሮው ደረቱ ላይ – እትም ብብቱ ስር ፥
የተለበጠለት – በልዩ ተዓምር ፥
አይመስለኝም ያለ – በሰው አፈጣጠር ፥
ሁሉ ሰው መሰል ነው – በቅርፆቹ እንኳር ።



በገንዘብ በዕውቀት – ሰው ባይስተካከል ፥
የኑሮ ፈርጅ እንጅ – ማን ከማን ይበልጣል !
በተፈጥሮ እኩል ነው – የሰው ልጅ በአካል ።

ባይኖ በድመቱ – ይኩራ እንጅ የሰው ልጅ ፥
በግና ፍየሉን – ይናቅ እንጅ የሰው ልጅ ፥
ገዛ መሰሉን ሰው – ቢያቃልል ወይ ቢያፋጅ ፥
ትዝብት እንጂ ትርፉ – ከቶ ምንም አይበጅ !

ሰው መሰሉን ፍጡር – ቢንቀው በመንፈስ ፥
ቅሌት እንጅ ትርፉ – ከምንም አያደርስ ።

እንድ ወይ ፍጡር – ቀንድ አልባው ጭራ አልባው
ተከባብሮ መኖር – ሰው ለሰው ሲገባው ፥
እኔን አይገባኝም – መናቁ ምነው !

ሁለ ነው ጠይብ ነው – የሚሉት ርችት ፥
ስንቱን ወገን ጠብሷል – መርዶት በስሜት !

የዘር አስተሳሰብ – መዘረር አለበት ፥

እንገላቷልና – የሰው ክብር በመንካት !

ማንም ከማን እያነሰ – ቢቆጠር እኖንቱ ፥
ብዙም አይደል ብልጫው – ቢለካ እንጀቱ ፥
እንዱን ሰው ሌላው ሰው – በልዩ በማቱ ፥
ምንም ፋይዳ የለው – ቢንቀው በከንቱ ፥
እኩያው ነውና – በሥነ ፍጥረቱ !

መሰሉ የሰው ልጅ – ነባቢት ነፍስ ያለው ፥
ሁሉም በተፈጥሮው – ትክክል እኩል ነው ።

ሊያማን ራስ ነው – ዘሩ እንኳ ቢቆጠር ፥
በመዝገበ ፍጥረት – ቀዳማዩ ቁጥር ፥
ከዕልፍ አዕዋፋት – ፈጡራኖች ድርድር ።

በክቡር ሰው እንግር – ብናነፃፅረው ፥
ባሕልና ልማድ – ያምባዎች ምርት ነው ፥
የዕድሜ ቆይታ – አካብቶ ያስገኘው ፥
በምንም አይበልጥም – ከክቡር ታላቅ ሰው ።



ቋንቋም ቢሆን ዛሬ – ተራ ሳይገለ ነው ፥
ባጭር ኢንቴንሲቭ ኮርስ – ግምንት የሚሰጠው ፥
ለማጥናት ለማወቅ – ብዙ ዘዴ ያለው ።

ትልቁን ክቡር ሰው ፥ ቁንጽል ልዩነቶች ፥
ማዋረድ አይችሉም – ዕብሪት ቢያብጥ ቢያሰለች
ማናጋትም አይችል – የኩልነት መብቶች ፥
በሰውነቱ እንግር – ናቸውና ሊምንቶች !!

ስለዚህ ጥያቄው – ትክክል ነው በርግጥ ፥
መሆኑን ያሳያል – ሰው ከሰው የማይበልጥ ፥
በተፈጥሮው መሰል – በውጭ ሆነ በውስጥ !!

ነሽ አሉ ነሽ ወይ – ነህ አሉ ነህ ወይ ፥
ሆናችሁ ያላችሁ – የልማድ ሲሳይ ፥
ከክቡር ሰው ይልቅ – ለባሕል እውደላዳይ !

ሁሉን እንተውና – ዕንቶ ፈንቶ ነገር ፥
በሰው እኩልነት – ተባብረን እንኑር !!!

* * *

# ድመቶች ሲያሾፉ!




ድመቶች ሲያሾፉ — አይጦች ተጠበው ፤
ከዕውቀታቸው ብዛት — ከድመቶች አልፈው ፤
ሰው እናድን አሉ — ዶክተር ሐኪም ሆነው ።

ፍንደታ — ቁ 94

# መዘክርነቷ

የብሔሯንን ክብረ ልዕልና በመናቅና በማቃለል አን ንድ ብልጣብልጥ ገለ ሰዎችና ጥቅም ያመጣኛቸው ወድናች የራሳቸውን ጥቅማጥ ጥንት እያለው በመግን ላይ ባሉበት ወቅት ፥ ሕጋዊ የዋኒቷ ባለቤት የሆነው ብሔሯት ሕዝብ የግኒ ተወልካች ሆና በመገኘቱ ፥ ደህች ግጥም ላስገራሚ ታጋሽነቱ ፥ ለራሱ በእርምጥ ላለው ብሔሯን ሕዝብ ነው ።




መምህሩ ተፈጥሮ — የሰው ፕሮፌሰር ፤
ስንት አለው ፎርሙላ — የሚያስተምረው ታምር ።

ስንት አለው ትምህርት — የሚያስጠናው ጥበብ ፤
ካንጀት ከቀረቡት — የሰው ልጆች ከልብ ።

ያስተምራል ተፈጥሮ — ሁሉን በየዘርፉ ፤
ተከታይ ካገኘ — ሐቅ የሚደግፉ ።

ከተፈጥሮ ትምህርት – ከጥበቡ ማዕድ ፤
እንዳንዱን ልጠቃቅስ – ብዙም ሳልቀላምድ ።

እነዋድ ገለባ – ልባቸው ተነፍቶ ፤
ከእሳት ቢጠጉ – ወኔያቸው ደንፍቶ ፤
ውበቱን ያስተምራል – ተፈጥሮ ተዝናንቶ ።

ያራል ይቃጠላል – ይከስላል ይከስማል ፤
ባለው ልዩ አቅሙ – ሌላ ምን ይሆናል ፤
ጭድ ከእሳት ቢጋባ – ውበቱን ያውቀዋል ፤
ወምከን ብቻ ሳይሆን – አልፀነት ያወርታል ፤
ይህን የጋድ መሆን – ተፈጥሮ ያስተምራል ።

ጆሮ ዳባ ልበስ – ብሎ ጭድ እጆሬ ፤
እሳትን ቢነጅስ – ቢለክፍም እንዳውሬ ፤
ካሳሉ ያገኛል – የውበቱን ፍሬ ።

ከዚህ የበለጠ – ተፈጥሮ ምን ያስተምር ፤
ምድሪቱን ተማምና – በርሷ ላይ ለሚኖር ፤
ሕግና ሥርዓቷን – ማክበር ለሚሞክር ።



በራሱ የሚያፌዝ – ነብርና አንበሳ ፤
ከስሩ ያገኛል – መከራና አበሳ ።

በራሱ እሚቀልድ – አንበሳና ነብር ፤
ካቅራቢያው ይማራል – የድቀቱን ምሥጢር ።

ውሻ ቢያስፈራራው – ፈሪኛን አንበሳ ፤
ምን ያስደንቀናል – እስከሆነ ሬሳ !
አጋድሞ ቢግጠው – ከጆሮው ቢያገሳ !

አነር ቢያስፈራራው – የለገመን ነብር ፤
ምን ያስደንቅ ከቶ – እስከሆነ ዕውር ፤
ግዳቱ ተስኖት – ሲሸናበት አነር !!

ፍየል ጥፍር አግኝቶ – ነብርን ቢቧጥጥ ፤
ምን ያስደንቀናል – እንዲህ ያለው በርግጥ ፤
ጥፍረኛው ተኝቶ – በቅዠት ሲማግጥ ፤
በሀልሙም እስካለ – ሌሎችን ሲያግርጥ ፤
ራዕይ አጥቶት – በምትጠት ሲያፋግጥ !!

አጅሬ እያ ቫዮን — ብትረግጠው አሀይት ፥
ምን ያስደንቀናል — ብትለጋው ሰማያት ፥
ወይም ብታጉነው — እንጦርጦስ አዘቅት !

ያንቀላፉን ጉንዳን — ትኋን ብትቆነጥጥ ፥
እንቴናውን ነክሳ — ሞጁ ብታስረግጥ ፥
አረ እንዴት ይደንቃል — ያስገርምስ በርግጥ !

እጇሬትን ጥንቸል — ኤሊ ብትቀድማት ፥
ማነው የሚደነቅ — በጥንቸሏ ልግመት !

በሆነው መሆን ላይ — ፍጥረቱ ሲያላግጥ ፥
ተዓራፊው ሁሉ — ደርሶ ነፍሱን ቢግጥ ፥
ማስገረም አይችልም — ወይም ሊያስደነግጥ ፥
ደግሞም ማበሳጨት — ሊያስተያይ የነፊጥ ፥
ራሱ ፈግፍን — ባስገኘው እረወጥ ፥
ራሱ በራሱ — ቢታጠል ወይ ቢፈርጥ ፥
ከቶ አያስደንቅም — ነብቶ ቢግቅቅ ግጥ !
ተነትሮ ያለ — ለዘመናት ሽቅብ ፥

ድመቶች ሲያሾፉ!


ድንገት ተደርብቶ — ተራራና ያ ግንብ ፥

ማንን ሊያስደንቅ ነው — ቢናድ ከራሱ ላይ ፥
ራሱን ጠብቆ — ካልኖረ ሰው ነኝ ባይ !
ካልተከላከለ — ዶፍ ሲወርድ ከሰማይ !
ማን ሊደርስለት ነው — ቢፀክ አደባባይ ፥
ራሱ በራሱ — ካልነተረ ሞቃይ !

ቁልቁለት ፈልጎ — የሚፈሰው ጅረት ፥
ወደላይ እቅንቶ — ፏፏቴውን ማያት ፥
ማዕበሉ ፈልቶ — ባያስበው ድንገት ፥
ባልሞተው ነፍሱ ላይ — ቢጥለቀለቅበት ፥
ዘማን ሊያወካኝ ነው — የጥሐኑ ፍጥረት ፥
የኛ ተንዘባናኝ — ወገን ሕዝብ የሚሉት !

ሰደድ እሳት ግዞ — ካለበት ቢያጋየው ፥
ባለ እጁን ተቀምጦ — ኡ ኡ ቢል በዋይታው ፥
እራታውን ቢያቀልጥ — ማን ሊደርስለት ነው !

ምንም ሳይዘጋጅ – ተዘርሮ ያለው !!

እውሱ ነፍስ ወጥቶ – ጠራርጎ ቢያጠፋው ÷
ዶጋመድ ቢያረገው – ብናኝ ትቢያ ያን ሰው ÷
እረ ከቶ ምን ሊል – በግን ሊያወሻኝ ነው !
ያላንዳች ዝግጅት – ተፈንግሎ ያለው !
በሞግዚር ቢነሳው – በፈንጂ ቢያመዘው ÷
እንደድርና ማግ – ሸራርቦ ቢፈትለው ÷
በካራ ቢወትረው – በጎራዴም ቢያርደው ÷
እረ ምን ሊል ይሆን – ብትን ነጠላው ÷

ወይም ድምፁ ሕዝብ – እርምጥ የጠጠው ÷
እላንዳች ዝግጅት – ጥበቃ ሳይኖረው ÷
ለዘመናት ፅድግ – ተኝቶ የኖረው !
እጆቹን አጣጥፎ – ሲያሾፍ የነበረው !

ዘወን ውሴ አይደል – በሉላ ባሕር አይከፍት ÷
ወይም እንደላሚት – ነልያድን ጠላት ÷
ወንጭፍ እላበጀ – በሩቅ የሚያሽበት ÷



ወንጅ እላደበረ – የሳምሶን አይነት ÷
አፀግደ ኢሎፍሊን – ነጥቶ የሚለበት ÷
ዘወን ተነምር – አልፏል ድር በቸንት ÷
ዛሬ የሚያጥቃው – የገዛ ራስ ጥረት ÷
እንደሆነ ታውቋል – ባያሌ ሊታወንት !

ታዲያ ለምንድነው – ንልበት ያላበጀ ÷
ባንድነት ተባብሮ – ኃይል ያላደራጀ !

ከላይ ካናቱ ላይ – ናላ ቢሰቅለት ÷
የባሩዱን ዝናብ – በገፍ ቢያወርድበት ÷
ጥይት ነገር እቅርቦ – ባቱ ቢያነርበበት ÷
ጋዝ ጠላ በጥብጦ – ቢግተው በንልበት ÷
ግን ሊርበለት ነው – በወከራው ሰንት ÷
ወላጅ አላበጀ – በርላታ እሚወክት ÷
ወይ ራሱ አልሠራ – ወላኛ ከወነት !

ግንን ድረስ ሊል ነው – ለርላታ ለወጥኝ ÷

ተኝቶ የኖረ — ሕልም ያላለ በታኝ !

ማጥቂያው እንኳ ቀርቶ — ለመከላከያ ፥
ያስፈልገው ነበር — ሕዝባዊ መገሬያ !

በመከራው ሰዓት — መሆኛው መገኛታ ፥
ጥበብ ያጥቀረው — ውስጣዊ መከታ ፥
ሊኖረው ይገባል — ለሕይወቱ አለኝታ !

እንዴት አይማርም — ሰው ልጅ ከተፈጥሮ ፥
የሚሰጠውን ሐቅ — ሌላም ተመክሮ ፥
ጥበቡን ምርኮቱን — ፀጋውን ዉምር !
ለክፉ ቀናቹ — ግለፊያ አፀምሮ ፥
ድልድይ እንዲሆነው — ሊያኖረው አሻግር !

ከቶ ምን ይገርማል — ያልተዘጋጀን ኃይል ፥
ዶጋወድ ቢያደርገው — ትንታግ ትንባት ከፍል !

ጥጥ ያለው ብዙኃን — አርምጥ የጥጠው ፥



ገለል ብሎ በሩቅ — ትንግርቶች የሚያየው ፥
ጃ ጊዜ ታዝዞ — ተዝብት ያልጠገበው ፥
ወንቶች ሲናጡ — ተወልካች የስተኛው ፥
ምን ቅጠል ነክቶት ነው — አረ እንዲያ ያስቻለው፥
ለዘመናት ፅናግ — ከፋር ቶጥ ያለው !!

እንደ ሊጥ አብኩቶ — ኩፍ እስኪል ጠብቆ ፥
በርጃና በሐሪፅ — አቅጥና ደባልቆ ፥
ከጋለ ምጣድ ላይ — ዘርር አድርቶ ፥

በስተመጨረሻ — ልዩነሀ ነው ቢለው ፥
ከቶ ለወታወም — ምንስ አቅም አለው ፥
ሉቆት ላይሆን በፊት — ነበር እንጅ አምቢታው፥
በላኔ ስብግ — ጋግርት ወቸ ሊለቀው !

በሕይወቱ ምርገው — ነፍሱን ሲያጥከፉት ፥
ኮርን አወግቅለው — ወላ ቅጥ ሲያላፉት ፥
የለሕላዊን ኩነት — ወቅናቢስ ሲያደርጉት ፥

እንዲያብድ እንዲቃወስ — አንዳንድ ሲያጥክዉት ፤
አረ ምን ነክቶት ነው — ጭጭ ፀጥ ያለበት ፤
ብዙኃኑ ክፍል — ያገር ሕዝብ ደግሚት ፤
ሞቱን ባይኑ እያየ — በአርምሞ እሚሞት !!

ጥቁር አዝሙድ ቁንዶ — ደግሞም ኮረሪማ ፤
ዝንጅብል በርበሬ —አሞሌ ጨው ሽንኩርት ፤
ሲወገብ የኖረን — ሲያግስል ያንን ድስት ፤
የደላውም ቅቤ — ያልተወቸው በይት ፤
ሲጠጣ የኖረ — የድስቱን ባላባት ፤
ያንን ማግሰያ — ወቅጣ በዱላነት ፤
ይዛ ብትወጣ — በሙሉ ልብ ድፍረት ፤
ታንክ አይወክታትም — እንኳን ተራ ጥይት !
መብቷን ለማስከበር — ብትነሳ እናት !!

ዕርፍና ጆሯትን — ቢታጠቅ ገበሬ ፤
እምዬ ቢነሳ — ነገ ሳይል ዛሬ ፤
መደደም ይችላል — እንኳን ሰው ከቶ አውሬ !

ነጋዴው ሚዙን – ካህኑም መስቀሉን ፣
ባለሙያው ሁሉ – ልዩ መግሬያውን ፣
እየያዘ ቢያምፅ – ቢያግርም ሥራውን ፣
ማንበርከክ ይችላል – እፑኪ ጠላቱን !!

ብዙኃኑ ወገን – ከሞጠው እርምጃ ፣
ያልታል በየተራ – ሳያልፍ የሞት ፅድም !

ድመቶች ሲያሾፉ – የሚለው ምሳሌ ፣
ለብዙኃኑ ነው – እንዳይቀርበው ቶሌ ፣
ንፃሬ በመስጠት – ለማስጠንቀቅ ሁሌ ።

ሌላው ሌላው ቀርቶ – ስቱሬው ትምህርት ፣
ወርቃ ወርቁ ምክር – አለማዊው ዕውቀት ፣
ጥበቡ ተመክሮ – ደረቁ ዕውነት ፣
ተፈጥሮ ሊቅ መምህር – ከሰጠን አብነት ፣
የነውር ታሪክ – ልዩ ናሙናነት ፣
ይበቃል ይችላል – ሊሆን ማስረጃነት ።

የውስጥ ችግሮችን – አድርጎ መከታ ፣



በቱማታው መሐል – ለሚጠቀም ቦታ ፣
ትርምስ ግርግርታን – አድርጎ ከለላታ ፣
ባገኘው ልዩ ዕድል – ሕዝቡን ሊያንገላታ ፣
ኃያላን ይዞ – በወገኑ ፋንታ ፣
ንፁሐን ወገን – ድባቅ ለሚመታ ፣
ማሳያ ይሆናል – ተንኮሉን ባንዳፍታ !

ለሚያሾፈው ወገን – አብነት ይሆናል ፣
የሚያስከትለውን – ጉዳቱን ያሳያል ፣
ፊንጠር ብሎ መሳቅ – ምንኛ እንዲበድል ፣
ወይም ንቆ ማየት – ትንንሹን አካል ።

ታሪኩ እንዲህ ነው – ሳያጥር ሳይረዝም ፣
በድመት ጀምሮ – ባይጥ የሚፈጸም !

በሆነ ምክንያት – ድመቶች ተናደው ፣
አኩርፈው ነበረ – ጠቃሚ መስሏቸው ፣
ነፅብ ቀንፅል የሚል – በሽታ ለክፋቸው ።

ለንዴት መጣ - የዘየዱት መላ ፥
ግዙፍ ነበር አንዱ - የተግባር በደላ ፥
ፈንጠር ብሎ በሩቅ - ወምስል ዋኘ ተላላ !

የድመትን ግዙፍ - አይጦች ተረድተው ፥
ያላ ኃይላቸውን - ከወዲያ አሰባስበው ፥
ያለምንም ስጋት - ገቡ ከዘረፋው ፥
ግርገጃ ጓዳውን - ያለ ፍርሀት ወረው !

በጥቂት ቀናቶች - ደቂቃ ሳያርፉ ፥
ጥራጥሬ ዘርን - ታቅመው አጠፉ ፥
ያስቸገራቸውን - ጥረው አፈሰሱ ።

ይህ እንኳ ብቻውን - ይበቃቸው ነበር ፥
አልፈው ተርፈው ሄዱ - ሥጋ ለማባረር ።

እጅግ የሚደንቀው - በሥጋው ወረራ ፥
እኩር በተኛው - በቤያ በቀብሬራ ፥
በራሱ በድመት - መሆኑ ነበረ !



ከድመት ቁጥጥር - ነፃ የወጣ አይጥ ፥
ያገኘታ ገባ - ብሎ አላስቀምጥ ፥
እለም አላስገባ - አላስተኛ አላስርጥ ፥
አላሠራ አላሥቅ - ደግሞም አላስቀምጥ ።

በድመት ማኅለብ - ነፃ ወጣሁ ብሎ ፥
ምድረ አይጥ አበደ - ጉድጓድ ቤቱን ጥሎ !

ከድፍረቱ ብዛት - አይጥ ልብ አግኝቶ ፥
ከጥራ ጥሬ እህል - አልፎ ሄዶ ገብቶ ፥
ከቤት ከማጀት ውስጥ - ዘሎ ተንሠራፍቶ ፥
ጆሮ ይቆርጥ ጀመር - ያለውን ተኝቶ ።

የድመትን ጥፍር - ቶሎጥ መጋዝነት ፥
ለጊዜውም ቢሆን - ለሚገኝበት ወቅት ፥
ከነመፈጠሩም - በጥራሽ ዘንጉት ፥
ያሸለበው ድመት - ታቅፎ ቢተኛበት !

ድመቶች ቢተኙ - በሚሞቅ ጋቢ ውስጥ ፥

ቀዘኛ አይጥ ሁሉ — ገባ ምንም ሳይጠርጥ ፥
የሚያንቀሳቅሰውን — ጆሮ ሊቆራርጥ !

ጆሮዎች ቆርጦ እንኳ — ቢተው ነበር ወልክም ፥
ካካል ውስጥ ገባ እንጂ — አጥንት ሊቆረጥም ፥
በጣውኝ ደገውኝ — ወወሬያ ሕግ ደንብ !

የቆረጠውን — አጥንቶች ሲቆጥር ፥
ከዚ አድርሶታል — ነደና አውቀ አይጥ ደፋር !

ጆሮዎች ወምጠው — ያረካው በነበር ፥
አጥንቶች ሰብስቦ — የወቁጠሩ ምሥወር ፥
ፍቺውን ለማውቅ — ሊጥጁል ታላቅ ችግር !
በዘወናት ሁሉ — ያልታየ ተዓምር !

አይጥ በድመት ላይ — ያስከተለው ጣጣ ፥
የሀ ነበር ባጭሩ — ተጧጦ ሲወጣ !
እንቅልፍ የፈጠረው — ሱብ ፅዳ ባላንጣ !



ባለንበት ዓለም — ምስየው ግንሩ፥
እዚያም እዚህ ምድር — በሕይወት ሲኖሩ ፥
ምኒም ሕዝቦች ናቸው — ክብሩና አድባሩ ።

በተፈጥሮ ግዛጅ — ቢኖር ማንቀሳቀት ፥
ሕግና ሥርዓት ነው — ለእንስሳት ላፉዊት ፥
ሁሉም ሲደክማቸው — ማሸለብ ወተኛት ፥

ባፍሪካ በሌላም — የሚኖሩ ሕዝቦች ፥
ይሀ ግዛጅ ይዟቸው — ሆነው ሰለባዎች ፥
ለጊዜው ቢገኙ — ሆነው እንቅልፋሞች ፥

ያንጋላታቸዋል — አበላባይ ውድን ፥
እነሱም ሲያሾፉ — እሱም ሲያበስ ሲያድን ።
እንደድመቶችም — ጆሮ ሲያስቆረጥም !

የማጥጊቱ ጥበበ — እንላይዘነጋ ፥
የሕዝቦችን ትኛ — ባይጠፍ ልዝጋ ።

በድመቶች ማሾፍ — አይጦች ቢያጠቁ ፥

# ድመቶች ሲያሾፉ!



## አይጦች አይሆኑም — ከቶ እሚጠየቁ !

ድመቶቹ ከእንቅልፍ — እስኪነቁም ለታ ፥
መፍጠሩ አይቀርም — ተድላና ደስታ ፥
ላይጦች ሠራዊት — ባጥንት ላይ ፌስታ !

የሚያሾፍም ሆነ — ያንቀላፋ ፍጡር ፥
ወቅቱ ሲደርስለት — መንቃት ስለማይቀር ፥

ወዮ ለአይጦቹ — ያቺ ቀን ስትመጣ ፥
እጥንቱን ሲቆጥር — የሚያገኘው ጣጣ !
በሚነቃው ጥፍር — ምንጭሩ ሲወጣ !

የሚሆነውን ጉድ — ዛሬ ከመዘብዘብ ፥
ብንጠብቅ ይሻላል — ያቺን ዕለተ ግብ ፥

# ወይዘሪት ወይዘሮ!



ፍንደታ — ቁ 95

# መዘክርነቷ

ማራኪ ውበቷን እንቅሩ በመከዳት ፥ ካሩዳ ኮርዋ ወንና ባላም ከገባች በኋላ ፥ ንጽሕ ና ሊናና ቅርስ ምሩል ለማምረት ስትሞክር ቆይታ፥ በስተኋላ ላይ ፥ መከሩዋ ውኃ እንዳልቷጠረላት ተረድታ ፥ እንደገና ካሩዳዋ ተወልዳ ፥ የናኤ ሩ በማቱ የገረረበትን ጉባል ኀረምላ በማሌሩሬ ቅ ፥ ታማዩ ጭታ ሆና ፥ በባሕረ ውስናና ወሲ ብ ውስጥ ተዘፍታ ፥ ዜሩያ ገረገንዶ እልበታ ብኋት ለምትምላቀቀዋ ምልታቂት ፥ ይሀች ማግም ግስታወቿዋ ትሆን ዘንድ ቀርባለች ።



# ወይዘሪት
# ወይዘሮ!

ምን ሊያሳየኝ ይሆን — ይኸው ዘንድሮ ፥
ምን ሊያሰማኝ ይሆን — ይኸ የኔ ጆሮ ፥
አዳዲስ ትንግርቶች — ያልነበሩ ድሮ ፥
ክሥተቶች ወለደችል — የሚያመርት እንክር ፥
ወኔና ከማያውቀው — ካራሱ ተፈጥሮ !!

አምናም አረጀና — ዘንድሮ ሞተ አሉ ፥
ኗሪ ልጁን ትቶ — ለፈላጊው ሁሉ ።

በጊዜ ድልድይ ላይ — ሁሌ ስንከራተት ፤
ያላየሁት የለም — የፍቅሬን ትንግርት ።

ምን ይነግረኝ ይሆን — እያልኩኝ ስጠብቅ ፤
ዘንድሮ ጃርዬ — ያስገኘን ዘሩቅ ፤
ከወትሮው ዜናዎች — እጅግ የሚያስደንቅ ፤
ነውና የሚያሰኘኝ — ብርቅና ዕፁብ ድንቅ ፤
ዛሬ ልናገረው — ሳልሸሽግ ሳልደብቅ ፤
የሚያልፍም ነውና — ለትውልድም ዘሩቅ !

የዘንድሮ ጃር — ታምር ያልተለየው ፤
ዜናው ሳይደርስ በፊት — ገና በቸዜግው ፤

እዩቸም ነበረ — ምልክቶች ባለም ፤
በጣም የሚያስገርም — ለሰዎች የማይጥም !

ፀሐይ ምሥራቅ ትታ — ስትወጣ አለወትሮ ፤
ምዕራቤ እግሯ — ከሥርዓት ደንብሮ ፤
ከፀደቷ ውጭ — መንገዷን ቀይሮ ፤



ራሳሩ ነይደም — ጠንግሮ ሽውርር ፤
መንገድ ለቃ ስትሔድ — ትራፊክ ተሽሮ ፤
አዲስ ሥርዓት ነለም — ያሉበት ዘንድሮ !!

ምን ሊወጣ ይሆን — እያልኩኝ በዉነት ፤
ምን ሊከተል ይሆን — በግለት ሥውቀት ፤
ደብዳቤ አገኘሁ — ካገር ቤት ሳልጠብቅ ።

ምን ያስገኝ ይሆን — እያልኩ ሳሰላስል ፤
ያ ደብዳቤ አወጣ — ዜናና ልዩ ገድል ።

የደብዳቤው ዜና — ባጭሩ እንዲህ ነው ፤
ታምር ፋር የሚባል — ልዩ ታንኳር ያለው ።

በተወለድኩበት — ባደግሁበት ወንደር ፤
አንዲት ልጅ ነበረች — የሚለየን አጥር ፤
ውበቷ ነረምሳን — ልብ ልቡን የሚሰብር !
የተፈጥሮ ሆና — ስጣት ዝንባሌ ፤
ጥከር እርተኝ ነበር — ፋስላት አጥሌ ፤

ባዘራዱ ሆናልኝ — ልገፋት ፋወሌ ።

እሷ ግን ወገቧን — ፋይናች እየረጨች ፤
ፀንቴን ጉብል ነበር — እርስ በርስ ያናጩች !
ከሥጋዋ ይልቅ — ለነፍሷ ያደረች !!

እንቱ ያሉት ሁሉ — እንቺ ያላት የለም ፤
ያቺን ተክለ ገነት — ልዋኒቱን ደግም ።

ፈገግ ፊታ ብላ — ከንፈሯን በትክፍተው ፤
የጥርሷ ወጋጋን — ወብረቅ ምስጋን ይነሳው ።

እያብረቀረቀ — ያንሸዋረረው ወንድ ፤
ለስሌት ያቅታል — እየታወረ ሲያብድ ፤
ያምባችን ኅሬምሳ — በፍቅሯ ሲሸወድ !

የቅንድብ ፅድሞቿ — በርገድ ወከክ ሲሉ ፤
ወንቶቹ ዓይናቿ — በላል ያበርታሉ ፤
ኅሉ ጆባሕ ፈጥረው — ፋይናሞች ሊያድሉ ።



ኅኅሿን በሙሉ — የሸፈነው ፀጉር ፤
ወልእከ የነደፈው — ሐወልግል ንፀፀር ፤
እንዳለው ያሳያል — ከነፋብሎን ሐር ፤
ቀለው ሐምራዊ — እምሳላዊ ሃምበር !

ባምቡ ወሳይ ሽወል — ያ ወዘየ እንገቷ ፤
እምሳለ ጠምበለል — ቁወቱ ቁወቷ ፤
ፀላተ ሙሴ አይነት — ገበታው ደረቷ ፤
የሚያንፀባርቀው — ፀሐይ ጸላል ፊቷ ፤
ትምቡክ ተርፏ ባዩ — ሽንጧና ያ ባቷ ፤
እለንጋ ይወስል — ተወንጫፊ ባቷ ፤
ፍጹም ፍጽምት ነው — ጠቅላላው ውበቷ !
ፀንከን የሌለበት — ጥቅል እካላቷ !

ውበቷን ለወግለጽ — በቋንቋ ወጠቀም ፤
ንፅፅር ማድረግ ነው — ኬወዮርከን ካንከበር።

ሲሥላት ሲወራት — ለዘለዓለም ኖሮ ፤
በትምህርት ኪነት — በጥበብ እንከር ፤

ማስተርስ ያገኘባት – አንድ አርቲስት ተምሮ ፤
የተወረቀበት – ወያን እስመሞክር ፤
ሞዴሉ ናት ማለት – ያስችለኛል ደፍሮ !!

ያቺን የመሰለች – ግግደ መላዕክት ፤
ምንም ሳይታወቅ – የነካት ምክንያት ፤
ገዳም ገብታ ነበር – ገና ሳለች ወጣት ፤
ያሉም ሰዎች አሉ – ዓለም አስጠልቷት ፤
ውስናው ወሲብ – ንቅዘቱ አስጠይፏት !!

ታሪያንን ደብዳቤው – የያዘው ዉዋታ ፤
የሷን ታሪክ ነበር – እሷሱን ሁኔታ ፤
ከገዳም ተጋብታ – ገዳም ስትፋታ !!

የገዳሙም ኑሮ – ስትቆይ አስመርሯት፤
ዛሬ ተወልሳ – አራዳ ፒያሳ ናት ፤
ይላል ደብዳቤው – ወይዘሮር ወይዘሪት !
ትላንት የነበረች – ፍጽምት ባሕታዊት ፤



ወርካቶ የገባች – ወቂንኑ ሰልችቷት !
አራዳዋ ገብታ – ዛሬ የምትዟዟት ! !

የምን ድንግልና – የምንስ ሞራል ክብር ፤
ድሮ እምታምንበት – በገዳም የነበር ፤
አራዳ ስትገባ – ቅዤና እሳት ነገር ፤
ሆኖባት ቀልዓለች – ይለኛል ያ ጦማር !
አዬ ጉድ መታለል – ለምኞት መመንዘር !
ምን መመንዘር ብቻ – ለንቅዘት መወይዘር !!

የገዳም ላይ ጀጌ – ፍጽምት የነበረች ፤
የመነኩሴ ሳይቀር – ቆቡን ያስወለቀች ፤
ከርከዱን ሸዋቦን – ፅንቁዴት የተባለች ፤
ፅንዜራና መመንቀ – ቅላኔ ያሷት ፤
አራዳ ስትገባ – ግንባር ወጂን አሳች !

ዛሬማ ይለኛል – ያ ትኩስ ደብዳቤ ፤
እንድነዘረው ሲያውቅ – ያ ውስጠኛው ልቤ ፤

ስለሷ ለመግር – ሊያገኝ ግንዛቤ ÷
መግቧቴን አይቶ – ሊያረካኝ ባባቤ !

ዛሬግ ዉርስ – ፍጹም ለይቶላት ÷
ግደሪያዋ ሆኗል – በየሆቴሉ ቤት ÷
ራስ ግዮን ዋቢ – ሒልተን ሪስቶራንት ÷
የዛሬ ወይዘሮ – ምንተ ባሕታዊት !!

ቀፀለ ገዳም ሆና – ቷቷ ፏ ቦግ ስትል ÷
ከላይ እንደሚንዘር – ወደታች ስትፀድል ÷
ሁሉን ጠቃቅሳለች – ባይኗ ለማባዘል ።

ግምጃዊ ቀሚሷን – በወጠኑ ገልባ ÷
በሚገላምጥ ጭን – የስንቱን ቀልብ ስልባ ÷
ከውጭ ሀገር ባይቀር – ስንቶቹን ሰባስባ ÷
አምጥታለች እሉ – ነረምሳ መገባ ÷
ውሽማና ደባል – ሊሆናት አስባ !

ትላንት የነበረች – ቀዘባ ወይዘሪት ÷



በገዳም መንኩሳ – ስንቱ እግሆይ ሲላት ÷
እራሳ ብትገባ – ሁሉ ቢቅ ዞረባት !
ምንነቷን ሳይቀር – ግወቅ አዘናጋት !

ምንትዎክ ቢሆን – ጋኔል የሚኀረር ÷
ለነፍስ የሚያድሩን ነው – ሥጋን በማባረር !

እሷም ሳይቸግራት – የጋኔሉን ወርሳ ÷
ስንቱን ፍዳ አሳየች – አዘላች አበሳ !

ትላንት የነበረች – ትሁትና ታጋሽ ÷
ዛሬ ተቀይራ – ሆናለች በሽበሽ !
እግድዋሽ እያየች – የምታደርግ ገሽሽ !

ትላንት የነበረች – ታታሪና ሠሪት ÷
ዛሬ ተምናድላ – ወይዘር ደግሚት ÷
እራሳ ጠቢታል – ምድሩ አልበቃ ብሏት !

ያ ወሬዋ ሁሉ – እስር ውሉን ስቶ ÷

ፅሰለት ምርጋን ይገባው — ቀኑ እስኪመሽ ነግቶ!
የምትቀበጥረው — ባቲሆ ፅንቶ ፈንቶ !

ዛሬ ያወራችው — እስከነገ አይቆይም ፥
የትናንትናውም — በዛሬው ቀን የለም ።

ወዳጅይነቷን — ሰው ሁሉ አረጋግጦ ፥
የማያምናት አጥታለች — ወይዘሪት ወረገጦ !

ልቧ ያሰበውን — ባካኪ ልትነዛ ፥
ዛሬ ከሊዮፓትራ — ትላንት ሞና ሊዛ ፥
ነገ ደግሞ ሔለን — ባርባራ ትሬዛ ፥
የማትሆነው የለም — በቀለም ጠንብዛ ፥
አይነት በሚል ፈሊጥ — እንዲል ተወርዛ !!

ድሮም እኔ ሳውቃት — በዚያች በኛ መንደር ፥
ከንፈሯን ሊፕስቲክ — ትቀባባ ነበር !
ለማስመሰል ብቻ — ባልሆነችው ነገር !

በትኩስ ፅድሜየ — ወጣች ባለች ድሮ ፥



አሊሆዶ ነበረ — ዘፈኗ ከበር !

አትወድምም ነበር — ምግብ እንጀራ መብላት ፥
አበሱላን ቅመም — ወጥ ከሌለበት ።

አምናና ሐች አምና — በርግጥ የነበረች ፥
ለሰው ልጅ ነፃነት — ለመብቱም ተሟጋች ፥
ዛሬ ተቀይራ — የማልብዋ ሆናለች ! !

ታንኪረኛው ጦማር — የወላጅ ደብዳቤ ፥
ያላወራው የለም — እንድረካ አንብቤ !

በዚያ ሰሞን ይላል — ባንደኛው እንቀፅ ፥
ያ ደብዳቤ ሊያትት — ባወፈረው ቅጹ ።

በዚያ ሰሞን ደግሞ — ባስከተለችው ገድል ፥
ያለወርግ ተድራ — ያገባችው ሞኝ ባል ፥
ሥታይ እንዳየ እለ — ባጋጠመው በደል ፥

ወዓ ገባ እያለች — ጠቃቅላ ስትወጣ ፥

የውሽግዋ አይነት — ፈጥርባታል ዓዓ ፥
እልፍኙን ወልቀቁ — እንግዳ ሲወጣ !

የነገር አባቷም — እያጥር እያጥር ፥
ሽሽቶ ካምባው ገብቷል — ከመድረክ ደንብር !

በስተኋላ በሩን — ባመጣባት ጠባይ ፥
ቋንቋውን እያየች — ታወጣለች ከላይ ፥
በግብ ግቡ ወቅት — ልዩ ንለውን እንዲያይ !

መወሪያ አድርጋ — የያዘችው ፈሊጥ ፥
እንዱን የሚያስቆም ነው — ሌላን የሚያስቀምጥ !

ፍሬግ ብሰባት — የምትሠራው ሁሉ ፥
እጅ እጅ እያለ ነው — ተግባሯ በሙሉ ።

ከሰው ሰው ለይታ — ማቅረብ ጀምራለች ፥
ወይዘሪት ወይዘር — መቁረጥ ያልሠለቻች !

ከከተማ ርቃ — የከረመች ገላም ፥
እራሳ ስትገባ — አልዘገንናትም !



ታመግቅባለች — በወሲብ ቱግታ ፥
ጥራል በኋ ጠባይ — ስለሌለው ቦታ ፥
ውስናን ይዛለች — ልትሆን ጋለሞታ !

ወይዘሪት ወይዘር — ይሉኝታን የበላች ፥
ጌጤዋን ጠብቃ — እንደገና ወጣች ፥
ወልኳን ተቀባብታ — ከፊቷ ልትለይ ።

ይሉኝታን ጨፍልቃ — የጠጣች እኝካ ፥
አጥዝታ ብቅ አለች — እያሳየች ወልካ ።

ድንቂቱ ወይዘሪት — ምን ይሉኝ ያማታውቅ ፥
ባደባባይ ወጣች — ወሳጅ ለማሠቀቅ ።

ከጠባዩዋ ሁሉ — በይዘልጥ የጎላው ፥
ቀረጣን መውደዷ — ነፍሷም መሆኑ ነው ፥
ቻኮላታዬ ነው — እሷ የምትለው !

ስለዚህ ይሆናል — ካች እምና ዘንድር ፥

# ወይዘሪት ወይዘሮ!

አመት ባልሞላው ወቅት — ምርቃቷ ሆምር ፥
ከወይዘሪት አልፋ — የሆነች ወይዘሮ ፥
ትንቢቷም ቢወልም — ቢያሰምርም እርር ፥
እስከ ዛሬ አለች — ወይዘሪት ወይዘሮ !!!


# መውጣት አዋራጁ!




ፍንደታ — ቁ 96

# መዘክርነቷ

በልዩ ልዩ ግላዊ ምክንያቶቻቸው አስገዳጅነት ፥ ዕትብታቸው ከተቀበረበት ቅድስት ሀገራቸው ምድር ፥ ድንገት ወጥተው በመሰደድ ፥ ነፍሳቸውን ከተራግጅ እግራቸው ላይ በማቆመር ፥ በባዕዳን ሀገሮች ውስጥ ተንከራታች ሆነው ለሚገኙ ወገኖች ሁሉ ።




ስንት ነገር አለ — በዓለም የሚደነቅ ፤
ባካባቢ ብቻ — እጅግ ሄደን ሳንርቅ ።

ተፈጥሮ ኮሚክ ነው — ባንዳንድ ልዩ ሥራው ፤
ከውስጡ ሳንገባ — በላዕላዊ ገጽታው ፤
እንደዘበት አርገን — ጨራርፈን ስናየው ።

ዕጹብ ነው ድንቅ ነው — የሚያሳየው ጥበብ ፤

በኅሊናው ብቻ – ወርዋር ለሚያስብ !

ምሥጢሩን ተረድቶ – ተፈጥሮን ለማወቅ ፤
ብዙም አያስፈልግ – አለቅጥ መራቀቅ ።

በፍጡር አካል ላይ – የሚታየው ብቻ ፤
ትልህ ግብረኛ ነው – ምሥጢራት መግለጫ !

ላይና ታች ማለት – ወይም ግራና ቀኝ ፤
ከቶ አያስፈልግም – ዕውቀት ለሚወኝ ።

ሁሉ ካጠገቡ – ካቅራቢያው ይገኛል ፤
ተፈጥሮን ወርዋር – ማወቅ ለሚከጅል ።

ለዚህ አይነቱ ግብ – ደገኛው ምሳሌ ፤
ግብርን በማሰረኛ – ጠጅን በብርሌ ፤
ብሎ እንደሚያቀርበው – ያገር ሽማግሌ ፤
እንዴን ልጥቀስለት – ለሚሰግኝ ሞሌ !!

ፍልሥፍና ሆነ – ወይም ሥነ ፍጥረት ፤



ከላይ አልወረደም – ከመናፍስት ዓለት !

ሁሉም ነገር በርግጥ – ከሰዎች ይገኛል
ነውና ተፈጥሮው – ጥበባዊ አካል ፤
ምሉዕ በኵለሄ – እንዲሆን አርጎታል ፤
ኋላ ሰው የሆነው – በመጀመሪያው ቃል ።

መውጣት የሚለውን – ብናይ በዚህ አንፃር ፤
መከሥት ነው ድርጊቱ – ለተለየ ምሥጢር !

በመውጣት ምክንያት – ያሉትን መዘዞች ፤
እንዳንዶቹን ልጥቀስ – የራሴን ትዝብቶች ።

ጥንተ ባሕርዩ – እንጎል የነበረ ፤
ካለበት ቦታው ላይ – ሲወጣ ከሠረ ።

ባጠገቡ ያለ – አሸንዳ ፈልጎ ፤
ባፍንጫ ቢወጣ – ቀዳዳ ሠንጎ ፤
ተራ ንፍጥ ተባለ – በመውጣቱ ባልጎ !

ለወትሮው ነበረ — የሐሳብ ማኅደር ፥
በንኅል እያለ — በአፅምሮ ሀገር ፥
በውስጥም ሲቀመጥ — እጅግ የሚከበር ።

ባልተረዳው ጥበብ — ባልፈጸመው ፍዳ ፥
ቀልጦ ፈሶ ቢሸሽ — ፈልጎ ቀዳዳ ፥
ተራ ንፍጥ ተባለ — በማያውቀው ዕዳ !

ካፍንጫ ቤቱ ውስጥ — ቢኖር ተደብቆ ፥
ማንም ንፍጥ ባላለው — ባልሆነም ዉምላቶ !

ከጥንቱ መኖሪያው — እንደምንም ቢኖር ፥
ማንም ባልሰደበው — ንፍጥ እያለ ሀገር !

በመውጣቱ ነው — ንፍጥን ንፍጥ ያስባለው ፥
በውስጥማ ቢኖር — ማንም ባልደፈረው ።

መውጣት አዋራጅ — በሐሳብ እያሰኘኝ ፥
የውስጠኛን እንኳ — ውጪ ንፍጥ አሰኘ !



ከራሱ መስደብ — ደግሞም አልፎ ተርፎ ፥
ሰው ያሰድብ ጀመር — በነጉንፋን አልፎ ፥
ንፍጥም አያሰኝ — በጅላጅል ወጥሮ !

አስጠያፊነቱ — በሰው ሁሉ ታውቆ ፥
መጥረጊያ መሐረብ — ሙርቶለታል ንቆ ፥
ጠራርጎ ሊያጠፋው — ካፍንጫ ስረ ፍቆ !

እስካልወጣ ድረስ — ባፍንጫ ቀዳዳ ፥
ምንጊዜም እንኳ ነው — የተሸከመ ዕዳ ፥
ክቡር አዕምሮ — ሰውን የሚረዳ ።

መውጣቱ ብቻ ነው — እንዲያ ያዋረደው ፥
ያ ክቡሩ እንኳ — መዝገብ የነበረው ።

መውጣት ያወጣው ጦስ — ለንፍጥ ብቻ አይደለም ፥
ሌሎችንም ጥምር — አዉግልቷል በጣም ።

በውስጥ ምራቅ ነበር — ባፍ ክልል እያለ ፥
ሳይቸገረው ወጥቶ — ከንፈር ሳለፈ ፥

በመውጣቱ ብቻ – ለሰው ነው ተባለ !

በነበረች ወቅት – በጉረሮው ወቅደሰ÷
ተመርገና ነበር – እፍ በወፋ ሲያርስ ÷
የወረቅን ያህል – እንደሀብታም ድግስ !

በጉረር ሳለ – ተፀውያ ሰው ÷
ምራቅ ብቻ ነበር – ተወፋጅ ባዕው ።

ድድና ጥርስ ሆነ – ላንቃም ሆነ ምላስ ÷
እያሆነላቸውም – ያለ ወራቅ ወራስ ÷
ምግበ ሆጋ ሁሉ – እፍ ገብቶ ሲደቆስ !

ፅንጥል እንኳ ሳትቀር – በነፃ እምትዋኘው ÷
በምራቅ ነበረ – ባሕር ከእፍ ባለው ።

ከጉረር ጥቫው – በድንገት ቢወጣ ÷
ከንፈር አቶፍ ሲደርስ – እመጠበት ጣጣ ÷
አከታ እያሉ – መጠየፍ በቶጣ !



ለሰው ነው እያሉ – የምራቅ ባፋንጣ !
መውጣት ባወጣው ጦስ – እውጭ ቢቀናጣ !!

አዬ መውጣት ከፋ – ሰንቱን አሰደበ ÷
ካለበት አሸሽቶ – ከውጭ እየሳበ !

ውሃና ደም ነበር – ሲኖር ባካል ከውስጥ ÷
በመውጣቱ ብቻ – ፋብ አሉት ሲግገጥ !
ከቤቱ ቢወጣ – ሲያጸፋ ያሠር ግጥ !

ለጉልበት ለሕይወት – የነበር መሠረት ÷
ከውጭ ቢወጣ – ቆሻሻ ፋብ አሉት !

ሲወገብ የኖረ – ቢወጣ ሰልችቶት ÷
ውለታ ቢሰጭ – ቆሻሻ ፋብ አሉት!

ነፍስ እስትንፋስ ሆኖ – አካል ሲያነቃንቅ ÷
የነበረ ግደ ደም – ፋብ አሉት ጥቅው ቢያልቅ!

መውጣት የጊሉት ቢቅ – ሰንቱን ነው ያሳጣው ÷

ደከሞ እገልግሎ — ለግሬና ሲታገሠ ፥
ያልሆነ ስም ሰጥቶ — በግልጽ ያስደበው !

ቁምታኝ ውስቢ ነበር — በሬት ያለው ሰው ፥
በእፍ ሲንቀረቀር — ቀይቶ እንዳቅው ፥
ኋላ ላይ ሲያልቅበት — የሚሰጠው ጥቅው ፥
ፈርጥጦ ቢወጣ — አልቆበት ጓዑው ፥
ሽንት ነው ተባለ — ውስጥ የነበር ደው !

ውሃ ጠላ ውና — ቿይ ይባል የነበር ፥
በጉረሮ ገብቶ — ቢወጣ በታች በር ፥
ውርቶ እገልግሎ — ያካላትን እውታር ፥
ሽንት ነው ተባለ — ባሽንዳ ሲባረር !

እዬ ወውጣት ክፉ — ሰንትኮ በደለ ፥
ባፍ ከላይ ሲገባ — ሰብኮ እያታለለ ፥
ጣፋጭ ነው እጥጋቢ — እርኪ እየተባለ ፥
ኋላ ላይ ሲወጣ — ጠያፍ ደጅ የፃለ ፥



ንፍጥ ላብና ንደናር — ሽንት የተከፈለ ፥
ኩስ ለሰጥ ተብሎ — እዳቅት የተጣለ !

በሬት ጠጅ ነበር — ሲገባ ተከብሮ ፥
በላዩው እሽንዳ — በሒያ በጉረሮ ፥
ኋላ ሽንት ተባለ — ቢወጣ ሽንቁር !
ቀላል ፈልነ — ከውስጥ ቢሽሽ ደፍሮ ፥
ለውራው ውለታ — በውስጠኛው ኑሮ ፥
ወርታ ሳያገኝ — የፈሰሰ ጓሮ !

እስታንሽ እርሰቶ — ኮቴሌቲ ፓስታ ፥
ክትፎ የዶሮ ወጥ — እንጀራ ሰለልታ ፥
ምንቸት አብሽ ቅንጪ — ወይም ቾኮላታ ፥
ተበልቶና ጣፍጦ — ላንጀት ሰጥቶ ደስታ ፥
በመጨረሻ ላይ — ቢወጣ ላንቃፍታ ፥
ኩስ እውር ተባለ — የርውብ እለኝታ !
እዬ ወጋቢ እካል — ቢወርድ ነልነታ !

አጥንትና አጥንት — ሲጋጠም እንዳያም ፥
ሉብሪኬቲቭ ነበር — የሚያወዛ ግጥም ፥
ያካል ውስጥ ግራሶ — ቅባቱ ሰልምልም ።

እሱም በበኩሉ — በጆሮ ቢወጣ ፥
ኩክኮ ተባለ — ወይ የመውጣት ጣጣ !

አንዱ ላይ ተገኝቶ — ባጥንቶች መካከል ፥
በጆሮ ጎራ ስር — አንቴና ሲያባብል ፥
የነበር ግራሶ — ወጥቶ ሲገላገል ፥
ቆሻሻ ኩክ አውር — ከቶ እንዴት ይባል !!

አረኮ ስንቱን ነው — መውጣት የበደለ ፥
ከምቀበት ቤቱ — አጥርዶ የጣለ !

ተከብሮ ካለበት — በግዴ እያወጣ ፥
አረኮ ስንቱን ነው — ያፈላበት ጣጣ !

ባይኖች ጓሮ ሠፈር — የነበረ ፈሳሽ ፥



ባጋጣሚ ነገር — ቢጠጥር ለወሸሽ ፥
ጎደኛር ነው ልዩ ስም — ያገኘው እወሳሽ ፥
ብርሃንን የሰጠ — ጥላጣውን ደምሳሽ !
በዐላል ያኖሬ — ባለም ሲያምነሽንሽ !

እያስደንቅም ወይ — ያገኘው ወርታ ፥
ከውስጥ ሲያገለግል — ለሰጠው ውለታ ፥
በመውጣቱ ብቻ — ላገኘ ብሎ ዕርዳታ ፥
ዕርፈትና ስድብ — የውርደት ቱግታ !!

በእፍላነት ዘመን — ተደብቆ ከውስጥ ፥
በወኑን ጠብቆ — ቢወጣ ቢጋለጥ ፥
ፀጉር እንኳ ተብሏል — ሽበት እንደማገጥ ፥
እውቀ እንደ ወጣ — በፅድግ ሊግግጥ !
ተቀጥሮ በሰዎች — የወጣ ሊያላግጥ !

ሽበት በመውጣቱ — በእንዳንዱ ራስ ላይ ፥
ስንቱን አረጋዊ — እፍውንት ነኝ ባይ ፥

ሽሜ ጉት እስን — ሊያሳዩ አደባባይ ፤

ከተደበቀበት — ያ ሽበት ቢወጣ ፤
ፀጉር የነበረ — ቅይር ስም አስወጣ !

የሰው ልጅ በረከት — የሰው ረድኤት ፤
ለዘር ፅርሾ ሆኖ — እንዲኖኝ በመሬት ፤
እንዲረጭ የብስ ላይ — እንደተራው አዝርዕት ፤
ፍሬ ነበር አብራክ — ባካል ውስጥ ሲቀመጥ ።

ኋላ ግን ወከር ላይ — ዝሬት ሲሠግሬ ፤
ባለበት ግብ ግብ — አካል ዘር ሲዘራ ፤
በሚገጥመው ትግል — ግሳ ላይ ሲያቅራራ ፤
በሙሉ ጉልበቱ — ወጥር ሲሠራ ፤

ወተንፈሲ ብሎት — ዘሩን ታች ቢበትን ፤
ኃይልቱ ወጣ — ሲሠምን ሊኮነን ፤
ተባለክ ሲተች — እዩ ጉድ ሰው መሆን !



ከውስጥ ባለበት ወቅት — እየተባለ አብራክ ፤
ሲከበር የኖረ — ዘር ተብሎ ብሩክ ፤
እንደቅዱስ ነገር — ባክብሮት ሲመለክ ፤

ሊያዩ ቢወጣ — ከኖረበት መቅደስ ፤
ኃይልት ተባለ — ከወጭ ዓለም ሲደርስ ፤
እንዲህ ያለው ወንት — ያስኛል አያድርስ ።

የነበር በቤቱ — ከኖንተ ሙዳኡ ፤
በገዛ አካሉ ውስጥ — በተፈጥሮ ልምዱ ፤
ክቡር ዘር ተብሎ — ኖሮ ነበር ሆዱ ፤
ባብራክነት ሳለ — በአካል ጉድጓዱ !

ኋላ ግን ቢወጣ — ስሜት እንስፍስፎት ፤
ከአካል ቢከፈል — ባጫጅ ፍላጎት ፤
ለሕጋዊ ግብሩ — ቢሠገሬ ድንገት ፤
እያስደንቅም ወይ — ወባሉ ኃይልት !

ኧረ ስንቱክ ነው — መውጣት ያዋረደው ፤

ተዘርዝሮም አያልቅ — አፅፋፍክ ነው !
ኅልቆ መሳፍርት የለሽ — ሚዛን ልክ የሌለው !

መውጣት የሚለው ቃል — በታሰበኝ ቁጥር ፥
ስደት ትዝ ይለኛል — የዚህ ዘመን አሳር !
እኔም ያለሁበት — መከራ ቸነፈር !
ሥቃይና ፍዳም — ሌት ቀን የሚያስቆጥር !

ነፍስን ካገር ትቶ — ሥጋን ብቻ ይዞ ፥
ከውጭ መንከራተት — በደል ፍዳ አርግዞ ፥
ካገር አገር መንጎድ — ጀንፍ የለሹን ጉዞ !
በባዕዳን ምድር — መነግነጥ ፈዞ !
ስደትኮ ማለት — መኖር ነው ተከዞ !

ነፍሴ እዚያ ግዶ — ሥጋዬ ግን እዚህ ፥
ሉአል ምንታዌ ነው — የሱ ትርጉም ይግባህ !

ነፍሴ ባሕር ግዶ — ባዕድ ሀገር ሥጋዬ ፥
ምንን ሰው ልሁነው — ባርባ ቀን ፅፋዬ ፥



አንዱ ነጠላ ሰው — መንታ ተገንጥዬ ፥
ስግትቅ ሰውታዬ — አለውዴታዬ !

ነፍስ የተለየው ሥጋ — ምንጊዜም ሞት ነው ፥
ነፍሴን ካገር ትቼ — ሞተር እንደሌለው ፥
መኪና አይነት ሆኜ — በውጭ እምኖረው ፥
በሥጋዬ ብቻ — የምንከራተተው !
የስደቴ ሕይወት — ምንም ትርጉም የለው ፥

በሥጋዬም ብቻ — ውጭ ሀገር እስካለሁ ፥
እወቁልኝ በርግጥ — አልኖርኩም ሞቻለሁ !

መውጣት ወንጀለኛ — በፈጸመው በደል ፥
ስንከራተት አለሁ — የዘመኔን አበሷል !

ከላይ ተዘርዝሮ — ስለ መውጣት ችግር ፥
የቀረበው ሁሉ — ሐተታ ስንከግር ፥
መስተዋት ነው ካርታ — ለተሰላጅ ችግር ፥
እንፀባርቆ መላሽ — ብሶት የሚናገር ።

ስለዚህም ነው — የማይወጣው ቢግ ÷

በዕዝልና አራራይ — በዝማሬ ራግ ÷

“ከርቸሌው ስደቱ”— እያሉ የማሰግ !

መውጣት የሚሉት ቢቅ — ከያዘኝ ጀምሮ ÷

አባዬው ለካከር — ከባለኝ ወርወር ÷

ከነጀሰኝ ወዲህ — በርር ጠፍር ÷

እንዳልኖርኩ እውቃለሁ — በባዕድ ሀገር ኑሮ !

ሰው ልጅ በሀገሩ — በገዛ ቀዬው ወንዝ ÷

እንዳሻው ተዝናንቶ — የትም ቢያደነድዝ ÷

ክብሩ ነው እላለሁ — ቢራብም ቢተክዝ !

ያካባቢ ቃና — ወንዝ ጅረያት ÷

የቄው ያሀያው — የእንሰሳው ዉከት ÷

የወፎች ዝማሬ — የተራራው ውበት ÷

የዘመድ የሀገር — ታላቅ በዓላት ÷

ባዕድ ሀገር ላለ ሰው — የሚፈጥሩት ናፍቆት ÷



ድንቋ አይገልጸውም — በብዕር ቢጥሩት !

ያገሩን ምድር ለቶ — ከወጣ የሰው ልጅ ÷

እንኳን ለሌላና — ለራሱም ኑሮ አይበጅ !

ወለያውን ክብሩን — እየመነዘረ ÷

ተጥርዶ ይበቅላል — ባዕድ ሀገር የኖረ ።

ቀውጢ ዘመን ደርሶ — የተገባት ዘመን ÷

መውጣት ባወጣው ጠንቅ — ሥቃይ እናያለን ÷

እኛም ዉው ይወስል — በዓለም ተበትነን !

ሥርዓት ተፈጥሮ — የደነገገው ሕግ ÷

ከቶ ከሆነማ — ምንም አይደረግ ÷

በመውጣት መግቶት — ያለ በእኛም ወግ !

ስለዚህ ይበጀል — ወኖር በየደጁ ÷

ከባዕድ ሀገር ኑሮ — ከምድሪ ፈረንጁ ÷

ከሚገመትበት — መውጣት አዋራጁ !!!

* * *



ወ ፋ ኛ ሽ  ወ ኛ  ነ ው

እማማ ኢትዮጵያ — ለዘመናት ታማ ፤

ይሻላታል ስንል — ስትማቅቅ ከርማ ፤

እንደገና ደግሞ — ዛሬ አገረሸባት ፤

ግካ የሚያስገባ — ትኩሳት ወረራት !!

*   *   *

# መርሳትን ነው መርሳት !

የገደልኩት በስሕተት ነውና ይቅርታ አድርጉልኝ !



የገደልኩት በስሕተት ነውና ፤ ይቅርታ እጠይቃለሁ !!

# መዘክርነቷ

ተከታዩ ግጥሟ ተልዕኮ ለሚመለከተው ሁሉ !

ምንድር ነው ብሏት — የይቅርታ ትርጓሜ ፣
የልቡን ተመኘቶ — በሚችለበት አቅም ፣
በስተመጨረሻ — ጥራ መቁላት ግርመም !

ምን ፈልጎስ ይሆን — የደንቋው አባባል ፣
ፍላጎቱን አርጎ — የምኞቱን ክፊል ፣
ተሳስቼሽ ነው — ይቅርታ አድርግ ሲል !

ምኞቱን ፈጽሞ — ከረካ በኋላ ፣
ይቅርታ ቢጠይቅ — የቱን ጥኝ ሊበላ !

It is easy to forgive ,
but equally difficult to forget!

እንዳለው ፈረንጁ — በይቅርታ እንቆጹ ፣
መርሳት ካልተቻለ — ምን ሊሆን ነው ቅርጹ ፣
ይቅር ለማድር ባዩ — በቂም ያለ ነጹ !



# መርሳትን ነው መርሳት!

ወገኛ እኛፈረን — እያሉ ተግግነው ፤
ጥቃቅን ግዜቶን — እንደያዩነታቸው ፤
በዚሀ ዓለም አሉ — ፎሬ ሰቅን ወሰለው ።

ፈረንጅ እንደሚለው — At closest range,
ቀርበን ብናያቸው — በርግጥ አወናባጅ ፤
ናቸው በባሕርይ — የሀሰት ንርግጅ !

አንዳንዶቹን ብጠቅስ — ለናሙና ያሀል ፤
ቀሬዎቹን ሁሉ — ወዴል ነው ያሳያል ፤

ትክክል ግልባጭ — ነውና በአምሳል ፥
በተቃዋሚነቱም — እንደራሱ ይሆናል !

በባላባት ዘመን — ከነበረው ኹነት ፥
ነበረ እንደኛው — ሊቀ መኳንንት ።

የዚህ ተጻጊ ሰው — ቀጣጊ ተግባሩ ፥
መሰሉ መታየት ነው — በመልካሙ ጎብሩ !
ፍውራው ባለሥልጣን — ሰውልቱ ምሥጢሩ !

ለዚህም ተብሎ — ይበላል ይጠጣል ፥
መኪሉን ለመምሰል — ተቀብቦቶ ይመጣል ፥
የአውራውን አይነት — ግልባጭ ይለብሳል !

ያ ሁሉ መቀባት — ያም ሁሉ መኳኳል ፥
ግቡና ጥረቱ — የመገልበጥ ትግል ፥
እንደሆነ ታውቋል — ፍጹም ለማስመሰል ።

ማስመሰል ማስረሳት — ሁለቱ አንድ ናቸው ፥
ጭብጡን ለመደበቅ — ነውና ግባቸው ።



ማስመሰልን ትተን — ማስረሳትን ብናይ ፥
ሰለባ ያደርጋል — በሰባኪ አታላይ !
ማስረጃ ልደርድር — ባንዳንዶቹ ጉዳይ ።

በጥሬ መልውሎ — እስኪበታው ድረስ ፥
እንጀቱን አርሶ — በጥላቻ መንፈስ ፥
ይቅርታ አድርጉልኝ — ማለት መጨረሻ ፥
ምን ማለት ነው ከቶ — የድለላ ቁኛ !
የልብን ፈፅሞ — ይረሰዋል ማለት ፥
ከንቱ ጅልነት ነው — ጨርሶ መሳሳት ።

መርሳት አይቻልም — ካንጀት ውስጥ ከገባ ፥
አታሞው እንድዶ — ሆድን እያባባ ፥
ያስመሳዮች ተንኮል — ፍጹም ፅውነት አልባ !

የልቡን ፈጽሞ — ምኞቱን ሲያረካ ፥
እንዳኛው አድርጎ — በድሉ ሲያመካ ፥

የሚፈልገውን — ከሙሉ በኋላ ፥

ተሳስቼኮ ነው — ይላል በድለላ ።

ምን ማለት ነው ይሆን — የዘይቤው ብሒል ፥
ተሳስቼኮ ነው — ይቅርታ አድርግ ሲል ።

እንደ ፍላጎቱ — ያገኘቱን አርሶ ፥
ይቅርታ ማለቱ — ወልሶ መላልሶ ፥
ምን ሽቶ ቅባት ነው — የማያሽር ኮሶ !

የልቡን ፈጽሞ — ተሳስቻለሁ ቢል ፥
የሠራውን በደል — ማን አምኖ ሊቀበል !

የሰው ዓይን አፍሶ — ማለት ወጨረኝ ፥
የምን ግራሶ ነው — ምን የሚሉት ፋኝ ፥
ማቅረብና መሆን — የቁስል ወጌኛ !
ዕውር የሆነን ሰው — ላይሆን መሪወኛ !

ሲያወጣና ሲያወርድ — ለወራት ሰንብቶ ፥
ሲያስላ ሲያደባ — ዓመት ያህል ባጅቶ ፥



የተሰቀለው ማነው? ለምን ተሰቀለ? እንዴት ተሰቀለ? መቼ ተሰቀለ? የተሰቀለውማ በሰማዕትነት ሞቷል ። የተሰዋበትን ምክንያት ወንጀሉ ( Cause ) የሚያውቁ ባለሕይወታውያን ሁሉ ፥ መርሳትን ይረሱ እንደሁ እንጃ ፥ ሕያው የነበረን ሐቅ ምንጊዜም አይረሱም !!!

ዕቅዶች ሲነድፍ — ሲያዘጋጅ ቆይቶ ፤
ወዳኛውን ዘዴ — ወዳ አወቻችቶ ፤

ከሙሉ ዘጋቢ — እጅግ ዘግናኝ ወንጀል ፤
ይቅርታ ቢጠይቅ — የቱ ሞኝ ሊቀበል !

ሆን ብሎ አውቆ — በውን ያረገውን ፤
Intentionally እንደሚለው ልሳን ፤
በደንብ ተወናድቶ — በዘዴ የሙሉውን ፤

ግን ያምነዋል ከቶ — ተሳስቼ ነው ቢል ፤
ይቅርታ እያለ — ቢማለል ቢደለል ፤
ያንጀቱን ፈጽሞ — የቱ ጅል ሊቀበል !

ልቡ እያወቀ — በፈጸመው ወንጀል ፤
የቱ ተበዳይ ነው — ከቶ ይቅር የሚል !

ምኞቱን ፈጽሞ — ከረካ በኋላ ፤
ይቅርታ ቢጠይቅ — የቱን ሞኝ ሊበላ !



ከድፍረቱ ብዛት — ደግሞ ሲያቅላምጥ ፤
“የኔ ጌታ” ይላል — ባቱ ሲያምጠውጥ ።

እንዳሻው በድሎ — ኖሮ ሲያወላልቅ ፤
በመጨረሻ ላይ — ይቅርታ ቢጠይቅ ፤
ስሕተት ነው ብሎ — በልመና ቢደርቅ ፤
ርኅሩኅን ጭምር — ስብኮ ቢወሽድቅ !

ግነው የሚቀበል — የይቅርታን ሽፋን ፤
ወንጀል ሲያወርት ኖሮ — በበደል ሲሰበን፤
ምሱን ሊያገኝ ሲል — ቢቆላ ጭራውን ፤
ግነው የሚያልፍለት — እሱ በሰራው ደይን !

ስንት ደፋር አለ — ስንትስ ዓይነ ደረቅ ፤
ያንጀቱን ፈጽሞ — ይቅርታ እሚጠይቅ !

አውቆ ይረግጥና — በኋላ እግሩ ፤
ይቅርታሀን ይላል — ደግሞ እለማሩ ።

ምን ይሆን ትርጉሙ — የዚህ ሰው ይቅርታ ፤
ካልሆነ በስተቀር — አርገኘሁ ዘለ ዘርታ !

ከድፍረቱ ብዛት — ደንግጦ ሲያቀላምጥ ፤
የኔ ጌታ ይላል — ቃላት በማማለጥ !
የለየለት ሞሌ — የምላስ ብልጣብልጥ !
“የኔ ጌታ”ይላል — ቃላት በማማለጥ !
የለየለት ሞሌ — የምላስ ብልጣብልጥ !

ተንደርድሮ መጥቶ — እያጥቆ በጥፊ ፤
ይቅርታህን ይላል — እንዳይባል አጥፊ ፤
ስንቱ ሞሌ እራሱ — ዉልሌ ቀጣፊ !

ወንጀልን ፈጽሞ — በራሱ ጥፋት ፤
ለኔ አይገባኝም — ይቅርታህን ማለት !

በግል ጥፋቱ — የኖረን ሲኮንን፤
ትርጉሙ አይገባኝም — የይቅርታ ብይን !

“የወጋ ቢረሳ”— ይላል ያገሬ ሰው ፤



ተወጊ እንዳይረሳ — ሲወጉን ወላለው ።

ሳንን መወጌ — ለመለኪያ መጠን ፤
መሆኑን ያሳያል — ለመቀመር ዕርከን ።

ወጊና ተወጊን — አቅርቦ በተራ ፤
ሎጂኩን ደርድሮ — ተርትሮ ሲያብራራ !

በሌላም ብሒሉ — ሲያስረዳ እያተተ ፤
“የተወጋው ሳለ — ደም የነካው ሞተ”፤
ይላል ያገሬ ሰው — ለሐቅ የቃተተ !

አላንዳች ምክንያት —“ደም መላሽ”አትልም ፤
እናት ስታወጣ — ለምትወደው ልጅ ስም !

የልቡን ፈጽሞ — ይቅርታህን ለሚል ፤
ደም መላሽ ምሱ ነው — በቀን ለሚያታልል ።

እንጀቱን አርሶ — ይቅርታህን አርሳው ፤
ይላል አጅሬ — እሱ ምን ደንታ አለው !

ከሆነ እንድረሳው – እሱ እሚጠይቀኝ ፥
"መርሳትን ነው መርሳት"– እኔ ግን ያለብኝ !

ይቅርታን ጠያቂ – የወንጀል ግብረኛ ፥
ከፍትሕ አያመልጥም – አይሆነውም ምልጃ !

ይቅርታን ጠያቂ – የወንጀል ደረሰኝ ፥
ቅጣት ተገቢው ነው – ላጭበርባሪ ለማኝ ፥
ያንጀቱን አድርሶ – ለግል ተሳሳትኩኝ ።

ማነው የሚለቀው – በላለ ይቅርታ ፥
በኢሰብዓዊነት – ኖሮ ሲያንገላታ ፥
መሰሉን ሰው ፍጡር – ከድባቅ ሲመታ ።

ማነው የሚምረው – ከፍርድ በላይ ቆሞ ፥
ተሳስቼ ነበር – ቢለን ዛሬ አርምሞ !

ደግሶ ይቅር ይበል – እምኖ በስሕተቱ ፥
ምን ሰበብ ልንሰጥ ነው – ለጠፉት በከንቱ ፥



ለረገፉት ነፍሳት – በገዳይ ለሞቱ ፥
ኅልነታ ወርደው – ላልተመለሱቱ !

የሙታኖች ወኪል – ምንጊዜም ሕያው ነው ።
ጠግር ሞታቸውን – የሚከታተለው ።

እንዴት እንደሞቱ – ለምን እንደሞቱ ፥
እስካሁን ድረስ – አይችልም እንጀቱ ፥
ያጋልጣል እንጂ – ለፍትህ ለቆሙቱ !

ገዳይ ካልተቀጣ – በፈጸመው ተግባር ፥
ተከታዩ ትውልድ – ማንን አይቶ ይማር ፥

የኖረበ ሲማወት – ያ ሁሉ መበላታ ፥
ከቶ እንዴት ይታለፍ – በተራ ይቅርታ !

ከፍትሕ ሸንጎ ቀርቦ – ለሞት ሆነ ሕይወት ፥
እንደየወንጀሉ – እንዲፈረድበት ፥
ከሆተቱ ለዚህ ነው – የፍትሕ የርትዕ ምርባት!

ይህ አይነቱ ድርጊት — መበቀል አይደለም ፥
ፍርድን መስጠት እንጂ — ለማስከበር ሰላም !

ንጹሐን ቀጥቅጦ — ከከፋ በኋላ ፥
ይቅርታ ቢጠይቅ — ስንቱ መርበሳ ፥
ትርጉሙ ምንድር ነው — የይቅርታው ውሳ !

ደም ዕንባ ሲያስለቅስ — የኖረ ወንበዴ ፥
ተሳስቼ ነው ቢል — ቧልት አይደለም እንዴ !

ስሕተቱን አምኖ — ይቅርታችሁን ቢል ፥
ቢማለድ ቢማጠን — በአማልክት ቢምል ፥

ማነው ችሎ እሚሰጥ — የምሕረት ይቅርታ ፥
ለነፍሰ ገዳይ ሰው — የሕይወት አለኝታ ፥
ከዚያው ካንዱ በቀር — ከፈጠረው ጌታ !
ወይም የሕዝብ ፍትሕ — ቢያገርም ቢፈታ !

ከቶ ማነው የሚል — በይቅርታ ወንፊስ ፥



ይታለፍ እንተወው — እንደዋዛ ፈሰስ ፥
እንዴ ሆዷልና — ወልሶ አይታፈስ ፥
በዕብሪት ተወጥሮ — ቢያጠፋም የሰው ነፍስ !

ይቅርታ ምንድር ነው — የጅል ሰዎች ፈሊጥ ፥
የፍርድ የፍትሕ ዓውንት — በነፍስ የሚያፋጥጥ ።

ጥሕፉን የሰው ልጅ — ዘር ብሎ ሲበላት ፥
ጎልጎታ አውርዶ — ስንቱን ጉብል ወጣት ፥
ታሪክ ሕግ የጣሰ — ሀገር የሚያራቁት ፥
በባዕድ ውክልና — እጥፉ ሕዝብ ሕይወት ፥
ትላንት ነገን ፍቶ — ለዛሬ እሚጓጓት ፥
ከግለ እሱ በቀር — ሌላ የሚያይበት ፥
ፍጹም ነይን የሌለው —ሽውራራ ውት ዓያት ፥

እረ ለመሆኑ — ቢጠይቅ ይቅርታ ፥
ሊግር ነው ወይ በርግጥ — ሊያገኝም እፎይታ !

ይህግ ከሆነ — እቅጩ ፍትሕ ቀለለ ፥

ምሰሶው ተነቅሎ — ጀሐነም ተጣለ ፥
ግለት አይደለም ወይ — ፍርድም ተጓደለ !

ይቅርታ የሚያልፈው — ከሆነማ ወንጀል ፥
ሰዎች ተሰብስበው — ነቃቅለን እንጣል ፥
አብያተ ፍርድን — እንድደን እናቃጥል ፥
ፀወደ ሕግጋትን — ከስሩ እንንቀል ፥
ስሕተት እያለ — ገዳይን ላይገድል ፥
ነፃ ከለቀቀ — ወንጀልና በደል !

ስሕተት እያለ — ይቅርታ ከሰጠ ፥
ፍትሐ ብሔር ይጥፋ — እንዲያ ከግነጠ !

ጅራፉም ይተርተር — እስር ቤቱም ይጥፋ ፥
ይቅርታ ካለፈው — ሁሉ ሰው ሲያጠፋ !

ያለፈው ይታለፍ — እንጣለ ይረሳ ፥
የሚሉ ውድኖች — ይቅር አይነሳ ፥

ምን ግለት እንደሆነ — ብሒሉ አይገባኝም ፥



የገደለ ይኑር — ሎጂክ አያስገኝም ።

እንደጧልተኞቹ — በይቅርታ ብናልፍ ፥
አይወቅሰንም ይሆን — የወታን ነፍስ በግፍ !

ኅልኅታ ያለው — አጥንቱ አፅማቸው ፥
አይታዘብ ይሆን — ሲኖር ገዳያቸው !
እሱ ሲንዘባነን — እነሱ አፈር በልተው !

ግለትስ አይሆን ወይ — የገደለ ይኑር ፥
አለፍትሕ ብናልፈው — ፀረ ነፍሱን ፍጡር !

ሌላው ሌላው ቢቀር — ያለወንጀላቸው ፥
ታርደው የረገፉት — ምን ይለን አፅማቸው !

እኛን ቋሚዎቹን — እርሱት ከተባለ ፥
መርሳትን ነው መርሳት—ሐቅ አስከበደለ !

መጋፋት ነው በርግጥ — የፍትሕ የርትዕ ከልል ፥
ይቅርታ እርጉ ግለት — ለፈጸመ ወንጀል ።

የፍትሕን መሠረት — ማናጋት ነው በርግጥ ፤
በይቅርታ ካለፍን — ያን ሁሉ ጋጠ ወጥ !

ሆን ብሎ አውቆ — የጋጋን በጥፊ ፤
ይቅርታ ቢጠይቅ — እንዳልሆነ አጥፊ ፤
በምሕረት ማለፉ — ያን መሳይ ቀጣፊ ፤
በፍትሕ ማሳነስ ነው — መሆንም አሻፊ ፤
በነፍስም መቀለድ — ወባ አይነት ነዳፊ !

ብልጣ ብልጥ ነኝ ብሎ — ሞሌ እሚበርባሪ ፤
የልቡን ፈጽሞ — በአፍ ቀባባሪ ፤
ይቅርታ እሚጠይቅ — እንዲያገኝ መሐሪ ፤

መርሆው ነው እሱ — ያለፈውን እርሳው ፤
አፈር ሲያስግጥ ኖሮ — እሱ ምን ደንታ አለው !
ሕይወት በሕይወት ውስጥ — መሆኑን አያውቀው !

ለሞትም ለሕይወት — ፅሴታዊ አይነት ፤
በርግጥ በዚህ ዓለም — ፍትሕ መኖር አለበት ፤



ውትሮቶ አጋልጦ — የወንጀልን ክሥተት ፤
ብያኔ የሚሰጥ — ለሰው ልጅ ሰውነት !!

ይቅርታ የሚሉት — የብልጥ መሸንገያ ፤
መታረም አለበት — ከሞሌዎች ጉያ ።

ይቅርታ ከቸረው — የፍርድን መራጃ ፤
ላያስፈልገን ነው — ማዉድ እረም ዋጃ !
እንክርዳድ ቢበቅልም — አብሮ ከገብስ ካጃ !

እንዲያገግ ከሆነ — ዳብሎ ዲያብሎስ ፤
ከቶ ለምን ይሆን — ወይስ በምን መንፈስ ፤
ሲታጠል መናፉ — ጃነም እንጦርጦስ ፤
በግፅት መግባቱ — ከድቅድቅ በርባርስ !

ሒትለር ሙሶሊኒስ — እረ ለምን ጠፉ ፤
ይቅርታ ከሆነ — የፍትሕ ምዕራፉ ፤
ስሕተት ተብሎ — ለምን አልታለፉ !

ብዙ ምሳሌ አለ — እኔ አልዘረዝርም ፥
ምንዝር ምን ይጠቅማል — ከማንዘር አይቆርም !

ደርዘን ሙሉ አመታት — ከባዕዳን ጋራ ፥
ሀገር ለመበተን — ሲያሳውር ሲያደራ ፥
የኖረ ያ ትንታግ — ቢተርክ ቢያወራ ፥
ሰላም ሰላም ብሎ — ቢዋራ ቢያቅራራ ፥

ማን ይቀበለዋል — ቢያጓራ ቢጮትት ፥
ከዉከቱ በፊት — ፍርድ ማግኘት አለበት ፥
የሕዝባችንን ፊት — እርጩሜ ግርፋት ፥
ወይም በነ ገጹን — ቡራኬ ምርቃት !

ሕዝብን እያናዉ — ሰላም ሰላም ማለት ፥
ሥርዓተ ብተናን — በሕግ ሲሠራበት ፥
ወንዝሩኝ እያለ — እልታኝ ለመንግሥታት ፥
የፍትሕ መደብዘዝ ነው — የመጥፋት ምልክት ፥
እንዲህ እንዲህ ያለው — ያባበጠ ዕብሪት !



ዕፁብ ድንቅ እንጅ ነው — ካማለት በስተቀር ፥
በንይን እውነቱ — በድፍረቱ እንኳር ፥
ይህን ወሰል ድርጊት — ሀገር የፈታ ነውር !

እረ ማነው ደፍሮ — ይቅርታ የሚያደርግ ፥
ያታገለበትን — ለነፃነት ለሕግ ፥
ለዘመናት ዕድሜ — በትውልዶች ፊለግ ፥
የሞተበትን ምድር — ያቆየውን ምሽግ ፥
የሕዝብ ሀገር ንዶ — ሰላም ለሚፈልግ ፥
ጥራኝ አይመስለኝም — ለሱ እሚያደገድግ ፥
ብያኔውን ሳይሰጥ — የሚተው አለወግ !

ሌላው ጉዳይ እንኳ — ቢታይ በለዘብታ ፥
በሀገር ደባ ግን — የለም ቀልድ ይቅርታ !

ያለፈውን እርሳው — ብሎ በርግጥ ቢደርቅ ፥
ማነው ተቀባዩ — እብሮ እሚጨግለት !

ከሆነ እንድረሳ — እጥፊ እሚጠይቀኝ ፥
በመርሳት ነው መርሳት — እለቀለው ይገባኝ ።

ስንቱ አጭበርባሪ — ምኞቱን እንግዛ ፣
ተበድሮ ወስዶ — እቃዬን ተውሶ ፣
ይቅርታህን ይላል — ሰበብ እንተርሶ !

ይቅርታ ምንድነው — በደል መሸፈኛ ፣
ሌላውን አድምቶ — እሱ የሚተኛ ፣
እንዱን አስጨንቆ — መሆን ደስተኛ !

ምሕረት እርቅ ሰላም — እንዲሁም ይቅርታ ፣
ለወንጀል አይደለም — መስጠት በይሉኝታ ።

ያለፈውን እርሳው — ብሎ የሚያቅራራ ፣
እየታሰበው ነው — በደል እንደሠራ !

ልቡ እያወቀው — የሰው ሚስት አማግጦ ፣
ድንገት ሲነቃበት — ካለበት ፈርጥጦ ፣
አማላጅ ይልካል — አረጋዊ መርጦ ፣
ባስታራቂ ጥበብ — እንደሚድን ቆርጦ !



ጉዳቱን ፈጽሞ — ቢጠይቅ ይቅርታ ፣
ስሕተት ሠርቻለሁ — እያለ ቢያምታታ ፣

ይቅርታን መስጠቱ — ፍርድን ማቅለት ነው ፣
ለፈጸመው ወንጀል — ቅጣት ባይሰጠው ።

የሰው ቤት እመቤት — አስነክሶ ፍራሽ ፣
ሲያዝ ማረኝ ተወኝ — የሚል ወሲብ ቀማሽ ፣
ተቀባይ የለውም — ነውና ሕግ አፍራሽ !

ስንቱ Social garbage — የኖረ ወገን ሲያርድ
ማነው የሚምረው — ኋላ ቢቀላምድ !

ዛሬ ይቅር ብሎኝ — ነውና ስሕተት ፣
ብሎ ቢጠይቅም — በሽፍንፍን ፀፀት ፣
መርሳት አንችልም — የሠራውን ትላንት ፣
በንጹሐን ሰዎች — የኖረ ሲጫወት !

እንደሱ ፍላጎት — ተገድለው ለሞቱ ፣

ግን ሊሆናቸው ነው — ጠበቃ ካንጀቱ ፤
ለትናንት ሕያዋን — ዛሬ አፈር ላሉቱ !

ስለዚህ ነው — የምለው ጠንቅቄ ፤
መርሳትን ነው መርሳት — የምለው አጥብቄ ።

እውነም ልጠቃቅስ — የይቅርታ አቃቂር ፤
አይነቱ ብዙ ነው — ብዙም የሚያናግር ።

ነይናቹ ፈርጦበት — ዕውር የሆነ ሰው፤
ያንን አፍራሹን ሰው — በርግጥ ይቅር ይለው
ካንጀቱ ከልቡ — ይሆን ይታረቀው?

እግሮቹን ቆርጦበት — ያረገውን ሰንኩል ፤
በስሕተት ሳይሆን — በታቀደ ተንኮል ፤
ይቅርታህን ቢለው — ቆራጩ ሊቀበል?

እጆቹን ነግምዶ — ያረገበት ጉንድሽ ፤
ቆራጭ ባለጅ ሆኖ — ባለም ሲምነሸነሽ ፤



የተነወደበት — በነግጅ ሳይወርሽ!

የማይወስል ትንግርት — ይቻላል አታውሩ ፤
ይቀርባታል ለፍርድ — እንደየምግባሩ !
የበደለ ሁሉ — ይገባል ቀንበሩ !

ቢሆን የሚያስፈልግ — መለገሥ ይቅርታ ፤
ባለቤቱ ብቻ አይደለም — ምሕረት ሰጭ ጌታ ፤
ፍትሕም ጭምር እንጂ — ሰሚ አቤቱታ !

አለያማ ድኩም — ሲታመስ ሊኖር ነው ፤
የፍትሀን ምንነት — ጥቅሙንም ሳያውቀው !

አለያማ ድኩም — በፍርድ በር ሳይገባ ፤
ሆኖ ሊኖር አይደል — የኃያል ሰለባ !

ልጆቹን ለባሩድ — የገበረች እናት ፤
ልጆቹን ለጥይት — ያበረከተ አባት ፤
አንጀት አርባቸው — የኖሩት በጎበት ፤

ሳምባቸው ተቃጥሎ — ያሉ በኩላሊት ፥

ይቅርታ አድርጉልን — ተብለው ቢጠየቁ ፥
እንዴት ሊያስችላቸው — ፍርድን ሲጠብቁ !

ከኢምንት ተቆጥሮ — አጥፊ እጅ ካወጣ ፥
ትውልድ እንዴት ይማር — ወንጀል ካልተቀጣ !

ማነው ፈራጅ ለኛ — ያጓለውን ምላሽ ፥
ሕዝባችን ይሰማል — የኖረው ሲከላሽ ።

ማነው ወንጀለኛው — ለሚልም ጠያቂ ፥
ሕዝቡ ይመልሳል — ማስረጃ አለው በቂ ።

ፍርድና ፍትሕ ርትዕ — ካልመየረ ወንጀል ፥
ሕይወት ሥርዓት ያጣል — ይሆናል ጅላጅል ።

ሞራል ይሳሳና — ንቅዘት ይዳብራል ፥
ፍትሕ ጉልበት ኖሮት — ወንጀል መቅጣት ባይችል ።



ወንጀለኛስ ቢሆን — እንዴት ግብሩን ይርሳው ፥
መሰሉን ሰው መጉዳት — ለምን አይፀፀተው ።

የተጎዳው — ምን ጊዜም አይረሳ ፥
ቀን ነግቶ እስኪመሽ — እያየ አበሳ ።

ዓይኑ የፈረጠው — እንዴት ዓይኑን ይርሳው ፥
ቀኑ ጨለምበት — ብርሃን የተቀማው ፥
ወጣ ባለ ቁጥር — ሲሄድ የሚደፋው !

ጆሮውን ያጣውስ — እንዴት ጆሮን ይርሳው ፥
መስማቱ ተሰናት — ደንቆሮ የሆነው ፥
ከውጪታ ፀጋ — ተነፍጎ የኖረው !

ተፎንኖ አፍንጫው — አፍንጫ እንዴት ይርሳ ፥
ከማሽተት ተጫልቶ — ሲያይ የኖረ አበሳ !
እግሩን ያስቆረጠስ — እንዴት እግሩን ይርሳ ፥
ሲያነክስ የኖረው — ስንት ወገን እንካሳ !

ይቅር ላሳሁ ማለት — የሕዝቡ ፋንታ ነው ፥

ይቅር ለእግዜር ማለት — ተፀዳይ ክፍል ነው ፥
ወንጀል ግን ጠባሳ — ምንም ቃል አይፍቀው ።

ጠባሳው ያ ወንጀል — አይታይ በቆዳ ፥
በውስጥ በልብ እንጅ — በረቂቅ ሠሌዳ !

ቀሌ የማይጠፋ — በደም የተከፋ ፥
ቢፀፋ የኖረ — የቸሐንን ገፋ !

በነፍስ ብፅርነት — በልብ የተሻፈ ፥
ወንጀል አይታጠብ — ተብሎ አደፈ !

ከልብ እስካልወጣ — ተንዶ የማይወርድ ፥
ታርጋው ወርግኮ ነው — ቀሎ እማይወገድ !

ወዳረኛዬ ላይ — ወቋጠሬያ ላብጅ ፥
ለዚሁ ለማኖኝ — ቢፀጅንም ባይፀጅ ።

በፍልስፍናና — ደግሞም በሃይማኖት ፥
ሞራል ከልል አለ — ደንግገው ያቀዩት ።



ሐተታ ዝርዝር ውስጥ — በሰፊው ባልገባም ፥
የይቅርታን ጥቅም — አስተምረናል በዓም ።
የኔም እቋም ቢሆን — ከነሱ አይወጣም !

ሌላውን ገጽታ — ከላይ ማሳየቴ ፥
ፈላጊ ይኖራል — ብዬ ነው ማተቴ ።

አይነቱ እየታየ — ይቅርታን ወለገፖ ፥
ተገቢ ይመስለኛል — ለሰው ልጆች ወንፈስ ፥
ሁላችን ተዓልተን — ከምንም እንደርስ !

የግሌን ትይታ — ባጭር ከተነፈስኩ ፥
ለብዙኃኑም ድምፅ — ነኝ የተገፀረከኩ ፥
በውሳኔው የማምን — ሀገሬ ኖርኩ አልኖርኩ !

ላኛው ጭታ ኹው — ወዉኔው ምስለኔው ፥
ለተዋለደት ግፍ — የግሉን ፍርድ ሰጭው ፥
ባገር ውስጥ ያለው ነው — ሲጠበስ የኖረው !

ቢፈልግ ይምራል — ባይፈልግ ይሥቅላል ፥

ለሰላም ከረባም − በይቅርታ ያልፋል ፤
አለያም አምርሮ − ቀቅሎ ይጠብሳል ፤
መብቱም ነው ግዴታው − እሱው ይወስናል ፤
ሲጠበስ የኖረው − በሆነው ባልሆነው ፤ በወንጀል በእከል !

የፍትሕና የርትዕ − መሠረተ አቋምም ፤
ማጥፋት ብቻ አይደለም − ይችላም ግረም !

ይህም በመሆኑ − ግድ ፍትሕ በዓለም ፤
ሰውን ለማዳን ነው − ከወንጀል ፅኩይ ደም ።

በዚህ በምድር ላይ − ፅኩይ ክፋት ነገር ፤
ተነቅሎ እስካልጠፋ − ከነሥንኮፉ ጋር ፤
ወና ሕይወት የለም − ነፃና ሰበ ፀር !

የወንጀል ሁሉ ነፍስ − ኢቨል ካልተቀጣ ፤
ምንጊዜም አይተውም − ከማስከተል ጣጣ ፤
በሰዎች መካከል − ሰላም አያሳጣ !



ሕዝባችን አንድ ቀን − በፍትህ ሲበረታ ፤
ክፋትን መጥረጉ − የግታ የግታ ፤
አምናለሁ አይቀርም − የተመቸው ለታ !


ወንጀልም በተራው − አይቀርም ይጣራል ፤
በፍትሕ ሰፈሮች ላይ − ፈስሶ ይበጠራል ፤
በፍርድ ወንፊቶችም − አይቀርም ይነፋል ፤
ግርድስ ሆና እንዳያልፍ − በቅጥ ይመለታል ፤
ማንም ሰው ይወቀው − ትንቢት ነው ይከ ታል ፤
ሁሉም እንደሥራው − ለሚዛን ይቀርባል ፤
እንደየአይነቱም − ይነጣል ይነድፋል !

ግን እስከዚያው ድረስ − ያ ፍርድ እስኪመጣ ፤
መርሳትን ነው መርሳት − ወንጀል እስኪቀጣ !

* To err is Human ,

To forgive is Divine የሚለው ፈረንጃዊ እንቆጽ ያልተሰመጠኝ ፥ መልዕክቱ እንዳይከለስና እንዳይበወዝ ፈርቼ ነውና አትዘከሩብኝ ።

# ምን አይነት ዘመን ነው?




የትዝብት ቢጋር !

ፍንደታ - ቁ 98

# መዘክርነቷ

ለዚህ ላለንበት ዘመን ትውልድ ።




ይህች አጭር ግጥም ፥ የአንድ አሳዛኝ አጭር ልቦለድ ጭማቂ ናት ። የልቦለዱ ይዘታዊ መዋቅር ፥ ከዚህ ጽሁፍ በስተራስጌ የሚታየው ቢጋር ነው ።

የልቦለዱ ታሪክ ርዕስ ፥ ባሩድ ያጨሰው ቤት የሚል ነው ። ታሪኩ ፥ እናትና አባት ፥ ትዳር መሥርተው አምስት ልጆች ያፈራሉ ። ልጆቻቸውም ለአቅመ አዳም ሲደ ርሱ ፥ በየበኩላቸው ፥እንደግላዊ ምርጫቸው ፥ ሚስቶች ያ

ገባሉ ። ( የትዳር ጥንዶቹ አዋጋጥ ግብቶቻቸው ፥ ከየት ኞቹ ትውልደያውያን ወገኖቻቸው እንደተገኙና እያንዳንዱም የ ቤተሰብ አባሎቻቸው በጊዜው ለነበረው የየትኞቹ የፖለ ቲካ ድርጅቶች አባላት እንደነበሩ ለማወቅ ፥ ከላይ የቀረበ ውን ዑደታዊ ቢጋር ያገናዝቡ )

ባለፉት ወንታ አሥርታት በበረቀው ፍላና ወከፉ ያልተጠበሰ ወገን እንደሌለ ሁሉ ፥ የዚህንም ቤተሰብ አባላት በሙሉ ፥ ከገፁበት ገብቶ እርስ በርስ በማጋጨት ወ ዝብሯል ። ወንዴው ወላጅ አባት ፥ አርሞአዊ ባለቤታቸውን አግብተው ሲኖሩ ፥ ያፈሩአቸው አምስት ልጆቻቸው ፥ በወ ለለደው ዱብ ዕዳ ፥ እንደፖለቲካ ዝንባሌያቸው ምርጫ ብቻ ሳይሆን ፥ በሁኔታውያን ሥርጊነት ጥምር ፥ ለተለያዩ ድርጅቶች ፥ የምሥጢር አባላት ይሆናሉ ።

በምድብ ሥራው ምክንያት ፥ ተንዛሆ የሄደው ልጃቸው ፥ ከአንዲት የአፋር ቆንጆት ላይ ፍቅር ጥሎት ፥ ወዲያው ትዳር ይመሠርታል ። የፍቅሩ ጆኬ አልከፋውምና በ ሕፃናት ምርት ላይ ጥሎታል ። እሱም የአባቱን ፖለቲካዊ



ፊር ተከትሎ ፥ የኢድዩ ምሥጢራዊ አባል ሲሆን ፥ አቶሬቱ ባለቤቱም ፥ቀድሞውኑ የማኅበረ ሰብ ድርጅት አባል ነበረች። የቤተ ሰው ቀዳማይ በኩር ልጅ ፥ የደርግ ተስፈንጣሪ ሁድ ን ለነበረው ሠደድ አባል በመሆኑ ፥ ለልዩ ከፍተኛ ተልዕኮ አሥመራ ሄዶ ሲኖር ፥ ከአንዲት ብሌናዊት ጋር ተ ጋብቶ ፥ ትዳር ይመሠርታል ። ባለቤቱም ፥ በተወለደችበት አካባቢ ግዳጃዊ ልማድ መሠረት የጀበሐ ድርጅት ምሥጢራዊ አባል ነበረች ። የዩኒቨርስቲ ምሩቅ የነበረው የቤተ ሰው ሌላው ልጅ ደግሞ ፥ ከቀደምት ታጋዮች አንዱ እንደመሆኑ የፖለቲካ ምሥጢራዊ አባልነቱ ፥ ለኢሕአፓ ነበር ።

በትምህርታዊ ሙስኩ መሠረት ፥ የከርሠ ምድር ም ሁር ( Geologist )በመሆኑ ፥ ለቤንዚንና ጋዝ አሰሳ ተግባር የተሠማራ ፥ የማዕድን ሚኒስቴር አባል ስለነበር ፥ በተመደበለት የሥራ ተልዕኮ ምክንያት ፥ በም ድረ ዑጋዴን ፥ ለብዙ አመታት ቆይቷል ። ጥቅማቸውን ለማ ጋለፍ ፥ ኃይላቸውን መከታ አድርገው ፥ በሀገራችን ውስጥ ይፈራረቁ የነበሩት እነሁለቱ ልዕለ ኃያላን ፥ ይህን የቢ

ተ ሰብ አባል ደጋግመው ከሥራ እስከማስወገድ ድረስ ፍዳውን ቢያበሉትም ፥ በበኩሉ ትዳር መሥርቶ ፥ የአምስት ሕፃናት አባት ሊያፈራ የቻለው ፥ ባካባቢው ያገኛትን አንዲት ሱማሌያዊት ቆንጆ ፥ በሕግ አግብቶ ነው ።

ሚስቱም በበኩሏ ፥ የአካባቢው የሱማሌ ማኅበረ ሰብ ድርጅት ምሥጢራዊ አባል ነበረች ። የቤተ ሰው የመጨረሻ ልጅ ፥ ወሊሰን ለሚባለው ድርጅት ምሥጢራዊ አባል ሰለ ነበረ ፥ ሙሉ ሕይወቱን ያሳለፈው ፥ በድርጅቱ ጽሕፈት ቤት የምሥጢር ቋሚ ሠራተኛነት ነው ። ሚስቱ ግን፥ አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገች ፥ ከአድዋ ወላጆች የተገኘች የለየላት የወያኔ ቡድን ምሥጢራዊና የውስጥ አርበኛቸውም ነበረች ።

ዘርፈ ብዙ ከነበረው የቤተ ሰው አዝማዶች ውስጥ፥ ከብዙዎቹም አክስቶችና አጎቶች ውስጥ ፥ ሁለቱን ብቻ በመምዘዝ ፥ በቀረበው አውዳዊ ቢጋር ላይ ሊመዘገብ የቻለበት ልዩ ምክንያት አለ ። ይኸውም ፥ ነዲድ ናፍቃ አቀጣጥለው እንዳባባሱት ሰደድ እሳት ፥ ኋላ ለተቀጣጠለው



ለዚያ ሰፊ ቤተሰብ ፥ እንደተጨማሪ ነዳጅ ቤንዚን ሆነው ወሬ በቤተ ሰው ውስጥ በማመላለስና በመነስነስ ፥ ይበልጥ ቃጠሎው እንዲጧጧፍ ፅኑዕ አስተዋፅኦ ያደረጉ በመሆናቸው ነው ። በአሁኑ ጊዜ ፥ ከዚያ ትልቅና ሰፊ ቤተ ሰብ አባላት ውስጥ፥ ምን ያህሉ ቁጥር ለአጥቂነት ተርፎ እንደሚገኝ ፥ በውል የሚታወቅ ባይሆንም ፥ ዘመን ወለዶ ባስገኘው የዱብ ዕዳ ክሥተትና ባስከተለውም የእርስ በርስ መባላት ዕልቂት ፥ ቢያንስ ቢያንስ የአንድ ታዳጊ ትውልድ አንጋፋ ቅርንጫፍ የሆነ ፥ የአንድ ቤተሰብ አባሎች መፈጀጀቱን ለማዘከር ፥ ይቺ ኩንትሽ ግጥማዊ ወርዶ በርቃለች ።

## ምን አይነት ዘመን ነው?

ያለፈን ቅርብ ዘመን — በትዝብት ያጠና ፥
ብዙ ታሪክ ያያል — የሚሠብር ኅሊና ።

ከሁሉም ከሁሉም — አንጀት የሚበላው ፥
ቤተ ሰብ ውስጥ እንኳ — ሰላም መጥፋቱ ነው ።

የጨነቀው ዓሌ – ይህን አስመልክቶ ፤
ዘመኑን ይወቅሣል – አጥፊውን ሰው ትቶ ፤
እንደሚከተለው – መርገም አዘጋጅቶ ።

ምን ያለ ዘመን ነው – ያረጀ የጃጀ
የራሱን ትውልዶች – እርስ በርስ ያፋጀ !

ምን ያለ ዘመን ነው – የጠፋበት ውላ ፤
የገዛ ወንድሙን – በወንድም ያስበላ !

ምን ያለ ዘመን ነው – የተገላበጠ ፤
ክቡሩን የሰው ልጅ – ያን ባሩድ ያስጠጠ !

ምን አይነት ዘመን ነው – ናላው የዞረበት ፤
የገዛ ራሷን ባል – ሚስት ያረደችበት !

ምን ያለ ዘመን ነው – የዘመኑ ቀውጢ ፤
አባት ያረደበት – ልጆቹን በውጊ !

ምን ያለ ዘመን ነው – ሰው የረከሰበት ፤



ልጅ እናቷን እሞራ – የገረፈችበት !

ምን ያለ ዘመን ነው – ፍቅር የጠፋበት ፤
ጥላቻና ፍርሀት – ጥል የነገሠበት !

ምን አይነት ዘመን ነው – ያበዛ ዘረኛ ፤
አንዱ ለሌው ሰው – ጨርሶ እማይተኛ !

ምን አይነት ዘመን ነው – የዞረበት ውላ ፡
እናትና ልጅን – እርስ በርስ ያባላ !

ምን አይነት ዘመን ነው – ፍቅር የከሣበት ፤
ባልን ከሚስቱ ላይ – የሚያፋታ ድንገት !

ምን ያለ ዘመን ነው – ዘመኑ ግራምቢጥ ፤
ታናሹ ታላቁን – ያስታቀፈ ረመጥ !

ምን ያለ ዘመን ነው – ክብረ ሰብ የላጨ ፤
ያንጀት ጓደኞችን – እርስ በርስ ያጋጨ !

ምን አይነት ጊዜ ነው – የተገላበጠ ፤

ያለበቂ ምክንያት — እያቁነጠነጠ ፥
ጓደኛን ጓደኛ — ሳያኝክ ያስዋጠ !

ምን አይነት ዘመን ነው — ባለ ልዩ Dialect ፥
ዜጋን የሚያስቀይር — ሙኅድና passport ፥
ከራስ ሀገር ገብቶ — ነብኝቶ ለመውጣት !

ምንኛ ዘመን ነው — ድምባሹ የዞረበት ፥
አይጦች ጎልብተው — ድመት የበሉበት !

ፍየል ነብርን አስራ — ያሾፈችበት ቀን ፥
መቼ ታይቶ ያውቃል — ይህን መሳይ ዘመን !

ምንኛ ዘመን ነው — ዘመን ተልካሻ ፥
መለየት ያቃተ — አህያን ከውሻ !

ምን ያለ ጊዜ ነው — የተንሸዋረረ ፥
የራሱን ምሁራን — ካገር ያባረረ !
ቀሪውን ዘባናድ — አጥና የዘረረ !



ምን ያለ ዘመን ነው — የባዕዳን ከርማ ፥
ሌላ ሀገር ገብቶ — ጊደር የሚቀማ !

ምን አይነት ዘመን ነው — ዘረኝነት ሰበብ ፥
ባርነት ወልሶ — እንዲያ እሚያከናንብ !

እርስ በርስ አባልቶ — ቤተ ሰብ ደምሳሹን ፥
ከቶ ምን ይሉታል — ዘመን ይህ አይነቱን !

# አውሬ ቡራቡሬ!



# መዘክርነቷ

በልዩነት ባይሆን ፥ ልዩነት በሚፈጥረው አጋጣሚ ሁሉ ፥ ግፋዊ እንጀራቸውን ለማቋሰል ለሚንሰፈሰፉና ለሚንሞለሞሉ አድርባይ ነቀዞች ሁሉ ።



ሲለብሱ፥ሰው አይመስሉምን?



# አውሬ ቡራቡሬ!

በተፈጥሮ ባካባቢ — በተመሳሳይ አስገዳጅ ኃይል ፥
እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ — የተገኙ አዕዋፍ አካል ፥

ይኖራሉ — በዚህ ዓለም ፥
በየረድፉ ተሠልፈው — ለሕላዌ ወለም ዘለም ።

እንደአይነታቸው እንደባሕርያቸው — ሲወደዱ በየክፍሉ ፥
የጋጣ ከብት የቀንድ ከብት — ባለአክናፍ ባለሰኮና ሙሉ፥
እግር አልባዎች ወርዋሮዎች — ለግዳዎች የሚያመሰኩ ሁሉ፥

ቀለኛና ደገኛ — ወይ እንስሳ ወይም አውሬ ፥ ሌላ ሌላም
እንዲያም እንዲያም ይባላሉ ።

ስለ አይነታቸው ትተን — ስለባሕርያቸው ብንተነትን፥
ያሳዩናል ምናምንቴ — በተፈጥሮ ብዙ እንከን !

ሥጋ በላው — ዕፀ በላው ፥
ባለቀንዱ — ባለጭራው ፥
ባለሸኮና — ከፍ ዓግው ፥
እየገተረ እያመሰኳ — ወደ ከርሡ የሚውጠው ፥
ብዙ ታንኪር ብዙ ጠባይ — ብዙ ትንግርት ታሪክ አለው ።

ፍላጎቱና ተምኔቱ — እንደተፈጥሮው ሆነና ፥
ዕፀ በላው ከሥጋ በላው — አይገናኝም በጥምና ፥
በየተፈጥሮ ምግቡ — የሌለው ተብሎ ጎሊና !!

ግባቸው ሆና ለየቅሉ — በየከርግቸው አቅጣ ፥
ለቅንጣቢ ሥጋ ሲንሰፈሰፍ — መስሉን ሲገጥ በወጣ ፥
ባለቀንዳውም ሲጥጋ — ጉንጥ ለማትሞላ እንገጣ !



እንስሳውና አውሬው — ወገን ለይቶ ኖሩ ፥
እየመሸ ይነጋል — ሌሊትና ቀኑ በየተራ ፥
የዓለም ባሕርይ ሆና — እርስ በርስ መፋተግ በኑሩ።

ለዕፀ በላው ፍጡር — የሥጋ ነገር ምንም አይደል ፥
የሥጋ በላው ፍጡርም — የዕፀዋት ነገር እንደማይቀበል ፥
Carnivorous,Omnivorous-እያለ ፈጥሮ ከለለ፥
በሁሉም በንድ ሲታወቅ — የየተፈጥሮአቸው ሁሉ አመል !

ያ ትልቁ መፈታቀድ ነበረ— ሊያቀራርባቸው የቻለ ፥
ሥጋ በላዊን ድመት — ከሳር በላዊ ላም ጋራ ፥ ለ
ግላላዎች እያለ ፥
ባንድ ጣራ ከልል ስር — በጉንና ውሻውን በእክብር
ት የተቀበለ ።

ሰው ግን በበኩሉ — ለሁለቱም ባላ ሆና ፥
ከአውሬውም ከእንስሳውም — አለ ከላይ ደምና !!

በየራሳቸው ምክንያቶች — እንደባሕርያቸው ቦድነው ፥

# አውሬ ቡራቡሬ!



ባይጣጣሙ እሱ — ዘንድሮም ሆነ እንደእምናው !

ድመቶችም ይላሉ — በበኩላቸው ሲያትቱ ፥
አይጥ ግደን ነው ግባችን— የተወደደልን ተግባር ከጥንቱ !

በወተትና በሥጋ እታሉ — ካውሬነታችን ያገረን ፥
ከነብሩና ከአነሩ — ጠፍራዊ ዝምድና የከዳን ፥
አሁንም ያው ሰው ነው — ለማዶች እያለ ያስገበረን!
ለስለሳ ባሕርያችንን ተገን አርጎ — አስገብሮ ይዞን ዘ ወፋ ፥
ጥርጥያው አርጎን ይኖራል — አይጥ አሁሉን እንዳይበላ !

የቀረው ቢቀር እንኳ — ከሚቀርቡን ወገኖች በተዘምዶ!
ከነብር ከአነር ጋር — እንዳንገናኝ ዘዴ ገምዶ ፥
ጠፍርን ይኖራል በቤቱ — ከተፈጥሮ መብታችን አስወግዶ!

እንደልባችን እንዳኛን — በዱር ገዳማችን እንዳንኖር ፥
ለማዶች እያለ ሰብኮ — አድርጎን ቀርቷል ለቤቱ አሽከር!

ወገኖቻችን እንነብር — እሻፈረን ብለው ጫራ የወጡ፥




በሊምላሜ ውበት ያሸበረቀችው ሀገረ ኢትዮጵያ ፥ እነዚህን ሁሉ አራዊትና እንስሳት ፥ በእንክብካቤ አቅፋ ፥ ለዘመናት ኖራለች ። ድርቀት እየበዛት ሲሄድ ግን ፥ ይህን እንክብካቤዋን ትቀጥል ይሆን?

በየዱሩና በየሜዳው — በተፈጥሮ መካናቸው ያሉቱ !

ውርደታችንን ተመልከተው — ነፃ ሊያወጡን እንዳይመጡ ÷
መጥኝ አድኑን እንዳይሉ — ምድረ ድመቶች የባጥ የቆጡ÷

ለዘለዓለም ሊገዙን — ተስፋ አድርጎ ያለው ÷
የዱርዬግ አውሬዎች ናቸው — እያለ ወሬ እሚያስነዛው፤
የተለያየ ቀለም ሰጥቶ — ቡራቡሬ አደረጋቸው !

ቡራቡሬ ቢባሉ እንኳ — ቀለመ ሥራቸው ባልከፋ ÷
በሚመስሉን አይነት ተባብረን — የማይመስሉንን ልንጋፋ÷
ይረዳን ነበር በውነቱ — አገልጋይ ሆኖ ከመኖር በይፋ !

ያ ነበርም በዘኩሉ — የፍየል አይለፈኝን ትቶ ÷
ምናልባት መላወድ ቢችል — ከሌላው ፍሪዳ ተጠግቶ ÷
ወይም ግር ቅጠሉን ቢጠላው — አልበላህ ቢለው ከቶ ÷

በሥጋ በላነት ባሕርዩ —ከምድቡ ፍጡራን ጋራ ÷
ምናልባት ከቶ ቢተባበር — ከምርት ትግሉ ጎራ ÷



ገጽታዬ አስፈሪ ነው ብሎ — በገለልተኝነት ቢገለል፤
ጉዳት ይሆናል ትርፉ — ሌላው በውሕደት ሲጠቃለል ÷

እንደሳም ሆነ ሌላው — በግርግ ምግቡ ተኮፍሶ ÷
ከሌላው አራዊት ሁሉ — የእበልጣለሁ ጉራውን ተንተርሶ ÷
ተዘርሮ ቢተኛ — ግን አለብኝን ባፉ ጎርሶ ÷
እየወዘረ ከሚዘላ — ሥጋ በሬውን ግርሶ ÷
ይሻለው አልነበር ቢለስልስ — ሸካራ እኔነቱን ደምስሶ !

ለማዳይቱም ዶሮ እንኳ — አውሬ ቆቄዷን ተመልከታ ÷
የሰውን ልጅ ዘመዴ ብላ — ትኖር የነበር ተነፉብታ!
እየዳዳት ነው አሁን — ከዱር ጫካም ልትኖር ገብታ!

የዝሆኑም አይነገረም — የዚያ ባለግዙፍ አካል ÷
ምናምንቴ የሚያገኝ መስሎት—ባለወደው መካን ሲያውደለድል!
ኩንቢው ሳይቀር ማነፍነፉን — ምሥጦች ወረውት ያጣጥራል!

ያ ጅብ አጅሬም ያለወትሮው—ባሕርየ ተፈጥሮው ተለውጦ÷
ያሀያ ያለሀ ሲል እንዳልኖረ— በድቅድቅ ጨለማ ተራውጦ፤

መሰልቀቅ የፈለገው ዛሬ — የሰው ሥጋ ቢያገኝ ቀላውጦ፤
ሆኗል ይበላል ምኞቱ — ቀን ባደባባይ ተቀምጦ !
የራሱን እድገት አካሄዶ — ተሻሽሏል ይሉኝታን ውጦ !

ያቺ አህያም በበኩሏ — ከማን እንሳለሁ ብላ ፤
ሥጋ መመገብ ጀምራለች — ሣርዶ ወናዋን ጥላ !

ቀበሮም ተኩላም ሆኑ — በየተፈጥሮአቸው ዝንባሌ ፤
መኅረር ነበር ተግባራቸው—አስገብሯቸው የጫካው ቀሌ፤
ዛሬ ግን አለወትሮአቸው — ተሠግርተዋል አሉ ከቀበሌ!

የምድረ በዳዎቹ ፍጡራን — ሥጋን ሆነች ቀጭኔ ፤
ባንገታቸው መርዝም ሲኮሩ — ለተሰቀለው ሁሉ አዳኜ፤

ዛሬ ሁለቱም እቀርቅረው — ወሬት ወሬት እያዩ ፤
ጥንተ ልማዳቸውን ትተው — ወንጠራራት ወደ ሰማዩ ፤
ወጣር ወተድፈር ሆኗል አሉ — በግብአተ ወሬት ሊለዩ።

ጆፌ አሞራውና ጨልሌው — ትንጫቢ ሥጋ ቢያጣ ፤



ቅጠል መላስ ጀምሯል አሉ — እንደ ግራስ ሆፐሩ ሬንጃ ፤
ወይም እንደ ተምች አጋዩ — እንደሰብል በላውም አንበጣ !

ደረተ እግር የነበረው — ያ ተንኮለኛ ዕባብ አጅሬ፤
እንደዘመዶቹ ደራጎን ዘንዶ — ከጥንቱ ይልቅ ዛሬ ፤

በተመክሮ ኃልብቶ — ከእግረ አልባነቱ ሊያገግም ፤
ደርዞን እግሮች አብቅሏል አሉ—ያን መርዙን ሊረጭ የትም።

በቀቀን ባይቀር እንጓቅው — የሰማውን እንዳለ የሚተፋ፤
ጆሮ ከበሮው ሥዐት — የማድመጥ ለው ሰለጠፋ ፤
ይቀባጥር ገብቷል አሉ — ዘላባጅነቱ ታውቆ በይፋ !
ቀለም ቋንቋውን ሊለውጥ — እንደወፈፈች ዕበት ሊደነፋ!

ሥራዊት ጉንዳን በሙሉ — ምስጥንና አሸንን ጨምሮ ፤
እንቴና ንይኑ ታመርበት — ራዳር ብሌኑ ተደናብሮ ፤
የሩቁን ማቅረብ አልቻለም — መጠኑ ቅማሬ ጠፍቶት ዘንድሮ !

ሩቅ ባንሄድ ከቤት ውስጥ —ሰው በልተው ይኖሩ የነበሩ!

እነትኳን ቁንጫ ቅማል — ምደረ ተባይ ከዘር ማንዘሩ፥

ለዘለዓለም የበሉት — ሥጋና ደሙ ስለቻሏቸው ፥
የውስጥ እጥንቱን ለመቆርጠም — በነበረው ፅቅናቸው !
ብራኳውን ሲግጡ — ያ ቅልጥሙም አልቀራቸው ።

ውሻና በግ ሳይባል — ወይ ጦጣ አሳማ ፥
የብሳውያን ባሕራውያን — ዓየራውያን ሁሉ በእድማ ፥
ጥንተ ስሪታቸው ተቀይሮ — ተቸንክረው በልዩ ካስማ፥
ተኰርኩረው ተከላልሰው — እንደየቀዬው ጉልማ ፥
እንዱን ሌላው እያወቀው —ውጥንቅጣቸው ወጥቶ ዛሬም

ለግልቢያ ነኝ ይል የነበር — ያ ቀፍጣፋው ወገጋ ፈረስ ፥
አጋሰስ ሆኗል ዛሬ — በያረገቷው የሚልከሰከስ !

ሥጋርነቷ ተመሥክሮ — ያስደነቀችው ያቺም በቅሎ ፥
ከሁለት ዘሮች ተገኝታ—የአንድ ወገኗ ፅድል ተሥናክሎ

እንደአባቷ እንዳህያ — ወይም እንደናቷ እንደፈረስ ፥
የመውለድ ፅድሏ ተሥናክሎ — እምባጓደር ያጣች ለራሷ ነፍስ፥



ለበቀል ይሁን ወይም ለሌላ — ባልታወቀ ምክንያት ፥
እንደ ለገመች አለች — በቅሎይቱ በበቅሎነት ።

ዝርዝር ሐታታ ላለመግባት — ለኮፍ አድርጎ በቅንጭቡ ፥
በጠቃላይ ወተው ይቻላል — ብዙ ጥቅንጥቅ ውስጥ ሳይገቡ።

እንዲያው ለመዝጊያ ያህል — ጉዳዩን ለመቋጠር ባጭሩ፥
የሚከተለቱን ጠቃቅሶ — ቢቆረጥ ይበጅ ነገሩ !

በኑሮዋና በሕይወቱ — በፍላጎቱም እንግር ፥
የፍጡራን ምኞቶች — ከሦስት አያልፉም በድምር ።

የሚመገበው ምግብ — የሚለብሰውም አልባስ ፥
ከሚኖርበት መቀላ ጋር — ለያንዳንዱ ቢዳረስ ፥

ቀሪው ሌላ በጠቃላይ — የላወላ ላይ አላል ነው ፥
ለቅንጦትና ለቅብጠት ብቻ — ይሆናልም ምላሴው ።

እንዚህን በሙሉ — ለዚህም ዓለም ሕላዌ ፥
እያንዳንዱ ማግኘት ከቻለ —ነፃ ማለት ነው ከደዌ።

# አውሬ ቡራቡሬ!

ታዲያንን ቡራቡሬው — አውሬ ሆነ እንስሳቱ ፤
የሚስማማበትን መመሪያ አድርጎ — የሚለያይበትን በየቤቱ ፤
የማዕከል ሐቅ አንግቦ — ጠቃሚውን ብቻ ለወል ሕይወቱ ፤
ምናለበትኮ ቢተባበር — እርስበርስ ከሚባላ በከንቱ !

ዓለም እንደሆነ መኖሩ አይቀር—ፍጡር ተስማማ አልተስማማ፣
መኖቴው ብቻ ያልፈጠለ — ፅድሜውን ቆጥሮ በሞት አውድማ!

ከቡራቡሬው ቀለሙ ላይ — የሚመሳሰልበትን ይዞ ፤
የሚለዩትን ዝብርቅርቆች — ኅብረ ቀለማቱን ሙርዞ ፤


ምናለበትኮ መኖር ቢችል — የየሁሉ ፍላጎት ተጠብቆ፣
በነፃነት በእኩልነት — በፍትሕ ርትዕ ተጠምቆ !

ቡራቡሬው ኅብረ ቀለም — በመረጠው ጥሕድ ብቻ ቢተካ ፤
በጋራ ድምፅ ወስኖ — እያንዳንዱን በሚያረካ ፤
አውሬነቱም ይቀር ነበር — በቡራቡሬነቱም እያወከ !

እንዳለው አይነት ሆኖ ቢኖር — አውሬ ቡራቡሬ ፤
ዘበት ነው ያገኛል ማለት — የምቾቱን ጣፋጭ ፍሬ !!

* * *

# ለኔ ለኢምንቱ!



ፍንዳታ — ቁ 100

# መዘክርነቷ

የትልቅነት ትምክሕት ፥ በታናናሾች ዘንድ

ዕሴት እንደሌለውና ዋጋም እንደማይሰጠው ፥ ካንጀታቸው

ለሚያምኑ ሁሉ ።



# ለኔ ለኢምንቱ !

ዓለም ጋለ ይሉኛል — ዓለም ቢግል ባይግል ፥
ለኔ ኢምንቱ ሰው — ምን ትርጉም ይሰጣል !

ለኔ ለትንሹ — ለጥቂቱ ፍጡር ፥
የትልቁ ዓለም — የግዙፉ ምድር ፥
ቢግልና ቢግም — ምን ሊሠራ ታምር !

ግሙ ግሙ ግሞ — አብጦ ቢሉ ቢው ፥
ያለው መፈንዳት — ምን ፋይዳ ሊኖረው ፥

በትልቅ ሥፍራ ላለው — ለኔ ኢምንቱ ሰው ፤
ከቶ ቢገለፀም — ምኑስ ቁብ ሊለው ነው !

ምን ግንኙነት አለው — ከኔ ከትንሹ ፤
ግዙፉ ሰፊ ዓለም — ጋላክሲ ምሬቱ ፤
በግዝፈቱ አንፃር — ለቅንጣት ትንሹ ፤
ፈንድቶ ቢፀፋ — ቢጠፋ ድራሹ ፤
ምን ስሜት ሊሰጠኝ — ዓለም አደራሹ !

ለኢምንቱ እኔ — ለተኪያው ፍጡር ፤
ዓለም ሞቶ ቢገል — ቢያብጥና ቢወጠር ፤
ከለስላሳነቱም — ጠጥሮ ቢኳከር ፤
ተቃጥሎ ቢጫጫስ — በፍም ቢኮማተር ፤
ምን ዝምድና አለው — ከኩንትሽ እኔ ጋር !
ምን ስሜት ሊሰጠኝ — በግዝፈት ቢያግጥር !!

ትልቁ ሲጠፋ — ትንሹም ይጠፋል ፤
ይኸ ሕገ ሥርዓት — ግዴታ ይኖራል ፤
ታፍኖ እሰካለ — ትንሽ በሰፊ አካል ።





እንዲት ቁራሽ ዳቦ — መግቦት ለሚኖር ፤
በኩባያ ውሃ — ነፍሱን ለሚያሳድር ፤
ቡትቶ ጨርቃ ጨርቅ — ለብሶ እሚገደረደር ፤
ለዚያ መሰሉ እኔ — ምስኪኑ ባይተዋር ፤
ግዙፉ ይህ ዓለም — ምን አለው ቁም ነገር !

ይጫነታቸው እንጂ — ከመቶ እጅ አንዱ ፤
ዓለሙን በእጃቸው — እንቀው የጨበዱ ፤
እናያ ሊታዎች — በወርቅ የነገዱ ፤
ሚሊዮነሮቹ — ዶላር ያሳበዱ ፤
እኔ ግን ኩታራው — ምን ሊሰጠኝ ጉዱ ፤
የነሱ ዓለም ቢጠፍ — እሊያው ይናደዱ !

ዓለም ቢፈጠፈጥ — ግዙፍ ኮከብ ገጭቶት ፤
እኔን ምን ሊሰጠኝ — ዓመን ያልቀመስኩት !

መረመንዱን ዝሆን — ትንኝት ብትረግጠው ፤
በርግጥ ያ ደንደሱ — ከብደቷ ሊሰማው !

ኢምንቲቷ ትንፋን – እፆ ብትቀነጥጥ ፥
በርግጥ አበሳጭታው – ጦር ጦቢ ሊረግጥ !

    አጋበስ አንበሳን – ትንሽ ምስጥ ብትነክሰው ፥
    ድረሱልኝ ብሎ – በርግጥ ሊያለቅስ ነው!

የማይመስለን ነገር – ያወሩታል ለምን ፥
ጎሊናን መንጥቆ – ልብ አካል ሳይለስን !

    ተመዘግዛጊን ጆሬ – ንቢቱ ብትነድፈው ፥
    በርግጥ ከመከነፉ – ተበሳጭቶ ሊተው !

ደራሳንን ያሀል – ያን ትልቁን ዘንዶ ፥
ትንሽ ትል ብትጧጥጥ – ሊሸኝት ተናዶ!

    የባሕሩንን ንጉሥ –ያንን ዓሣ አንበሪ ፥
    ዓሊቷ ብትረግጠው – ተሰምቶት ሊል እሪ!

የማይመስል ነገር – ኧረ ተዉ አታውሩ ፥
ጥጋብ የለውም – በስተቀር ከነውሩ !



ምንም አይፈይድም – የወሬኛም ክብሩ !

    እንዲያማ ከሆነ – በትልቅ ውስጥ ትንሽ ፥
    አብሮ የሚደቆስ – ያ ትልቁ ሲሸሽ !
    ትርጉሙ ምን ይሆን – አፋሽ ወይስ አፍራሽ !

“ከኑግ የተገኘህ – ጅላጅል ሞኝ ሠሊጥ ፥”
ያገሬ ሰው እንዲል – ባንድነት ተወቀጥ ፥
ትፈርዱብኝ ይሆን – እኔም እንድረገጥ ፥
ትልቁ ዓለም ወርዶ – ባካል ሲፈጠፈጥ ፥
ምድረ ፋይድ ሲገባ – ዩኒቨርስ ሲናወጥ !

    እኔ ኢምንቱ ሰው – በምን አበሳዬ ፥
    አብሬ ልደቆስ – በሌለ ዕዳዬ !

የጅንጀሮ ታሀል – ሀገር እንኳ የለኝ ፥
የነበረችኝን – ጆሬ ያንኪ ነጥቆኝ !

    እንደናሕ እጥሩ – የሌለኝ ግረፊያ ፥

ከጥንፍ እስካድማስ — የማስስ መጠጊያ !

የያገሩ ጃሬ — ስዞር የሰለቸኝ ፥
መዉታ እያለ — ካፌሩ እሚነፍገኝ !

ታዲያ ትልቁ ዓለም — ለኔ ለኢምንቱ ፥
ምን ትርጉም ይሰጣል — ቢኖር ባይኖር ከንቱ !

ወይስ በግልብጡ — ይሆን ወይ ትርጉሙ ፥
ያለው ዘይቤ — መሠረተ ትልሙ ።

እንዲያማ ከሆነ — አይጥም ድመትን ፥
አጅሬት ፍየልም — ጠላቷን ነብርን ፥

ቻሉ ማለት ይሆን — በጉልበት መበቀል ፥
በትንሽ ግልብጦሽ — ትልቅ ማስተካከል !

እንዲህ ያለው ብሒል — ነው ወይ ፍልስፍና ፥
ደንታቢስ የሚያደርግ— ንፁስ ልዕልና !

ብዙ ስቀባጥር — ሐቁ እንዳይሆን ከንቱ ፥




ባጭሩ የምለው — ሲደጠር ዕውነቱ ፥
ግዙፉ ይህ ዓለም — በታላቅነቱ ፥
ደርሶ ቢከውከም — በገዛ ጥፋቱ ፥
ምንም ትርጉም አይሰጥ — ለኔ ለኢምንቱ !!!


# እንዲህ እንደ ኪሩብ!



እንዲህ እንደኪሩብ !

እንዲህ እንደኪሩብ — ክንፍ አካል ቢኖረኝ ፤
ወቸ እጠበሰ ነበር — በዚህ ዓለም በታኝ !
ስላጣሁ ብቻ ነው — መሸኘ መድረኘ ፤
በዚህ በጂት ዓለም — የኖርኩ እንደወኘ !





# ጦማራት!

የሀገራችን ነባር ባሕል አግሯቸውም ይሁን ሳያውቃቸው የሚኖሩ ብዙ በጎና እጅግ ጠቃሚ ልምዶች ፣ በዓለም ላይ አሉ ። ከነዚህም አንዱ የሰላምታና የልዩ ልዩ ምኞት መግለጫና ሐሳቦች ማስተላለፊያ የሆነው ጦማር ( Card ) ነው ። በምዕራቡ ዓለም ፣ በልዩ ልዩ የሐሳብና የምኞት መግለጫ ካርዶች መጠቀም እጅግ የደራና በጣም የተወደደና የተለመደ ነው ። በካርድ አገልግሎት መጠቀም ብዙ ችግሮች

ን ያቃልላል ። ጊዜ ይቀጥባል ፤ ምን ልጅና የሚለውን ጭንቀት ያስወግዳል ፤ ቀሎ ደራሽ ነው ፤ በምስታ ሲላክ ዋጋው ርካሽ ነው ፤ ኢንቮልፕ አልብሱኝ አይልም ፤ የተቀባዩን ቀልብ የመሳብና የመግረክ ኃይል አለው .... ወዘተ

በዚህ በአለንበት ፈጣን ዘመንና በየጊዜው በማኅበረ ሰባችን ውስጥ እየተፈጠሩ የሚከሠቱት ልዩ ልዩ ድርጊቶች ከምንጊዜውም እንደዕንጉዳይ እየፈሉና ዕድገታቸውም እየፋፋ በመምጣቱ ፤ የሕዝባችንን በቅርብ መገናኘትና በሐሳብም እየተለዋወጠ ከልብ መተሳሰብና ከአንጃትም መረዳዳትና መደጋገፍ ፤ ከሚያስፈልገው ደረጃ ላይ ደርሷል ። እንደማንኛውም ማኅበረ ሰብ ፤ በኛም ሕዝብ ሕይወት ውስጥ በየዕለቱና በየአመቱ ፤ እንደ ልጅ መወለድ ፤ እንደ በዮት ማለፍ ፤ እንደዕለተ ጋብቻ ማዘጋጀት ፤ እንደ የተለያዩ በዓላት ማክበር ፤ እንደየትምህርት በዓለ ምረቃ ማድረግና የመሳሰሉትም ድርጊቶች ይከናወናሉ ። እነዚህን ለመሳሰሉ ክዋኔዎች ሁሉ ፤ እንደየአይነታቸው ፤ የደስታና የሀዘን ፤ የበጎ ምኞትና የመልካም ተምኔት ሐሳባቸ መግለጫም



ች ፤ ለመላጅ ዘወድ ጦማራት ( cads ) መለዋወጥ እየተለመደ ምጥቷል ። ያ አይነቱ በጎ ልምድ ፤ ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ይለመድ እንጂ ፤ የመገልገያው ካርድ እስካሁን በሥርዓት አልተዘጋጀም ። በተለይም በየቋንቋችን ! ይህን ባዶ አገልግሎታዊ ቦታ ለመሙላት ሲባል ፤ ይበልጥ የተሻለና የተሟላ ዝግጅት ለወደፊቱ እስኪቀርብ ድርስ ፤ ለጊዜው ለውክራ ያህል የሚያገለግሉ አቅርቤአለሁ ። "ይድረሰች" ብዬ ነው የሠየምኳቸው — እነዚህን ካርዳዊ መልዕክቶች ። በተዋቡ ተልዕኮአዊ ሥዕሎች አስጊጦ ፤ ካርዶቹን ለሚያትምና ለሚያሠራጭ ማንኛውም ግለ ሰብም ሆነ ድርጅት ፤ የሃምሳ እጅ የድካም ዋጋ እስከከፈለ ድረስ ፤ ለተግባሩ መጋበዜንም ፤ በዚሁ መልዕክቱ አስታውቃለሁ ።

ይድረሰች!



ፖ ስ ታ ዎ ች - Cards

ጥምር - አንድ

የአዲስ ዘመን በዓል ፣ የደስታ ምኞት መግለጫ ።

ይድረስ ! ________

ለሚከብርም

[illegible]

[illegible]

የዘመኑ ... ይሁንልም !

አክባሪም

---

ጥምር - ሁለት

የገና በዓል የደስታ መግለጫ ።

ይድረስ ! ________

ምንጊዜም ለማትረሳም

[illegible]

እንደገና መልካም ልደት !

አክባሪም



ጦማር - ሦስት

የፋሲካ በዓለ የደስታ መግለጫ ።

ይድረስ ! ________

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሰዎ !

በዓለ ትንሣኤ ፥ የመዋትያን የሰው ልጆች ፥ የበስተ ኋላ ሕያውነት ምልክት ነው ። በመሞት ፋግግጭ ሕይወት እ ንደሚገኝ ፥ በዓለ ትንሣኤ ያስተምራል ። ምሥጢረ ትንሣኤ ለመደቀ መንፈስ ፥ የእንደገና መንቃት ቀስቃሽ ደወል ነው ። በተለይም ፥ ቀቢጸ ተስፋ ለሚያንገላታው የዘመናችን ሰው በትምህርተ ትንሣኤ ሊጸናና ይገባዋል ። እንደትንሣኤ ላለው ታላቅ ዕለተ በዓል መድረስ ፥ የገዛ ራስን መንፈስ ለማንቃት ለተሐድሶ ነፍስ መብቃት ስለሆነ ፥ እጅግ መታደ ል ነው ። ስለዚህም ፥ የትንሣኤ ሕይወት ነፀብራቅ ለሆ ነው ፥ ለታላቁ የትንሣኤ በዓል እንኳን አደረሰዎ እያልኩ ከልብ የመነጨ ምኞቴን እገልጽልዎታለሁ ።

ምንጊዜም አክባሪዎ !

ጦማር - አራት



አዲስ የቤተ ሰብ አባል ላገኙ ወላጆች የደስታ መግለጫ

ይድረስ ! ________

እንኳን ደስ አለዎ !

በደመ ነፍስ ለሚንቀሳቀሱ ፍጡራን ፥ ራሳቸውን መሰል ተዉማፊ ፍጡር ከማስገኘት የበለጠ ሌላ ተድላ ደስታ አይኖ ራቸውም ። የምድራዊ ሕይወት ፥ ታላቁ ጸጋና በረከት ልጅ ነው ። ልጅ ማግኘት ፥ የራስን ተንቀሳቃሽ ሐውልት የማነፅ ያህል ነው ። ወላጅ ሁሉ ፥ የሚያፈራው ልጅ የሕይወቱ ተተኪና ግላዊ እምባማደሩ እንደሆነ ያውቀዋል ። ለአንድ ቤተ ሰብ ፥ ሌላ አዲስ አባል ማፍራት ፥ የማኅበ ረ ሰብን መሠረት ማፅናትና ብሎም የወገንን ሕዝባዊ ቁጥር ማካበት ነው ። በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ ፥ ልጅ ለመውለድ መታደል ፥ ለቤተ ሰቡ ሐረጋዊ ቅርጽን መስጠት ብቻ ሳይሆን ፥ ለተከታይ ትውልድ ሕልውናም ፥ ደጊ ዋስትና መገንባትም ነው ። የወለደ ይከብዳል ። የትውልድን ሚዛን ያነሳልና ። ቤተ ሰብዎ ልጅ በማግኘቱ ፥ ለግልዎ የሚሰማዎ ደስታ ቢያመዝንም ፥ ልጅነቱ የማኅበረ ሰቡ

ጥምር በመሆኑ ፥ ደስታው የጋራችንም ነውና ፥ "እንኳን ደስ አለዎ!" ማለት ብቻ ሳይሆን ፥ "እንኳን ደስ አለን!" እያልኩ ፥ ከፍተኛ ደስታዬን እገልጻለሁ ።

የደስታዎ ተካፋይ የሆንኩ ፥

አክባሪዎ

## ጦማር — አምስት

የሀዘን ማፅናኛ

ይድረስ ! ______

ለማከብርዎ

ሀዘንና ደስታ በፈራረቃ በሚቀያየሩበት ዓለም ውስጥ ሁልጊዜ በተድላ ደስታ መኖር ከቶ አይታሰብም ። ተራውን ጠብቆ ድንገት ሳያስቡት ዱብ የሚል ሀዘንም ይኖራል ። ፍጻሜ ሕይወቱ ሞት ለሆነ ሰው ፥ ይህ አይነቱ ዕጣ የሚያስደንቅ አይሆንም ። በደረሰብዎ መሪር ሀዘን ፥ እጅግ ከተሰማችው ወገኖችዎ አንዱ ነኝ ። ሰዎችና ዓለም በአንድ እስካሉ ድረስ ፥ የተራ ቅደም ተከተል ሥርዓት ሆኖ እንጅ ሁላችንንም በየቀናችን የማለፍ ግዴታ አለብን። መፐቲው የሰ



ው ልጅ ፥ ሞትን ሲያስተናግድ ቢኖርም ፥ ሞት ግን ሁልጊዜ አዲስና እንግዳ እየሆነ ሲያሠቅቀን ይኖራል ። የደረሰብዎ ሀዘን መሪር እንደሆነ ይሰማኛል ። ሆኖም ፥ ሞት እያንዳንዳችን የምንከፍለው የተፈጥሮ ዕዳችን ነውና በደረሰብን ጊዜ ሁሉ ፥ በትዕግሥት ልንቀበለው ይገባናል ። የያንዳንዱን የሰው ልጅ የመሞት ግዴታ የምናውቀው ፥ በተወለደበት አንፃራዊ ባሕርይ ነው ። ይህን የተፈጥሮ ሕጋዊ ግዴታ ሰብሮ ያመለጠ ፍጡር የለም ። በበጎ ምግባራቸው ዕሴት ፥ እንጎናክ ፥ እነፅዝራ ፥ እነኤልያስ ፥ ሞትን ተሠውረውታል ቢባልም ፥ በጊዜያዊነት እንጅ ቋሚ አይደለም። ሠይፈ ሞት ኖሮ ፥ የበቃውን ዘርና አፅም ባይሠይፍ ፥ ፍጥረተ ዓለሙ ምን ይልስ ምንስ ይቀምስ ነበር ! ሞት ግዴታ መሆኑ ፥ በዚህም ቁም ነገር ጥምር ነውና ፥ ከደረሰብዎ ሀዘን ጽናቱን ይስጥዎ እያልኩ ፥ የሀዘንዎ ተካፋይነቴን እየገለጽኩ ፥ ሰላም እንዲሠፍንልዎ እመኛለሁ ።

አክባሪዎ

## መግር − ስድስት

ሥርዓተ ጋብቻ ፈጽመው ፥ ትዳር ለሚመሠርቱ ጥንዶች ፥

የብሩህ ሕይወት ምኞት መግለጫ !

ይድረስ ________________

ለግክብርዎ

በዚህ ዓለም ሕይወት ውስጥ ሳሉ ፥ ተረዳድቶ መኖር ግዴታ መሆኑ ፥ በሥነ ፍጥረት ልዩ ልዩ ዘርፋዊ ሕጋጋት ላይ ፥ በየመልኩ ታይቷል ። መረዳዳት ሲባልም ፥ ቢያንስ ቢያንስ ፥ ጥንድ መሆንን ይጠይቃል ። የሚጀመረውም ለማኅበረ ሰብ እምድና ምሰሶ ከሆነው ፥ ከቅዱሱ የቤተ ሰብ ምሥረታ ላይ ነው ። ምናልባትም ፥ መረዳዳት ባያስፈልግ ኖሮ ፥ የፆታዎች በሁለት የሚሳሳቡ ስሜታዊ ባሕርያት ባል ተከሠቱ ነበር ። ይህን ሉዓላዊ የተፈጥሮ ሕግ በማክበር ሥርዓተ ጋብቻዎን በዚች ዕለት በመፈጸምዎ ፥ ደስታ ከፈነቀላቸው ብዙ ሰዎች ውስጥ አንዱ ነኝ ። ጋብቻችሁ ፥ እንደቀደምቶቹ አዳምና ሔዋንና እንደኋለኞቹም እንደ አብርሃምና ሣራ ፥ የተባረከ እንዲሆን ፥ ተስፋዬም እምነቴም



ነው ። ጋብቻ ፥ እርስ በርስ በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ፥ የሚከፍለው ክቡር ዕሴት አለው ። የከፍተኛ ፍሬያማ ምርት አበርካች በመሆኑም ፥ የሚመሠርቱት ቤተ ሰብ በሕፃናት ምርት የሚፋፋና የሚበለጽግ እንዲሆን በመመኘት ፥ በዚህ በሠርግዎ ዕለት፥ “እንኳን ደስ አለዎ! እያልኩ ፥ ለመልካም ጋብቻ በዓልዎ ፥ የደስታዎ ተካፋይነቴን ከልብ እገልጽልዎታለሁ ።

አክባሪዎ !

## መግር − ሰባት

የትምህርት ምረቃ በዓል ፥ የደስታ መግለጫ ።

ይድረስ ! ____________

ለግክብርዎ !

በሰዎች የሕይወት ኑሮአዊ ሂደት ውስጥ ፥ ትምህርት በየዘርፉ የወሳኝነት ባሕርይ አለው ። ግላዊ ዕውቀትንና አስተሳሰብን ማዳበር ብቻ ሳይሆን ፥ የጥሪትን ዋጋ በመክፈል ፥ በሚሳድግ ያመነጫል ። ምግበ ነፍስ የሆነውን

ትምህርት ተጠንቅቀው ከተወገቡት ፥ በምግብ ሥጋነትም የሚያገለግል ፀጋና ረድኤትም ያወርታል ። በዓለም ላይ ከሚኖሩት ሕዝቦች ውስጥ ፥ ጥቂቶቹ የሥልጣኔን ሸግ የመልበስ ዕድል ያጋጣማቸው ፥ የሕይወት ግግና ድራቸውን ትምህርትን በማድረግ የሸወኑ ናቸው ። ግፋዊ ብልጽግናን ከማምረት አልፈው ፥ ለሚኖሩበት ሀገርና ሕዝብ ፥ ከድንቁርና ደዌ የሚያነሱ ፥ ፍቱን አብነቶችም ሆነዋል ። ትምህርት የማይሻምጠው ድንቁርና ፥ የማይቀጣው ውስና ፥ የማያለስልሰው ሸካራ ጎሊና የለም ። ስለዚህም ምግብ ትምህርትን ለመሳተፍ የበቁ ግለሰቦች ሁሉ ፥ ዕድለኞች ናቸው ። በበኩልዎ ፥ በተሠለፉበት የትምህርት ወሰክ ፥ ፍላጎትዎን በሟሟላት ፥ ከሚወኙት ምዕራፍ ላይ አድርሰው በመመረቅዎ ግላዊ የመንፈስ ኩራትና እርካታ ሊሰማዎ ይገባዎታል ። እጅግ ደከምው ያወረቱትን ንባብ ታላቂ ዕውቀት ፥ በጠቃሚ ተግባር ለመተርጎም የሚያስችልዎ ተስማሚ ሥራ እንዲያገኙ በመወኘት፥ በአሁኑ ወቅት ምድብ ትምህርትዎን አጠናቅቀው ለዕለተ ምርቃት በመድረስዎ ፥“እንኳን ደስ አለዎ!”እያልኩ



ግልፃዊ የደስታ ስሜቴን በአክብሮት ስገልጽልዎ ፥ እኔም ጭምር ደስ እያለኝ ነው ።

እክባሪዎ!

ጦማር – ስምንት

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ( March 8 – ዕለተ እማማዎች ) በየዓመቱ ሲከበር ፥ ለነእማማዎች የሚላክ ።

ይድረስ ።

ምን ጊዜም ለምትታሰቢኝ ፥

በምናርበት ዓለም ለመገኘት ፥ ተቀዳሚ ምክንያት ለሆንሽው

ለተወዳጇ እናቴ እማምዬ ________

የሕፃን አንደበቴ በወቅቱ መናገር የማይችል ሆኖብኝ እንጅ ገና ያኔ በወለድሽኝ ዕለት ፥ ላደረግሽልኝ ውለታ ፥ ለምድር ለሰማይ የከበደ ከፍተኛ ምሥጋና ፥ ባቀረብኩልሽ ነበር ። ዛሬ ግፅዘ አዕምሮዬ ዳብሮ ፥ እኔን ስትወልጅ የነበረብሽን ጭንቀት ፥ የዘጠኝ ወራቱን የዕርግዝናሽን ድካምና ፥ ኋላም ነገረ ዓለሙን ለመረዳት እስከምችልበት ድረስ ፥ ላደረግሽልኝ ከፍተኛ ያገልግሎት ውለታሽ ፥ ምን

ጊዜም ባለመለታሽ መሆኔ ይሰማኛል ። የኔ በዚህ ዓለም ላይ መኖር ፥ ያለእንቺ ተቀባዊ ርባታ ፥ ጭራሽ የማይታሰብ ነው ። በዓለም ላይ ለሚገኝ የማንኛውም ቤተሰብ ፥ እናቶች የኑሮ ሕይወታዊ ቅመሞች መሆናቸው እንደታመነበት ሁሉ ፥ እንቺም የኔ እናት ፥ ቹንጉርጉሩን ዓለም በተለያየ መልኩ አጣርቼ የማይበት ፥ ልዩ መነጽሬ ነሽ ። ከማኅጸንሽ የተከፈልኩ ውንድ የሥጋሽ ቁራጭ ፥ ያጥንትሽም ፍላጭና ኩፋሌ ነፍስሽም በመሆኔ ፥ እንቺን ለመርሳት የምችልበት ፥ ኀይልም ሆነ አንጀት ጨርሶ የለኝም ። ሁለንተናዬም በመሆንሽ ፥ ሁለንተናሽ ነኝ ። የመኖሬ ዋስትና ነሽና አለኝታነትሽን ምንጊዜም እፈልገዋለሁ ። የየዕለቱ ምናቤም ስለሆንሽ ፥ ካጠገቤ ስትለይኝ ይጨንቀኛል ። ግርማ ሞገሴም በመሆንሽ ፥ ስትርቂኝ ቀልቤም ሆነ ፀጋዬ ይገፈፋል ። የሕልውናዬ ተድላ ደስታ ፥ ምንጩ እንቺ በመሆንሽ ፥ ሕልውናሽ ሕይወቴ ነው ። የትም ልሂድ የትም ልኑር ፥ ትዝታሽ ምንገዜም ሕያው ነው ። ሕልሜ ሆነ ራዕዬ ምንጊዜም እንቺው ነሽ ። የምኞቴን ያህል እንዳች ቁምነገር እንዳል





ፈየድኩልሽ በታወሰኝ ቁጥር ፥ ቁጭቴ ሥጋዬን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ነፍሴን ሳይቀር ይቆጠቁጣታል ። እምላኬን የምማጸነው አንድ ነገር ቢኖር ፥ ያንቺን ክፉ እንዳያሳየኝ ነው። በዛሬው ዕለት ፥ ይህን ከውስጥ አንጀቴ የመነጨ የደስታ መግለጫዬን የማስተላልፍልሽ ፥ የእናቶች ውለታ ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወስበት ዕለተ-እማማዎች በመሆኑ እንጂ፣ እንቺማ ምንገዜም የልቤ ፅላት ስለሆንሽ ፥ ከኅሊናዬ ርቀሽ አታውቂም ። ነባሩ የተፈጥሮ ሕግ ተሸሮ ፥ ለዘለዓለም የሚያስኖር የሕያውነት ፅድል ለተወሰኑ ሰዎች ይሰጥ ቢባል፣ የመጀመሪያ ምርጫዬ እንቺ እንደሆንሽ ፥ ልደብቅሽ አልፈልግም ። ይህ ምኞቴ የተፈጥሮን ድንጋጌያዊ ምሽግ ሠብሮ ፥ ላንቺ ያለኝን ተምኔት ማሳካት እንደማይችል ባውቅም እንኳ፣ ለሕልውናዬ መተርጉምና ለሕይወታዊ ደስታዬም ዋነኛ ምንጭ ለሆንሽው እናቴ ፥ በሕያው ስምሽ እንዲታወስ በተወደደው በዚህ ቅዱስ ዕለት ፥ ሌላው ቢቀር የምኞት መግለጫዬን በየዓመቱ እንዳስተላልፍልሽ ፥ ለዘመናት በሰላምና በጤና ትኖሪልኝ ዘንድ ፥ ፈጣሪዬን እየተማጸንኩ ፥ ለሚቀጥለውም

ኑወት ወሰል በኅል እንዲያደርስሽ ምኞቴን በመግለጽ ፥ ዛሬ በዚሁ እሰናበትሻለሁ ።

የምንጊዜም አክባሪ ልጅሽ

ጦማር — ዘጠኝ

የዕለተ ፍፃሜዋም በኅል ላዘጋጁ የወደፊት ሙሽሮች ።

ይድረስ ______________

ለማክብርዎ

ኑሮ ያለተመጣጣኝ ረዳት አካል እንደማይገፋ ተረድተው ፥ የሕይወት አጣማጅዎን አባል መርጠው ፥ በጋራ ወሬታቀድ ፥ የቃል ኪዳን ውል ለመተሳሰር በወሰኑበት በዛሬዋ ዕለት ፥ የዚህ ከፍተኛ የሕይወት ዕቅድ ዝግጅትዎ ፥ ደጋፊና አበረታታች መሆኔን ልገልጽልዎ እወዳለሁ ። ቃል ኪዳን የትንቢት ጊዜን ምሽጋዊ ክልል በርግዶ የሚያልፍና የሩቁን ሕይወት የሚያሳይ ፥ በመተማመን ላይ የተመሠረተ ሕልውናዊ መስተዋት ነው ። ዛሬ የማያምኑትን ፥ ለነገ አይወኙትም ። በዛሬው ሁለንተና ሁኔታዎያን ላይ ተማምና ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል ፥ ቃል ኪዳናዊ ውል መግባት ፥



ትንቢታዊውን ሁኔታ ሁሉ ድል እንደመምታት ይቆጠራል ። ልዩ ልዩ ፈተናዎች በሚያንገላታው ዓለም ውስጥ ፥ ለሕይወት ፅድቄ ውሉ የሚዘልቅ ቃል ኪዳናዊ ውል ማድረግ ፥ ቀላል ውሳኔ አይደለም ። እርስዎ ግን ይህን ከባድ ውሳኔ አድርገው ፥ በዛሬዋ ቀን ሕጋዊ ወለክ በመስጠትና ይፋ እንዲወጣ ለወዳጅ ዘመድ በማስታወቅዎ ፥ የኑሮን ትግል ለመቋቋም የወሰረጥዎ ማረጋገጫ ማኅተም ነውና ፥ በዚህ ውሳኔዎ የመንፈስ ኩራት ተሰምቶኛል ። ይህ ውሳኔዎ በገቢር ከሚታይበት ከዚያች ቅድስት የጋብቻ በኅልዎ ፥ ጥንዶችን ፈጥሮ ጋብቻን የደነገገው አምላክ ፥ ሁላችንንም በሰላምና በጤና ጠብቆ እንዲያደርስዎ በመመኘት ፥ እሁንም ቶራዋ ውሳኔዎን እንደገና በማድነቅ ፥ የቃል ኪዳን ማሠሪያ የሆነው የቀለበት መለዋወጫው ቀን ፥ የደስታና የፈንጠዝያ እንዲሆንልዎ ከልብ እመኛለሁ ።

አክባሪዎ

ጦማር — አስር

ለተጫጩ ፍቅረኞች ፥ የመገናኛ መልዕክት ።

ይድረስህ (ሽ)__________

ለማከብርህ (ሽ)ና ለማፈቅርህ (ሽ)

ያ የለመድከው(ሽው) ሰላምታዬ ይቀድማል ። በፈጠረህ(ሽ) ፥ ለመሆኑ በነፍስህ(ሽ) አያለህ(ሽ) ነው እንዲህ እስጨከንህ (ሽ) የጠፋኸው?(ሽው)? እንዴው መኖሬውን የማን ጠንቋይ ሰጠህ (ሽ) ይሆን? የፍቅር አምላክ እንኳ እንዲህ ጨክኖ አያደርገውም ። ድምፅህ(ሽ) ከጠፋብኝ ጀምሮ ፥ እህል ውሃ መቅመስ እንኳ ተስኖኛል ። ዓይንህ (ሽ) እያየ ልሞትልህ (ሽ) ነው ። ኧረ በዚያች በምትወዳት(ጃት) እናትህ (ሽ) ፥ ያንን ልቧን የሚያነዝ ረውን ደብዳቤህን(ሽን) እንኳ አትንፈገኝ (ጊኝ) ። ትዝ ባልከኝ (ሽኝ) ቁጥር ፥ የምሆነው ጠፋ ቅጡ ይጠፋኛል ። እንዲያመጣህ(ሽ) የማልማፀነው የፍቅር መናፍስት የለም ። የሚያባየኝ ሕልም ሁሉ ፥ እንደትራጀዲ ቲአትር የሚያስጨን ቅ ነው ። ክፉ ነገር ያጋጠመህ (ሽ) ይመስለኛል ። ሌላ አታልዋም የመሰችህ(ሽ) እየመሰለኝ እበሻቃለሁ ። ኧረ እባክህ የኖፈት ነፍሴን ኋስ አድርገህ(ሽ) አትግመትዓት



(ችበት) በሕይወት መኖሬ ፋንተ(ፋንቺ) እስከሆነ ድረስ በእንዓሩም አንተም (አንቺም) ለኔ ብቻ መሆንህን(ሽን) ማረጋገጥ ይኖርብሃል(ሻል)። ለዚህም አይነተኛው ምልክትና ማስረጃ ፥ በየጊዜው መገናኘታችንና ደብዳቤም መለዋወጣችን ስለሆነ ፥ ቶሎ ባስቸኳይ ባትጽፍልኝ(ፊልኝ) የቀጠነውን ውኃ እንደገና የማቀጥን መሆኔን እንድታውቅልኝ(ቂልኝ) ። ንፍቀትህና(ሽና) ትዝታህ (ሽ) የሚያንሰፈስፈኝ ፥ የምን ጊዜም ፍቅረኛህ(ሽ) ነኝ ።

ከከንፈሮቼ ማኅተም ጋር እስናፀትሀለሁ(ሻለሁ) ።

የዘለዓለም ፍቅረኛህ(ሽ)

* ዛሬ እነዚህን አጭር ጦማራት ብቻ ብልጭ አደረግሁ እን ጂ ሁለገብ የሆኑ አያሌ "ይድረሶች" አሉኝ። በተለይም እንደ የኢትዮጵያውያን የደብዳቤ መለዋወጫ ቀን ያለ ልዩና ለነባ ሩ ባሕላችንም ፅንግፋና አዲስ ልምድ የሆነ ዝግጅት ጭምር የሚያገለግል አለኝና ፥ ወደፊት ሁሉንም እሰባስቤ እወጣቸ ዋለሁና እስከዚያው ቸር ይግጠመን ። ጦማሮቼ በሚታተሙበት ውቅት ፥ እጃቢ ሥዕሎቹ በሙሉ፥ መልዕክቱን የሚያስተጋቡና

የሚያንፀባርቁ ፥ የኢትዮጵያ ቅርሶች ቢሆኑ ይመረጣሉ ።

## ማሳያ

### የገና


ሃማኖታዊ ባሕልነቱ ፥ የረቂቅ መለኮት ከግዙፍ ትስብዕት ( ሥጋ ለበሱ ሰው ) ጋር መዋሐዱን ሲመሠክር ፥እንደ ዓለማዊ ባሕልነቱ ድግሞ በገናና በሩር ያጫውታል።

### የፋሲካ

ሃይማኖታዊ ባሕልነቱ ፥ የትንሣኤ እምላክን አስመልክቶ የትንሣኤ ሰብን ለማዘከር ሲሆን ፥ እንደፋሲካ ባሕልነቱ ደግሞ ምግበ መረቅ ያስፈተፍታል ።




መውጣት እየፈራኹ ከሚለው ግጥማዊ ይዘት ጋር ይህንን ትንግርታዊ ንግርት የሚያንፀባርቅ ሥዕል እንዴት ያገናዝቡታል



መኖሩ ሕልው ነው — በመንፈስ በአካል ፥

ያላዩኝ ወገኖች — ቢሉም ሞቷል አልፏል !

ለሚፎክሩትም — ፀረ ሰብ ተንባላት ፥

ገላው አካሌ ይኸው — ነፍሴን ግን አይገኟት !